መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 39 ጥር 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99

# የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች
# የቁልቁለት ጉዞ

## መካነ አእምሮ ለመካን ትውልድ?



- የአብዮት መፍለቂያዎች
- "ብሔራዊ" ወይስ "የብሔር" ዩኒቨርሲቲዎች
- ብሔር፣ ጠባብነትና ግጭት በዩኒቨርሲቲዎች
- ክሽፈት በዩኒቨርሲቲዎች ጓዳ
- የመምህራን እሮሮ
- የግጭት መንስዔና ጦሶች በዩኒቨርሲቲ
- ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ
- ነገ ምን ይሁን?



## ሀገራችን እንዴት ከመስቀልያ ትውጣ?
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)



## የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም መርገም
ዮናታን ፍሰሀ (ዶ/ር)



## ለእርቅ ለፍቅር ዘመን ከቶ አይመሽም
መስፍን ጌታቸው



## "በፈተና ያልተፈተሸ ሕይወት ረብ የለሽ ነው"
ወንድሙ ነጋሽ (ኢ/ር) ከለንደን

8 ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለዴሞክራሲ ግንባታ

9 የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም መርገም
ዮናታን ፋሰሀ (ዶ/ር)

10 ፍሬ አልባው ኦነግና የኦዴፓ መቋጫ ያጣ ውዝግብ

11 ለእርቅ ለፍቅር ዘመን ከቶ አይመሽም
መስፍን ጌታቸው

14 ሀገራችን እንዴት ከመስቀልያ ትውጣ?
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

16 ጌታቸው አሰፋና የሕወሓት "የክፉ ቀን" የቤት ሥራ

18 መንግሥት በይቅርታው ገፍቶበታል፤

19 አዲስ አበባ ላይ የሚደመሩት መቀሌ ላይ የሚቀነሱት ደብረጺዮን
ተስፋዬ ሽብሩ

21 ኢትዮጵያዊው የነጻነት ታጋይ ሐኪም
ብሩክ መኮንን



# መካነ አእምሮ ለመካን ትውልድ?



4-7

## የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች
## የቁልቁለት ጉዞ

23 አዲስ አበባ ያረጠችው ከተማ
ጥላሁን መሸሻ

25 ስርዓት አልባዋ ሀገር
ተሾመ ሺፈራው

27 በአቶ ጌታቸው አሰፋ ጉዳይ ፖለቲከኞች ምን ይላሉ?

28 "በፈተና ያልተፈተሸ ሕይወት ረብ የለሽ ነው" ሶቅራጠስ
ወንድሙ ነጋሽ
(ኢ/ር) ከለንደን




ቁጥር 38 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ጥር 11
ይጠብቁን!

# የፌስቡክ መዘዝ ብዙ ነው ተባለ

በዓለም ላይ ያሉ የሶሻል ሚዲያዎች ውስጥ አንድና ዋነኛው የሆነው ፌስቡክ በዓለም ላይ 2.27 ቢሊዮን ተጠቃሚዎች እንዳሉት የሚነገር ሲሆን በቅርቡ በተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ራሳቸውን ከሌሎች ጋር ሲያነፃፅሩ  የእንቅልፍ ችግር፣ የክብደት ለውጥ፣ የጡንቻ መዛል እና የራስ መተማመናቸው ዝቅ እንዲል ያደርጋል ተብሏል፡፡ ግለሰቦች ስለራሳቸው እርግጠኞች እንዳይሆኑና በተለይም ሴቶች በተጨማሪ ሥጋትና ጭንቀት ይበልጥ ለችግሩ ተጋላጭ መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

ራስን ከሌሎች ጋር ማወዳደር አዲስ ነገር አይደለም፤ ነገር ግን በማኅበራዊ አድገት ምክንያት የዕለት ተዕለት ሕይወት እየሆነ መምጣቱ ትልቅ የማኅበራዊ ቀውስ እያስከተለ ነው ተብሏል፡፡

# ለአዲስ አበባ የውሃ ችግር መፍትሄ ተገኘ

የአዲስ አበባ የውሃ ችግር የከተማዋን ነዋሪ ለብዙ እንግልት የዳረገ እንደሆነ ይታወቃል:: በመሆኑም መንግሥት ባወጣው መግለጫ በከተማ ያለው የውሃ ሥርጭት በፈረቃ የሚዳረስና ፍላጎቱና አቅርቦቱ ተመጣጣኝ ባለመሆኑ መ/ቤቱ በሚቀጥሉት 3 ዓመታት የሚጠናቀቁ 3 የውሃ ፕሮጀክቶች ነድፎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጿል::

ይህንንም እውን ለማድረግ በአያት አካባቢ የሚለማና በቀን 68 ሺ. ሜትር ኪዩብ የማምረት አቅም ያለው ፕሮጀክት በሚቀጥለው ዓመት ተጠናቆ አገልግሎት ይሰጣል ብለዋል:: የለገዳዲ የከርሰ ምድር ውሃና የገርዲ ግድብ ፕሮጀክቶች በቀን 159ሺ. ኪዩብ የማምረት አቅም ያላቸው ሲሆን እነዚህም በ2014 ይጠናቀቃሉ ተብሏል:: አሁን በአዲስ አበባ ያለው የውሃ ፍላጎት በቀን 930ሺ.ህ ሜትር ኪዩብ ቢሆንም የመዲናዋ የውሃ የማምረት አቅም ግን 574 ሺ.ህ ሜትር ኪዩብ ነው::

# ብዛት ያለው ሕገወጥ መሣሪያ ተያዘ

በቅርቡ በበርካታ የኢትዮጵያ ክልሎች ብዙ የፀጥታ መደፍረሶች ይስተዋላሉ:: ከነዚህ ክልሎች ውስጥ አንዱ በነበረው የቤንሻንጉል ጉምዝና በኦሮሚያ አጎራባች አካባቢዎች ተከስቶ የነበረ መሆኑ ይታወሳል:: በመሆኑም የእነዚህን አካባቢዎች ሰላም ለመመለስ የተቋቋመው ኮማንድ ፖስት በታጠቁ ኃይሎች ተፈጥሮ በነበረው የፀጥታ መደፍረስ የተጠረጠሩ 171 ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስረድተዋል:: የታጠቀው ኃይል ለግድያና ሌሎች ጥፋቶች ሲጠቀምባቸው የነበሩ 49 ክላሽንኮቭ ጠበመንጃዎችና 1ሺ.ህ 31 የተለያዩ ጥይቶች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ገልፀዋል::

ከዚህ በተጨማሪ ግለሰቦች በሕገ ወጥ መንገድ ሲያንቀሳቅሱት የነበሩ 1.9 ሚሊየን ብር እና 12 ሺ.ህ የአሜሪካ ዶላር መያዙን ኮማንድ ፖስቱ ገልጿል::

# በመከላከያ ሰራዊት የሚመራ ተጨማሪ ኮማንድ ፖስት ሊቋቋመ ነው

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከሰቱ ላሉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍትሄ ይሆናል ብሎ መንግሥት ያቀፈ በመከላከያ ሰራዊት የሚመራ ኮማንድ ፖስት ሊያቋቁም መሆኑን አስታወቀ:: የሀገር መከላከያ ሚንስትሯ ኢንጅነር አይሻ መሐመድ ለፓርላማው እንደገለፁት በክልሎች ጥያቄ ፀጥታ ወደ ደፈረሰባቸው አካባቢዎች የገባው የመከላከያ ሰራዊት የሕዝቡን ደህንነት ለማስጠበቅ በሙሉ ኃይሉ እየሠራና ሀገራዊ ግዴታውን እየተወጣ መሆኑን ገልጸው፣ ኅብረተሰቡም ከመንግሥት ጎን በመቆም ተባብረን የሀገራችንን ሰላም እናስከብር ብለዋል::

# ዶ/ር ደብረ ጽዮን የትግራይ ሕዝብ አይረበሽ አሉ



የትግራይ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረ ጽዮን ገ/ሚካኤል ጥር 1 በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ የትግራይ ሕዝብ ሕጋዊ በሆነው የመከላከያ ሰራዊት ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ ሳይረበሽ በልማቱ ላይ እንዲያተኩር አሳሰቡ::

የክልሉ ሕዝብ የመከላከያ ሰራዊት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ሕጋዊና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችል ነው ብለዋል:: ስለሆነም ይህንን በመረዳት ያለ ምንም መረበሽ የልማት ሥራውን እንዲቀጥልና የሕገ መንግሥት ይከበርልን ጥያቄ እራሱ ከማክበር የሚደምር መሆኑንም ጠቅሰዋል::

የክልሉን ሰላምና ፀጥታ የማስከበር ጉዳይም ሕዝቡ በፈጠረው አደረጃጀት አንድነቱን ማስቀጠል እንደሚኖርበትና የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት ባደረጉት የጋራ ስምምነት የሁመራ-ኦምነሀጀር መንገድ መከፈትም ለሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት ጠቃሚ እንደሆነ ገልፀዋል::

# “ፍልስፍና ሦስት” መጽሐፍ በገቢያ ላይ ዋለ




ይህ መጽሐፍ ለደራሲው ብሩህ አለምነህ አራተኛ ሥራው ሲሆን፣ከዚህ ቀደም “ፍልስፍና 1”፣ “ፍልስፍና 2” እና “የኢትዮጵያ ፍልስፍና” የተባሉ ሥራዎችን አስነብ□ል::ደራሲው በዚህ በአዲሱ ሥራው ውስጥ “የባህልና የትውፊት ተsም የሆነችው የኦርቶዶክስ ቤ/ክ በኢትዮጵያ የሕዳሴና የዘመናዊነት ፕሮጀክት ውስጥ በባለቤትነት የማትሳተፍ ከሆነ ወደፊት የሚገጥማትን ፈተና፣እንዲሁም ሰሞነ ሕማማት እንዴት የኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ምንጭ እንደሆነ” ያብራራል::በተጨማሪም ፣በቅኔና በፍልስፍና መካከል ያለውን ግብግብ ይተነትናል::

# ምርጫ ቦርድ ከፓርቲዎች ጋር ወይይተ አካሄደ

የዴሞክራሲና የምርጫ ተቋማትን የሚመለከቱ ሕጎችን የማሻሻሉ ሂደት ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም ባዘጋጀው መድረክ ላይ ገለፀ::

ምርጫ ቦርድ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሀገርና ለተቋማት ግንባታ ስለሚኖራቸው ፋይዳ ውይይት በተደረገበት ወቅት ፓርቲዎች በአገራዊ ችግሮች ላይ ከማተኮር አማራ መፍትሄ ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በውይይቱ ላይ የተሳተፉ አስተያየት ሰጪዎች አሳስበዋል:: ከጥቃቅን ጉዳዮች ይልቅ በአገራዊ አጀንዳዎች ላይ ማተኮር አለባቸው የሚል ሐሳብም ቀርቧል::

የምርጫ ቦርድን የሚመለከቱ አዋጆችን በተመለከተ ለሚቀርበው ቅሬታም ጥናት እንደተካሄደ እና በቅርቡ መፍትሄ እንደሚሰጠው ጥናቱን ያቀረቡት ባለሙያዎች አስረድተዋል::



# ጫልቱ ታከለ ታሰረች



ለዐሥር ዓመታት ታስራ የነበረችውና በኦሮሚያ ሕዝባዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ስሟ ጎልቶ የሚጠቀሰው ወጣቷ ጫልቱ ታከለ በምዕራብ ኦሮሚያ ወለጋ ከተቀሰቀሰው ግጭት ጋር በተያያዘ በኮማንድ ፖስት አማካይነት በቁጥጥር ስር መዋሏ ታውቋል::

ከዚህ ቀደም የግዮን መጽሔት እንግዳ በመሆን የተፈፀመባትን ግፍና በደል በዝርዝር የገለፀችው ጫልቱ ታከለ ሁለት ጊዜ ከኦነግ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በነበረው አምባገነኑ የሕወሓት መንግሥት ታስራ እንደነበር ይታወቃል:: ሰሞኑን በምዕራብ ወለጋ የተቀሰቀሰውን ሁከትና የኦነግ ጦር የፈጠረውን አደጋ ተከትሎ በክልሉ ኮማንድ ፖስት የታወጀ ሲሆን መንግሥትም ከጉዳዩ ጋር ንክኪ አላቸው፣ የኦነግ አባል በመሆን ፀጥታ እንዲደፈርስ አድርገዋል ያላቸውን 171 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር አውሏል::

ጫልቱ ታከለ ከላይ ከተጠቀሰው ምክንያት ጋር በተያያዘ ረቡዕ ጥር አንድ ቀን ሻምቡ ከሚገኘው ወላጅ እናቷ ቤት በኦሮምያ ፖሊስ የተያዘች ሲሆን መጽሔታችን ለህትመት እስከገባችበት ሀሙስ ጠዋት ድረስ ፍ/ቤት አልቀረበችም:: ጫልቱ በምዕራብ ወለጋ ሆድሩ ጉድሩ ዞን የሚገኘው ኦነግ ጽ/ቤት የምትሰራ የድርጅቱ ተጠሪ መሆኗ ይታወቃል::

## ናሁ ቲቪ ዛሚ ራዲዮን ለሶስት ወር ያስተዳድራል

ሰሞኑን በተለያዩ ማኅበራዊ ድረ ገፆችና ሚዲያዎች ዛሚ ኤፍ ኤም 90.7 ራዲዮ ለናሁ ቲቪ ተሸጧል በሚል የወጣው ዜና ሙሉ በሙሉ የተሳሳተ መሆኑንና፣ ራዲዮ ጣቢያውም ለሽያጭ አለመቅረቡን የዛሚ ባለቤትና ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ዘሪሁን ሙላቱ ለግዮን መጽሔት ገልፀዋል::

“ናሁ ቴሌቭዥን በ16 ሚሊየን ብር ክፍያ ዛሚ ኤፍ ኤም 90.7 ራዲዮን ገዝቷል” የሚለውን ዜና ለማጣራት ለጣቢያው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ስልክ ደውለን ባገኘነው መረጃ መሰረት፣ አስቀድሞ የተናፈሰው ወሬ የተሳሳተ መሆኑን ጠቁመው “ዛሚ ራዲዮ ከሌሎች ራዲዮ ጣቢያዎች ጋር ተፎካካሪ ሆኖ እንዲቀርብና፣ በሥራም ሆነ በገቢ ረገድ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ሲባል የጣቢያውን የማኔጅመንትና ማርኬቲንግ ጉዳዮች በተመለከተ ናሁ ቲቪ ለሦስት ወራት እንዲረከብ ጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም ከስምምነት ላይ ደርሰናል” ብለዋል::

‹‹ምናልባት የአስተዳደርና የማርኬቲንግ ሥራው ድክመት ካለብን በሚል ፕሮግራም ሪቪው፣ የጋዜጠኞችን የብቃት ጉዳይ በተመለከተና በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ናሁ ቲቪ ለተጠቀሰው ጊዜ ብቻ ኃላፊነቱን ወስዶ እንዲሠራ ከስምምነት ላይ በመደረሱ፣ በተጠቀሰው ቀን ለጣቢያው ሠራተኞችም ጉዳዩ በይፋ ተገልጿል” በማለት ለዝግጅት ክፍላችን አስተያየታቸውን የሰጡት የዛሚ ሬድዮ ባለቤት አቶ ዘሪሁን ሙላቱ የቢዝነስ ስምምነቱን ዝርዝር ለጊዜው ባያሳውቁም ጣቢያው ለሌላ ወገን ተላልፎ አለመሸጡን ግን አረጋግጠዋል:: ባለፈው ሳምንት በተመሳሳይ ሁኔታ ዛሚ ሬድዮ “ለጃዋር መሐመድ ተሸጠ፤ አብርሃም ወልዴ ገዛው” የሚሉ ወሬዎች በስፋት መሰራጨታቸው አይዘነጋም::

## የጀርመኑ ፕሬዝዳንት ኢትዮጵያን ሊጎበኙ ነው

የጀርመኑ ፕሬዝዳንት ፍራንክ ዋልተር ስቴይኑሚየር በያዝነው ወር መጨረሻ ለ3 ቀናት ኢትዮጵያን ሊጎበኙ ነው:: ፕሬዝዳንቱ በሚያደርጉት ይፋዊ የሥራ ጉብኝት ከኢፌድሪ ፕሬዝዳንት ሳህለ ወርቅ ዘውዴ እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ጋር የሁለትዮሽ ወይይትን ጨምሮ ታሪካዊውን የላልይበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያንም ይጎበኛሉ::

ኢትዮጵያና ጀርመን ከ56 ዓመት በላይ የልማት ትብብር ሲያደርጉ የቆዩ ሲሆን ጀርመን ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቶች የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ግብርና እና ብዝሃ ሕይወት ድጋፍ ከሰጣቻቸው ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው:: ወደ 35 የሚጠጉ የጀርመን ኩባንያዎችም በኢትዮጵያ በአበባ ልማት በሎጀስቲክ በትራንስፖርትና በፋርማሲቲካል ዘርፎች ላይ ተሰማርተዋል::

# መካነ አእምሮ ለመካን ትውልድ?

# የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች የቁልቁለት ጉዞ

መላክ ቢ.


መካነ አእምሮ የእንግሊዘኛውን ቃል “ዩኒቨርሲቲ” ተክቶ ሥራ ላይ የዋለ አማርኛ ነው። ትርጉሙ የአእምሮ ማጎልመሻ፣ ማበልጸጊያ ቤት እንደማለት ነው። ይህ የአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብትና ፖለቲካ የሚፈተፈትበት ግዙፍ የትምህርት ተቋም ዛሬ ከመካነ አእምሮነት ወደ ትውልድ መምከኛነት እየተለወጠ የመሄዱን ምልክት ዕያሳየ ነው። በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሊሰፋ የመጣ ተማሪ እየጠበበ የሚወጣበት፣ ከዚያም አልፍ ሲል ብዕር መጨበጥ በሚገባው እጅ ዱላ እየተሸከመ የሚደባደብበት እና የሚገዳደልበት የጠባብ ብሔርተኝነት ትርክት ውስጥ ገብቷል።ዩኒቨርሲቲዎች የቁልቁለት ጉዟቸውን ጀምረውታል። በዚህ ከቀጠሉ ምናልባትም ከተማሪና ሀገር ከሚገነባ ትውልድ መብቀያነት ወጥተው የዚህች ሀገር የርስ በርስ ግጭት መፍለቂያ ስፍራዎች የሚሆኑበት እድል የሰፋ እንደሚሆን የብዙዎች ስጋት ነው። ለዚህ ደግሞ መምህራን ከነውጠኛ ተማሪዎችና ከእሳት ጫሪ ባለተልዕኮ ግለሰቦች ያላነሰ ምናልባትም እኩል ድርሻ አላቸው ተብለው እየተተቹ ነው።በሌላ በኩል የነበረው ከፋፋይ ሥርዓት ለዘመናት ስሩን በተከለበት ዩኒቨርሲቲ  የቀበረው የክፍፍል ችግኝ ጸድቆ ማፍሪያው ላይ የመድረሱ ምክልት ነው ብለው ችግሩን በቀደመው ኢሕአዴግ ላይ የሚያላክኩም አሉ። በቅርብ ጊዜ ደግሞ የዩኒቨርሲቲዎቹ የቁልቁለት ጉዞ ነዳጅ ሰጪዎች ራሳቸው መምህራኑ ናቸው ብለው የተቹም አሉ። ችግሩ የቱ ጋ ነው?

### የአብዮት መፍለቂያዎች

ከቀደመው የአጼ ኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ዩኒቨርሲቲ እና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሕዝብ ጥያቄ የሚስተናገድባቸው መድረኮች ሆነው ነው የፖለቲካ ተሳትፏቸውን በጉልህ የጀመሩት። የያኔው ትውልድ የሚባለው የ60ዎቹ ፖለቲካ አቀንቃኝ የአጼውን አገዛዝ በመሬት ላራሹ መፈክር የነቀነቀው መነሻውን ከዩኒቨርሲቲ አድርጎ ነው። የቀድሞው አጼ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በማርክሲስት ሌኒኒስት አብዮት የነደደውን የያኔውን ወጣት አፍርቶ ለጭቁኖች መብት እንዲታገልና ለአንዲት አብዮታዊት ኢትዮጵያ እንዲፋለም ማድረጉ እንዳለ ሆኖ በሌላ በኩል የብሔር ፖለቲካም የተጠነሰሰበትና ዛሬ ድረስ ለተረፈን አለመስማማት ምክንያት የሆነው ትርክት የወጣበት ተቋም ነው።

የዘመኑ አንባቢ ትውልድ በጊዜው በፈጠረው ሁለት ቡድን ተቧቅሶና እርስ በርስ ተላልቆ እጁን ለደርግ አገዛዝ ቢያስረክብም በጓሮ በር ዞሮ የመጣውና ኢሕአዴግን ይዞ ሀገር የመራውም የዚያው ዩኒቨርሲቲ ውጤት የሆነው ትውልድ ነው። ምንም እንኳን ተውልዱ አብዮተኛ ሆኖ መገለጫውም አብዮት ቢሆንም ከዛሬ በተሻለ ብቻ ሳይሆን እጅግ በላቀ መልኩ የሕዝብን ጥያቄ ያነገበ ተውልድ ነበር። ታግሎም ያታገለ፣ ነቅቶ ያነቃ፣ ተደራጅቶ ያደራጀ በአጠቃላይ የዜጎች መብት አንዲጠበቅ አጥብቆ የጮኸ ትውልድም ነው። ማሩን በግራዋ በርዞ ወደ ብሔር ትርክት ከገባ እና የስታሊንን ርዕዮት መከተል ከጀመረ በኂላ ለዚህች ሀገር በማይሠራ እና ዓለም ሞክሮት ከውድቀት ባለፈ ምንም ባላተረፈበት መንገድ ሀገርን የነዳም ትውልድ የወጣው ከዩኒቨርሲቲ ነው።

በደርግ ዘመን አብዮት ቆስቁሱ ሥልጣን ላይ ያወጣው ተማሪ መሆኑን ያልዘነጋው ወታደራዊ አገዛዝ በራሱ ዘመን ሌላ አብዮት እንዳይመጣ አፍኖና ጨፍልቆ ዝም አስብሎታል። መንግሥቱ ሃይለማርያም ዝመቱ ለማለት ዲስኩር ከማሰማቱ ባለፈ ዩኒቨርሲቲ ከማናቸውም የፖለቲካ ተዋስዖ ርቆ ኖሯል። ►




ዛሬ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ተቆጣጥሮ እግሩን ሲያደረጅ የደርግን አምሳያ እቀባ እና አፈና ያካሄደው በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን በመምህራኑም ጭምር ነው። ከደደቢት የመጡት ሕወሓቶች የቀድሞ የትምህርት ቤት ጓዶቻቸውን እዚሁ ዩኒቨርሲቲ ቢያገኟቸው ሥልጣናቸው ገና ሳይደላደል በፊት 40 የዩኒቨርሲቲ መምህራንን መርጠው ለማባረር በቁ። ከዚያ የጀመረው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድህነት አዘቅት ወርዶ ዛሬ በቀበሌ ጉዳይ ለመነታረክ አልፎም ለመጋደልና ለመጥበብ በቃ።

## “ብሔራዊ” ወይስ “የብሔር” ዩኒቨርሲቲዎች

የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እድገት እዝጋሚ ነው በሚል መነሻ ፣ ወዲህም በየክልሉ ዩኒቨርሲቲ ገንብቶ ለተወላጆች ቅርብ የሆነ የትምህርት ተቋም ማዳረስ በሚል ሽፋን በየክልሉ የተገነቡት ዩኒቨርሲቲዎች ሲቀድም ምንም ዓይነት ፌዴራላዊም ይሁን ሀገራዊ ቀለም የላቸውም። ከነአርማቸው ከዘመን ተሻጋሪ እና ከዓለምአቀፋዊ እሳቤ ይልቅ አንድ የኀብረት ሱቅ ሊለጥፈው በሚችለው የየአካባቢው መለያ ምስል (ኮባ፣ ጎጆቤት፣ በርጩማ፣ ጥለት ወዘተ) ራሳቸውን አጥብበው ፣ ስማቸውንም በዚያው ክልል አጥረው በባዶ መምህር እና ባልረባ የትምህርት መርጃ ቁስ ትምህርት ሲጀምሩ እንደማይዘልቁበት አመልካች ነበር።

ዩኒቨርሲቲ መገንባት ለፉክክር እና አለኝ ለማለት ብቻ አስመስለው በተገነባላቸው ቁጥር እንደቱሪስት መስህብ የሚደነቁት ክልሎች ከገዛ ክልላቸው ከወጣው ይልቅ ከተለያየ ቦታ ከመጣው ተማሪ ጋር ጊዜያቸውን እያሳለፉ መድረክነታቸውን ለብሔር ፍትጊያ አውለው ነገሩን አርክሰውታል።

የትምህርት ዘርፉ በሽታ ሆኖ የኖረው የአካዳሚ ነጻነት አለመከበር በዘለቀበት ሀገር ላይ ዩኒቨርሲቲዎች የኢሕአዴግን የዘር ወረርሽኝ እና ብሔር ቡድንተኝነት ከማሳለጥ ባለፈ የረባ ሀገራዊ ተዋስጾ ሳይኖራቸው ነው ዛሬ ላይ የደረሱት። እያንዳንዱ የኢሕአዴግ አባል ድርጅት ቢሮ ይዞና ተቧድኖ ከየክልሉ የሚመጣውን ኢትዮጵያዊ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ደቡብ እያለ በአራት እያቧደነ አጋር የኢሕአዴግ ድርጅቶችን እንኳን የሚያማክልበት አሠራር ሳይኖረው ሁሉንም በከፋፋይ አጀንዳው ሲጠቀምባቸው ኖሯል።

ተማሪዎች ከትምህርታቸው ይልቅ በባከነ የብሔር ፖለቲካ ላይ ጊዜያቸውን በማሳለፍ ሥራ የመቀጠር ዋስትና ለማግኘት ሲለፉ የአካዳሚ ጉዳይ ገደል ገብቷል። መምህራን በበኩላቸው በተመሳሳይ መልኩ ተደራጅተው በብሔር ከተማሪ ጋር ሲጠቃቀሙና ሲጎዳዱ ነው ዘመን ያሳለፉት። በዚህ ሳቢያ ሀገር አቀፍ አጀንዳ ቀርቶ ብሔር ተኮር ጥያቄና መልስ ያልሆነ ምላሽ ሲደመጥባቸው ቆይተዋል። ዩኒቨርሲቲዎች ያቀነቅኑት የነበሩት ብሔራዊ አንድነት እና የሕዝብ መብት መከበር የወረዳ ወረዳ ወርዶ በአማራ ነኝ ትግሬ ነኝ ብሽሽቅ እና ቁርሾ ውስጥ ሲገባም ታይቷል።ለዚህ ክስረቀት ቀዳሚ ተጠያቂ ሥርዓቱ መሆኑም አሌ የማይባል እውነት ነው።

## ብሔር፣ ጠባብነትና ግጭት በዩኒቨርሲቲዎች

ጥላቻ እና ልዩነትን እንደአንድ የፖለቲካ መሳሪያ የሚቆጥሩና ይህች ሀገር ከዚህ መስመር ዘልላ ወደሉላዊው ሥርዓት እንዳትቀላቀል አንቀው የያዟት በብሔር ፖለቲካ የናወዙ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ይህንኑ ትርክት ከጥላቻ ሚዛን ላይ ሳያወርዱ በተማሪዎቻቸው ላይ መርዝ ሲነዙ የሚውሉ መምህራንም ጭምር ናቸው።

ተቋማቱን ከምርምር ማዕከልነት ወደ ግጭት መናኸሪያነት ለመለወጥ ሲንቀሳቀሱ ምክንያታዊ ሆነው አይደለም’። የግለሰብ ጉዳዮችን አግዝፈው ወደ ብሔር እና ሃይማኖት ተኮር ግጭት ሲቀይሩ መኖራቸው ፍሬ አፍርቶላቸውም ዩኒቨርሲቲዎች የጥበት ማዕከላት እንዲሆኑ፣ የግጭት መዝሙር ሪትም የሚቀመርባቸው ስፍራዎች እንዲሆኑ ምክንያት ፈጥረዋል።

ዘረኝነት ከሰው ባሕሪይ የተደመረ ሳይሆን ከሰው ሐሳብ ጋር አብሮ የመጣ ትርክት ነው። በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ ዘረኝነትን የሚያራምዱና በእንጭጩ መወገድ የሚኖርባቸው ሐሳቦች አሉ። ዩኒቨርስቲዎች የዕውቀትና የትምህርት ገቢያ እንጂ የፖለቲካ ማዕከል መሆን የለባቸውም የሚል ሐሳብ ያላቸው አካላት በዚህ እርምጃ የትም መጓዝ እንደማይቻል ሲናገሩ ኖረዋል።

## ክሽፈት በዩኒቨርሲቲዎች ጓዳ

ዩኒቨርሲቲዎች የምሁራን ጓዳዎች ናቸው። የመካነ አእምሮ ጓዳዎች ሀገርን መለወጥ የሚችል ምሁራን የሚፈሩባቸው ስፍራዎችም ናቸው። በሀገራችን ባሉት 45 ዩኒቨርስቲዎች የሚገቡ ተማሪዎች ወደፊት አንድ ሀገር ለመገንባት ሀገር ተስፋ የጣለችባቸው ቢሆኑም በተቃራኒው ግን አዲስ

ቋንቋ መልመድና ማወቅ ሲገባቸው ቋንቋን የልዩነት ምክንያት ማድረግ ከማይማሩት መሃይማን በምንም አይሻሉም ለሚል ስድብ ያጋልጣቸዋል።

ባለፈው ጊዜ በአሶሳ ዩኒቨርስቲ ህዳር 10 ቀን የተነሣው ብጥብጥ ቋያው ተፋፍሞ በብዙ የሃገራችን ዩኒቨርሲቲዎች ተላልፎ አደጋ አንዣብቦ ነበር። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፌዴራሉ መንግሥት መቀመጫ በሆነችው መዲና ውስጥ የሚገኝ እንደመሆኑ ፖለቲካውን አገናዝቦ በአብዛኛውም ምክንያት ይዞ የሚደግፍና የሚቃወም ቢሆንም ሌሎች በክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ግን አስፈላጊ ጥያቄ አንኳን መጠየቅ እየተሳናቸው በግለሰቦች ጸብ መሃል የብሔርን ጥያቄ ለማንሳት ሲጣደፉ፣ ቢዘያም ሳቢያ ሲፈናከቱ ታይተዋል።

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር (ቀድሞው ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር) ዶ/ር ሂሩት ወልደ ማርያም "በቤኒሻንጉል ክልል በሚገኘው አሶሳ ዩኒቨርስቲ በሁለት ተማሪዎች ጠብ የተነሣ ሦስት ተማሪዎች ሕይወታቸው ሲያልፍ 40 ተማሪዎች መቁሰላቸው ሲናገሩ በፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ተስፋ መቁረጥ ለብዙዎች መልዕክት ነበረው።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በበኩላቸው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ እያጋጠመ ያለውን የሰላም እጦት ለመቅረፍ መንግሥት ያካሄደው እንቅስቃሴ ጠንካራ ነው ቢሉም ለውጥ አምጥቶ የተሻለ የመማር ማስተማር ሂደት ሲፈጠር ገን አልተስተዋለም።

አቶ ደመቀ የተማሪዎችን ረብሻ መንስዔ ያሳዩበት መንገድ ኢሕአዴግ አሁንም የችግሩን መድሃኒት ከስሩ ላይ ማፍሰስ አለመቻሉን የሚያመላክት ነው ሲሉ ብዙዎች ተችተዋቸዋል። እንደ ም/ጠ/ሚኒስትሩ ገለጻ በትምህርት ተቋማት ለሚፈጠረው ችግር እንደ መንስኤ ለተቋማቱ የሚመጥን አመራር አለመኖር ፣ ችግሮች ሲነሱም ለችግሮች አፋጣኝ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ የማባባስ አዝማሚያ ማሳየት ዋናዎቹ ናቸው ብለዋል።

የመውጫ ፈተና ከተቋም ተቋም የተለያየ መሆን ፣የተማሪዎች ወጥ ያልሆነ የምደባ ሥርዓት እና ተፈላጊነታቸው ያልተረጋገጡ የትምህርት ክፍሎች መኖር ለግጭቶቹ ምክንያት ናቸው ቢሉም የተዘረዘሩት ችግሮች መቀስቀሻ ከመሆን እንደማይዘሉ ፣ በአንጻሩ ደግሞ መሰረታዊው ምክንያት ያለፉት 27 ዓመታት የፖለቲካ ሴራ መሆኑን መግለጽ ግድ እንደሆነ ተተችተዋል።

ለዚህም ይመስላል አቶ ደመቀ የብሔር ግጭቶች በዩኒቨርሲቲዎች ከተስፋፋበት ምክንያት አንዱ የራስን የፖለቲካ ፍላጎት በሌሎች ላይ የመጫን ፍላጎት ያላቸው መምህራንና አመራሮች የፈጠሩት ችግር ነው በማለት ተናግረዋል። በርግጥም መምህራኑ በዚህ ተወቅሰዋል።

## የመምህራን እሮሮ

በቅርቡ የሰላም ሚኒስቴር ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ የትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ አመራሮችን ጨምሮ ብዙዎች መምህራን እና ወኪሎች ተገኝተው ነበር። የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ ለግጭት ያለው ድርሻ እና ግጭትን ለማስወገድ መጫወት የሚገባውን ሚና በተመለከተ ብዙ ተብሏል። ከዚህ በላይ ግን መምህራን በትምህርት ተቋማት ሰላም ላይ ሊኖራቸው በሚገባው ሚና ላይ ተንተርሰው ከመምህራን ጋር ውይይት ያደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ለመምህራኑ ታላቅነትና ትውልድ ቀራጭነት ያላቸውን አድናቆት ገልጸው ነገር ገን በዚያው መጠን ትውልድ ተጣምሞ እንዲያድግ የነርሱም ድርሻ አንደሚኖርበት ነግረዋቸዋል። ከዚህ አንጻር በቀድሞው ዘመን መምህራን ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ እንዲሰበሰቡ ሲደረግ እና ከዚህ ቀደም ፍቼ ከተማ ላይ ኢሕአዴግ እድርጎት እንደነበረው ሁሉንም መምህራን መልምሎ ኢህአዴግ ለማድረግ ያካሄደውን ምዝገባ ላሰበ ዛሬ መምህራን በነጻነት ትውልድን የመቅረጽ ተግባራቸውን የሚወጡበት ዘመን ላይ ለመገኘታቸው ዋስትና ይሰጣል።

> **በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ሊሰፋ የመጣ ተማሪ እየጠበበ የሚወጣበት፣ ከዚያም እልፍ ሲል ብዕር መጨበጥ በሚገባው እጅ ዱላ እየተሸከመ የሚደባደብበት እና የሚገዳደልበት የጠባብ ብሔርተኝነት ትርክት ውስጥ ገብቷል**

መምህራን የአንድ ማኅበረሰብ ቀራጭ እንደመሆናቸው በተለይ በዩኒቨርሲቲዎች ግቢ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያቸው በሚካሄዱ ማናቸውም ማኅበረሰባዊም ይሁን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚኖራቸው በጎና አሉታዊ ተጽዕኖ የጎላ ነው ። ይህንን ማኅብራዊ ደረጃቸውን እንዲጠቀሙበት በዚሁም ክብር እንዲያገኙበት ከከፋፋይ አጀንዳ መራቅ ይገባቸዋል የሚለው ሐሳብ የብዙዎች ነው። ለምሳሌም በብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ለተነሱ ብሔር ተኮር ግጭቶች አንድም የዳር ተመልካች አለያም መሀል ባይገቡም ቆስቋሽ መምህራን መኖራቸው መነገሩ ለበዙዎች ማፈር እና እሮሮ ማሰማት ምክንያት ሆኗል። እንደአምቦ ዩኒቨርሲቲ ያሉ ተቋማት በዩኒቨርሲቲ አመራሮች ግጭትን ለማብረድ እና ሰላማዊ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴ ለማድረግ የተወሰዱ እርምጃዎች አበረታች ቢሆኑም በዚያው መጠን መምህራን ከዘመኑ የትውልድ ዝቅጠት ለመዳን ራሳቸውን ከጥላው ሲያሸሹና በምን ቸገረኝነት ሲመለከቱ ያየ ሰው ቢወቅሳቸውና ተባባሪ ቢያደርጋቸው የሚገርም አይሆንም።

የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ታደሰ ቀንዓ አመንቴ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያስተላለፉት መልዕክት ስሜት የሚነካ ነበር።

*"አጠገባችሁ ያለው ተማሪ ወንድማችሁ እንደእናንተው ከምስኪን ቤተሰብ የተገኘ፣ ጭራሮ ለቅማ፣ ጠላ ሸጣ፣ ግፋ ቢል በጉሊት ችርቻሮ ወይም በመንግሥት ሥራ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ የምትኖር የአንተንው እናት የምትመስል እናት/ ሀርሜ አለችው።እንዳ አንተው በእርሻ፣ በመለስተኛ ንግድ ወይም በመንግሥት ሥራ የሚተዳደር አባት፣ እንዳ አንተው ነገ ተመርቀህ ለራስህና ለእኔ ታሳልፍልኛለህ ብሎ ተስፋ የሚጣልበትና የሚያዝንለት ወገን ያለው ወገንህ ነዉ። ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሁነው በቃላት ተነጋግረው መግባባት የሚያቅታቸው ሌሎች የኢትዮጵያ ጠላቶች የጫኑባቸውን ሐሳብ ብቻ ተሸክመው በዱላና በፌሮ ብረት ችግር ለመፍጠር ከሞከሩ የእነዚህ ተማሪዎች ዲግሪ ምን ጥቅም አለው።"* ነበር ያሏቸው።እንዲያም ብለው ተማሪዎቻቸውን አስታርቀውና ትምህርት አስጀምረው የአቋም መግለጫ እስከማስወጣት አድርሰዋቸዋል።

ቡድንተኝነት፣ ጠባብ ብሔርተኝነት እና ዳተኝነት በሰፈነባቸው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ትውልድን መቅረጽ ከባድ ቢሆንም መምህራን ግን ይህንን ትግል በአሸናፊነት መወጣት እንዳለባቸው የታወቀ ግዴታ ነው። ከዚህ አንጻር ትብትብ ፖለቲካውን ከሕይወት ልምድ ጋር አቀናጅተው አርአያ እና በትውልድ ተከባሪ ይሆኑ ዘንድ የሙያ ክብራቸውን በሚያስጠብቅ መልኩ መልካም ማድረግ የነርሱ ፋንታ ይሆናል የሚል ድጌታም የጣሉባቸው ብዙ ናቸው¸መንግስትን ጨምሮ።

## የግጭት መንስዔና ጦሶች በዩኒቨርሲቲ

አቶ ደመቀ መኮንን በዩኒቨርሲቲዎች ለሚነሱ ችግሮች ምክንያት ናቸው ብለው ካስቀመጧቸው ችግሮች መካከል መርጠው መፍትሄ ነው ያሉትን ተናግረው ነበር።

*"የፖለቲካም ሆነ የሃይማኖት እንቅስቃሴ እንዳይኖር መከታተል፣ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችንና መሰረተ ልማቶችን*

*በፍጥነት ማስተካከል ፣በዩኒቨርሲቲዎች ዙሪያ የሚገኙ የንግድ ቤቶችን ተግባር መፈተሸና ሁከት ፈጣሪ የሆኑ ተማሪዎችን መለየትና እርምጃ መውሰድ”* ብለዋል:: ይህንን ለማድረግ ከጎራው የወጣ እና ሀገር ግድ የምትለው የዩኒቨርሲቲ አመራር ያስፈልጋል::

በአብዛኛው ዩኒቨርሲቲዎች ብሔር ተኮር በሆነ አደረጃጀት ታጥረው ክልል አቀፍ አመለካከት ይዘው ብሔራዊነትን መርሳታቸው ምክንያቱ የፕሬዚዳንቶቹ ምደባ ነው የሙሉ ወገኖች አሉ::

በየክልሉ ለተቋቋሙ ዩኒቨርሲቲዎች በኮታ የሚዳረሱ መምህራን የዚያን ብሔር አባል መሆናቸው ሳያንስ በዚያው መጠን ፕሬዚዳንቶቹን ሆን ብሎ ከዚያ ብሔር ማድረግ የብሔር ፌዴራሊዝም ጦስ በትምህርት ተቋማት ውስጥ መግባቱን አመልካች ነው:: በዚህ ሳቢያ በፕሬዚዳንቶቹ ከባቢ የሚኮለኮለው የጎሳና ብሔር ዘመዳዘመድ ሐቀኛ እና ትምህረት ብቻ ትኩረታቸው የሆነ መምህራንን በማግለል ከጨዋታ ውጪ እያደረጋቸው ለጥላቻ እና ምን ቸገረኝነት ይዳርጋቸዋል:: ይህ አሠራር ቆሞ ፕሬዚዳንትነት ብሔርን ባማከለ መልኩ ሳይሆን የአካዳሚክ እና የማስተዳደር እውቀት ተዳምረው በሚሰጡት መመዘኛ መመረጥ እንደሚገባው ብዙዎች ያምናሉ::

**የኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት እድገት እዝጋሚ ነው በሚል መነሻ ፣ ወዲህም በየክልሉ ዩኒቨርሲቲ ገንብቶ ለተወላጆች ቅርብ የሆነ የትምህርት ተቋም ማዳረስ በሚል ሽፋን በየክልሉ የተገነቡት ዩኒቨርሲቲዎች ሲቀድም ምንም ዓይነት ፌዴራላዊም ይሁን ሀገራዊ ቀለም የላቸውም**

## ዩኒቨርሲቲዎች ዛሬ

በአንድ ወቅት ቢቢሲ ራዲዮ ይህንን ዘግቦ ነበር “በተማሪዎች መካከል ማንነትን መሠረት አድርገው የሚነሱ ግጭቶችን ተከትሎ በተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል:: የአካል ጉዳት ከመድረሱም በተጨማሪ ንብረትም ወድሟል:: ይህ ክስተትም የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማስተጓጎሉም ባሻገር ጥቂት የማይባሉ ተማሪዎች ለደህንነታቸው በመስጋት ወደየመጡበት ለመመለስ ሲገደዱ፤ ሌሎች ደግሞ ሥጋት ውስጥ ሆነው በየዩኒቨርሲቲዎቹ ባልተረጋጋ መንፈስ ይገኛሉ::በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የነበሩ በርካታ ተማሪዎች በየተቋሞቻቸው ባጋጠሙ ግጭቶች ሳቢያ ለደህንነታቸው በመስጋት የጀመሩትን ትምህርት አቋርጠው ወደየመጡበት አካባቢ ለመመለስ ተገድደዋል”

በርግጥም የሆነው ይህ ነው:: እናትና አባት ይማርልኛል ብለው የሚልኩት ልጅ ባልታወቀ የብሔር ግጭት የጦር ቀጣና ውስጥ መሆኑን ቢነግራቸው በርሱ ሳይሆን በሀገራቸውና በልጆቻቸው የወደፊት እድል ላይ ተስፋ ይቆርጣሉ:: አንድ ወላጅ ልጁን ወደክልል ሲልክ ርቀት እና ምግብ አለመመቸት ያስጨንቀው የነበረበት ጊዜ አልፎ አሁን ደህንነቱ ካስጨነቀው የአንድ ሀገር ኑሮ ትርጉም አልባ ሆነ ማለት ነው:: ይህ ከዩኒቨርሲቲ የሚጠበቅ ውጤት አልነበረም::

በዚህ ችግር ውስጥ ከነበሩ ተማሪዎች አንዱ ትምህረት ሚኒስቴት ከክልሉ አርቆ እንዳይመድበው ከጓደኞቹ ጋር ጠይቆ ነበር:: ሚኒስቴሩ ዩኒቨርሲቲዎች የፌዴራል ናቸው:: እንዲህ አይነት ጥያቄ አንቀበልም በማለቱ ትምህርቱን ትቶ ተቀመጠ:: ያ ተማሪ እንዳለው ከ 5 ወር በኂላ እርሱ እምቢ ብሎ በቀረበት ዩኒቨርሲቲ ሊማሩ የሄዱ ጓደኞቹ ተሰድደው በችግር ወደትውልድ ቀያቸው ተመለሱ:: ጊዜው ይኸው ነው::

የተለያዩ ተማሪዎች እንደሚሉት በዩኒቨሲቲዎቹ የሚነሱት ግጭቶችና ጥቃቶች በቀላል አጋጣሚ የሚጀመሩ ቢሆንም እንኳን የሚያስከትሉት ጉዳት ቀላል የሚባል አይደለም:: የሚደርሰውን ጉዳትም ለመከላከል ተቀናጅቶ በአንድነት የሚሰራ አካል ባለመኖሩ የከፋ ሁኔታ እንዲፈጠር ምክንያት ነው:: ለምን በምንማርባቸው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሚከሰቱ ግጭቶችና ጥቃቶች ሳቢያ ደህንነት ተሰምቶን ትምህርታችንን መከታተል አልቻልንም ያሉ ተማሪዎች በሩን ያንኳኩበት የትምህርት ሚኒስቴር፤ ችግሩ የሀገሪቷን ሰላም የማይፈልጉ ኃይሎች የፈጠሩት እንጂ የሕዝቡም ሆነ የተማሪዎቹ ችግር አይደለም ብሎ ጥያቄያቸውን ዘግቶታል::

## ነገ ምን ይሁን?

የማኅበራዊ ሚዲያው አባባሽእና ሃላፊነት የማይሰማቸው ሚዲያዎች ሽፋን ተደምሮበት የዩኒቨርሲቲዎች እሳት በቀላሉ የሚቀጣጠል ቋያ እየሆነ ነው:: ያንን ለመግታት የግድ ከፍ ያለ ስራ መሰራት አለበት አለያ ትውልድ እንዲከስም ጉድጓድ መቆፈር ይገባል ይላሉ አስተያየት ሰጪዎች:: ለዚህ ኃላፊነት ቁጥር አንድ አድርገኸው የሚያጯቸውም አስተማሪዎቸን ነው::

*“የዩኒቨርሰቲ አመራሮችም ከአካባቢ ሳጥንና ከጎጥ አስተሳሰብ በመውጣት ለዩኒቨርስቲው በሚመጥን አእምሮና በዓለም ዐቀፍ እይታ ማሰብ ይኖርባቸዋል::የዘረኝነት ነቀርሳ እግዚአብሔር ይማርህ የማይባል ክፉ በሽታ ነው::በበጎች መካከል ያደቡ ተኩላዎችን የዩኒቨርሰቲ አመራሮች በጥንቃቄ የመለየት ሥራ መሥራት አለባቸው::”*

በርግጥም ይህንን ማድረግ ከመምህራን ሳይሆን ከዩኒቨርሲቲ ማኅብረሰብ የሚጠበቅ ተግባር ነው:: የዩኒቨርሰቲን ካባ ለበሶ የዘረኝነትን ጨዋታ ማስፈጸም ሀገርን ብቻ ሳይህን እያንዳንዱን ዜጋ ማቀጨጭ በዚያውም መግደል በመሆኑ ጨዋታው የትም አያደርስም፤ በአንድ ጽሑፍ ላይ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲጎቡ አሉ የተባለው ሐቅ እዚህ ላይ ቢገባ የተሻለ ሐሳቡን ሊገጸው ይችላል:: “ሐሳባችሁን ለዕለት ጥቅም ብቻ እንዲያገለግል አታድርጉት ፤በነፍስም በሥጋም እንድትጠቀሙ መንፈሳዊ ትምህርትንና *ሥጋዊ ትምህርትን በርትታችሁ ተማሩ“*

መንፈሳዊነት የግል ምርጫ ቢሆንም ዛሬ ግን ሐሳብን ከቀን የማያልፍ አድርጎ መስራት በተመለመደበት ዩኒቨርሲቲ የቁልቁለት ጉዞው እንዳይፈጥን የነገንም ማሰብ መልመድ መተግበርም ጭምር ሊበረታታ ይገባል:: ይህ ሲሆን ነው ትውልድ መዳን የሚችለው::

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱም ከመንደርና ከክልል አስተሳሰብ ሳይላቀቁ ማንኛውንም ኃላፊነት በብሔር ማንነት እየሰጡ፣ የሌላ አካባቢውን ተማሪ በገዛ አገሩ እንደ ባዕድ ዕያዩ… ወጥተው የሚመጥናቸውን ዓለም አቀፋዊነትን ማስተማር ባለመቻላቸው፣ በአካዳሚክ ነጻነት ሐሳብን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመግለጽ፣ የመደራጀትና ዴሞክራሲንና አገራዊ አንድነት በተግባር የማሳየት ትግል ባለማስጀመራቸው የዘሩትን ማጨድ ጀምረዋል፡ ይላል በጉዳዩ ላይ በበይነመረብ ላይ የሰፈረ አንድ ጽሑፍ::

*“እንደልምዱም ሆነ ግዴታው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ዜጎች በነጻነት የሚንቀሳቀሱባቸው፣ ለአገር ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮች የሚከናወኑባቸው፣ ወጣቱ ትውልድ የሚቀረፅባቸው፣ ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጥባቸውና መሰል ተግባራት የሚከናወኑባቸው የልቀት ማዕከላት ሊሆኑ ይገባል:: ግልጽነት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሌለባቸውና ማንም እንደፈለገ የሚፈነጭባቸው ከሆኑ ግን ከጠቀሜታቸው ይልቅ ጉዳታቸው ይብሳል:: ትውልዱን ከመቅረፅ ይልቅ እንዲደነዝዝ የሚፈቅዱ ከሆነ ባይኖሩ ይመረጣል:: በአንዳንድ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚታዩ ዘረኝነት፣ ቡድንተኝነት፣ ሙስና፣ ፣የትምህርት ጥራት መጓደል ፣ ለአካዴሚያዊ ነጻነት አለመኖር ፣ ሕገወጥ አሠራሮችና ለመማር ማስተማር ሒደቱ ፈታኝ የሆኑ ድርጊቶች ከሥር መሠረታቸው ሊናዱ ይገባል::”* ብዙዎች እንደሚያስቀምጡት የመፍትሄ ሐሳብ::

የትውልድ ማፍሪያ ሥፍራ የትውልድ መምከኛ ሲሆን ማየት በርግጥም የነገን ጉዞ አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ጥርጥር የለውም::ያ መንገድ ደግሞ ለዩኒቨርሲቲዎቹ የቁልቁለት ጉዞ ፣ ለትውልዱ ደግሞ የመምከን ጅማሬ ነው:: ከዚያ በፊት ግን ይህ አገር ነዳፊ ተቋም ግንቡ በጥላቻ ሳይሰራበት በፊት ሊደረስለት ይገባል::

# ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለዴሞክራሲ ግንባታ

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ከመምህራን ጋር ያደረጉት ውይይት የብዙዎችን ትኩረት ስቦ አልፏል::የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍልን ማእከል ያደረገ ውይይት በአፋኙ የሕወሓት/ኢሕአዴግ የአገዛዝ ዘመን የተለመደ ነበር::የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የወጣቶች፣የሴቶች እና የሙያ ማኅበራትን በተለያየ ጊዜ እየሰበሰቡ ከሕዝብ ግንኙነት ፍጆታ የዘለለ፣የዜጎችን ተሳትፎ የሚያጎለብት ግልጽ የፓለቲካ ሥርዓትን በማንበሩ ረገድ የተጫወቱት ሚና እዚህ ግባ የማይባል እንደነበረ እሙን ነው::አዲሱ የለውጥ አስተዳደር ከቀደመው አገዛዝ ለመለየቱ አንዱ ማሳያ በዚህ ማእቀፍ ውስጥ የሚተገብረው ፋይዳ ያለው እንቅስቃሴ ይሆናል::

ከሰፊው ሕዝብ ጋር እጅ እና ጓንት የሆነ፣ የሚያስተዳድረውን ማኅበረሰብ ትኩሳት በቅርብ ለመረዳት በልዩ ልዩ አውዶች ላይ አሳታፊ መድረክን ማዘጋጀት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አንዱ መለኪያ ነው::ማንኛውም የመንግሥት እርምጃ ሕዝብን ባማከለ፣ ከታች ወደላይ በተሰናሰለ መልኩ መሆን ይኖርበታል::ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ሥልጣን ከመጡ አጭር ጊዜ ቢሆንም በየዘርፍ ያሉትን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎትን የሚያንጸባርቅ ፍትሐዊ እና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የማቆሙ ሐዲትን ለማፋጠን የሚኖራቸው ተነሳሽነት ከሁሉም በላይ ወሳኝ እንደሆነ ይታወቃል::የሚዲያ፣የሲቪክ እና የሌሎች የሙያ ማኅብራት የሚጎለብቱበትን ነጻ ምህዳር በመፍጠር የሽግግሩ ሒደቱ የተቃና እንዲሆን ማድረግ ይቻላል:: የመገናኛ ብዙኃን የመንግሥት አራተኛው ቅርንጫፍ ተብሎ የሚወሰድ እና ያልተማከለ አስተዳደርን በመግንባቱ ሒደት ላይ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ነው::እነዚህን ወሳኝ ክፍል ወደ ጎን ገፍቶ አንዲት ጋት ወደፊት ፈቀቅ ማለት አይቻልም::ስለዚህ አዲሱ የለውጥ አስተዳደር በዚህ ረገድ የሚሄድበት ርቀት ቀጣዩን የሀገሪቱን ዕጣፈንታ የሚወስን ነው::

መንግሥት የፓለቲካ ምሕዳር እንዲሰፋ ቁርጠኛነቱ ከሚለካባቸው መመዘኛዎች አንዱ በገዢው ፓርቲ ሳምባ የሚተነፍሱ፣ በቀበሌ እና በወረዳ እርከን የተደራጁ ማኅበራትን በማወያየት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ የሚሠራበትን የከዚህ ቀደሙን መናኛ አካሄድን መለስ ብሎ በማጤን ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲኖር ከምር የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ናቸው::እነዚህ በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል እንደ ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉትን ማኅበራትን ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው በራሳቸው እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ሥልጣን ላይ ካለው ገዢ ፓርቲ የሚጠበቅ ነው::

ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዴሞክራሲዊ አገዛዝ ባይተዋር ሆና እንደኖረች ይታወቃል::ይህንን በወጉ ያልጠና ሥርዓት የበለጠ ወደፊት ለማስቀጠል ከአዲሱ የለውጥ አስተዳደር ብዙ ይጠበቃል::በርግጥ በዚህ ወቅት ቅድሚያ የሚሰጠው ለሀገሪቱ ጸጥታ እና ደህንነት መሆኑ አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም::ከፀረ ለውጥ ኃይሎች ጋር የሚደረገው ግብግብ ገና እንዳላከተመ ፍንጮች ዕያየን ነው::ለአዲሱ አስተዳደር የእፎይታ ጊዜ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው::የመንግሥት ሙሉ አትክሮት ይህንን ዓላማ አንግቦ ወገቡ ያልጠናውን አስተዳደር በወጉ ማጠናከር ይኖርበታል::

ዕየታየ ያለውን የተስፋውን ጭላንጭል የበለጠ ለማፍካት ከመንግሥት የሚጠበቀው የቤት ሥራ ከመቼውም ጊዜ በላይ ፈታኝ እየሆነ ቢመጣም፣ ሊነጋጋ ሲል ይጨልማል እንዲሉ ሀገሪቱ ወደ አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ለመግባት አፋፉ ላይ ሆኖ የሚከሰት የተለመደ ኹነት ነው::መንግሥት በዚህ ሰዐት ጥንድ ዓላማዎች ላይ መትጋት ይጠበቅበታል::በአንድ ወገን ከቤተመንግሥት የተባረረው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አፋኝ ሥርዓት የተወው የኃይል ክፍተትን ለመሙላት በየማእዘኑ መባከን ሲሆን በሌላ ወገን ሀገሪቱ ዘላቂ እና አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማጽናት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ትኩረት መስጠት የግድ ነው::

ባጠቃላይ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለጎን ተሸካሚ ተደርገው የሚቆጠሩት ማኅበራት እና ሚዲያዎችን የሚያቀርብ አካሄድ ከወዲሁ ቢጀመር ፋይዳው የላቀ ይሆናል::እንደከዚህ ቀደሙ በይስሙላ ተሳትፎ(Mobilization)ምትክ መንግሥት ከአንጀት ግድ ያለው የውይይቱ መድረክ እየጎለበት መሄድ አለበት::


## ግዮን መጽሔት

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ደረጀ ይመር

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ተስፋዬ ሽብሩ
ሔማስ ታፈረ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 5ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 501
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም



ዮናታን ፍሰሀ (ዶ/ር)

# የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም መርገም

## እንደ መግቢያ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሥርዓት ውስጥ እንደ ምሶሶ የሚቆጠረው በመልካምድራዊ ገጽታ መሰረት ችምችም ብለው ለሰፈሩት የዘውግ ማኅበረሰቦች የግዛት ነፃነትን ማጎናጸፍ ነው:: የ1987ቱ ሕገ መንግሥትም ቢሆን ዋንኛው መርሁ የሀገሪቱን የአስተዳደር አዋቃቀር የዘውግ ማንነትን ታሳቢ ያደረገ የግዛት ነፃነትን በመተግበር እንደሆነ ይታወቃል:: ለዚህም ነው አብዛኛዎቹ በኢትዮጵያ የፌዴራል ሥርዓት ላይ ሂስ የሚሰነዝሩት የፖለቲካ ታዛቢዎች የ1987ቱን ሕገመንግሥት ተከትሎ ለዓይነ ሥጋ የበቃውን አስተዳደር የዘር ወይም የጎሳ ፌዴራሊዝም ብለው መበየንን የሚመርጡት::ይህ ለአፍሪቃም ሆነ ለኢትዮጵያ እንደ አዲስ የፖለቲካ ምዕራፍ የሚቆጠረው ተሞክሮ በውስጡ ብዙ ፀጉረ ልውጥ ባህሪያትን አቅፎ ይዟል:: የዘውግ ማንነት ከሁሉም የፖለቲካ ማንነት በላይ ቅድሚያ ተሰጥቶት በአንድ ወይም በሁለት ግዛት ላይ የበላይ እንዲሆን የይለፍ ፍቃድ የተሰጠበት ውሳኔ የመርገሙ ጥንስስ ነው:: በዚህም የተነሳ በዘውግ መስመር የሚሰባሰቡ ኃይሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጽኗቸው እየበረታ ለመሄድ ችሏል::

## በዘውግ አጥር የተበጃጁት ክልሎች

ኢትዮጵያ ከአፍሪቃ ሀገራት በተለየ የፌዴራላዊ ሥርዓትን ከዘውግ ማንነት ጋር በአንድ ጎጆ ጥላ ስር ያዋለች ሀገር ናት::የፌዴራል ሥርዓቱ የሕዝቦችን መልካምድራዊ ኩታገጠም አሰፋፈር ወደ ጎን በመግፋት የዘር ማንነት ላይ ብቻ ነው የተንጠላጠለው:: ለዚህም ዋነኛው መዳለደል ሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ባስ ሲልም እስከመገንጠል ነፃነትን የሚሰጠው የሕገመንግሥቱ አንቀጽ 39 ነው::

ከዚህም በተጨማሪ በአንቀጽ 46 መሰረት ከ80 በላይ የሆኑት የሀገሪቱ የዘውግ ማኅበረሰቦች በዘጠኝ ክልል እና በሁለት የከተማ አስተዳደር ሊካለሉ ችለዋል:: ሁሉም ክልሎች እንደ ስያሜያቸው የአንድ የዘውግ ማኅበረሰብ ርስት እንደሆኑ ተደንግጓል::ሌሎች በክልሎቹ ውስጥ የሚኖሩት ማኅበረሰቦች ዕጣፈንታቸው የሚወሰነው በርስትነት በተሰጠው ብሔር ችሮታ ይሆናል::በዚህም የተነሳ ሕገመንግሥቱ ፊት የነሳቸው ዘውጌዎች ራሳቸውን እንደ መጤ፣ ሰፋሪ ቆጥረው አንገታቸውን ደፍተው እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል:: ይህ ነጥብ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ትንሹን የሐረሪ ክልልን ዋቢ አድርገን ማንሳት እንችላለን፤ ሐረሪ ክልል ሕገ መንግሥት በርስትነት የሰጠው ለሕዳጣኑ ሐረሪ ዘውግ ነው::

በግዛቱ ውስጥ የሚኖሩት ሌሎች ማኅበረሰቦች ከሐረሪ ብሔር ጋር ሲነፃፀር ቁጥራቸው የላቀ ቢሆንም መብታቸውን የሚያስከብሩበት የውክልና ሥልጣን ያለው የፓለቲካ አስተዳደር ባለቤት መሆን አልቻሉም:: ምንም እንኳን ይህ ገሀድ እውነታ መሬት ላይ በግልጽ የሚታይ ቢሆንም ትንሹ ሐረሪ የፖለቲካውን መንበር በበላይነት ይዞ የሌሎች ብዙኃን ማኅበረሰብን እጣ ፈንታ እንዲወስን ሕገመንግሥቱ ኢፍትሓዊ በሆነ መልኩ ሥልጣን ለግሶታል::

የሀገሪቱን የግዛት አወቃቀር በጎሳ መስመር ብቻ መቀንበቡ አንድ ወጥ የሆነን የፖለቲካ ማኅበረሰብን ከመፍጠር ይልቅ በክልል አጥር የተካለሉ እና በጎሪጥ የሚተያዩ ብሔረሰቦችን ለዐይነ ሥጋ አብቅቷል:: አንድ ወጥ ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ የሚገነባባቸው የፌደራል ሥርዓቶች የሚቀለሱበት ዋንኛ መርህ መልካምድራዊ አቀማመጥን ወይም ኩታገጠምነትን ከግምት አስገብተው ነው:: በአንድ አካባቢ የሰፈሩትን የዘውግ ኅብረተሰቦች ባለቤት እና ደባል ብሎ ሳይከፍል ፍትሓዊ የሆነ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን እውን ያደርጋል:: ይህም ማለት አዲስ አበባ የአዲስ አበቤዎች፣ ድሬድዋ የድሬዎች፣ ሀዋሳ የሀዋሴዎች እንደ ማለት ነው::

በአንፃሩ ባለብዙኃ ብሔር ፌዴሬሽን የዜጎችን በታሪክ፣ በባህል፣ በጋብቻ የተጋመዱበትን እውነታን በመግፋት የደም ጥራትን ብቻ ከግምት ውስጥ በመወሰድ የግዛት አወቃቀርን ይከተላል:: ለአብነት በዚህ መርህ መሰረት ወለጋ በርስትነት የተሰጠው ለኦሮሞ ማኅበረሰብ ብቻ ነው:: በግዛቱ ውስጥ ከቅድመ አያቶቻቸው አንስቶ ከቀዬው አድባር ጋር ተላምደው የሚኖሩት ሌሎች ማኅበረሰቦች፣ የፖለቲካ ውክልና የሚያገኙበት ምንም ዓይነት ዕድል የላቸውም:: ዕጣ ፈንታቸው የሚወሰነው በአካባቢ ወይም በቀበሌ ሹማምንት ችሮታ ይሆናል::

## የተለየ ገጽታው

ሕገ መንግሥቱ የዘር ማንነትን ለግዛት ማዋቀሪያ እውቅና መስጠቱን ስንመለከት፣ ኢትዮጵያን አንድ አይነት ሀገራዊ ማንነትን ያዳበረ ሕዝብ ይኖርበታል የሚለውን ትርክት በአፍጢሙ እንደተከለው እንረዳለን:: ሰነዱ ኢትዮጵያን የጋራ ፖለቲካዊ ማንነት ያልዳበረባት የብዙ ሕዝቦች ሀገር እንደሆነች በቁሙ ይቀበላል:: በዚህም የተነሳ ኢሕአዴግ ከዚህ ቀደም ሀገሪቱ በታሪክ ካስተናገደቻቸው መንግሥታት ጋር ሲነጻጸር የተለየ መንገድን ተከትሏል ቢባል እውነታውን ማበል አይሆንም:: ፌዴራላዊው ሥርዓተ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ከአማርኛ ተናጋሪ ውጪ ለሆኑ ሕዝቦች ባሕላቸውን እና ቋንቋቸውን እንዲያበለጽጉ አንጻራዊ ነጻነት ለግሶዋቸዋል:: ከዚህ በተጨማሪ ክልላዊ ውክልና ያላቸው የፖለቲካ መሪዎች ከየዘውግ ማኅበረሰብ ብቅ ብቅ እንዲሉ እና የክልላቸውን የሥራ ቋንቋን ለመወሰን የሚያስችላቸውን ነጻነት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 5 መሠረት እድል ሰጥቷቸዋል::

## የፌደራል ሥርዓቱ ቀይ መብራት

የፌደራል ሥርዓቱ የሀገሪቱን አንድነት በእጅጉ አናግቷል:: በዘር መስመር የሚደራጁ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሆኑ ማኅበራት ከመቸውም ጊዜ በላይ ተበራክተዋል:: በ2007 ዓ.ም የምርጫ ውድድር ላይ የምርጫ ቦርድ ከመዘገባቸው 79 ፓርቲዎች መካከል 65 ዘርን መሰረት ያደረጉ ናቸው:: በሐሳብ መሰባሰብ ብርቅ እየሆነ መጥቷል::

## መደምደሚያ

የታሪክ፣ የባህል፣ ሥነልቦና ብሎም የመልካምድራዊ ኩታገጠምነትን ከግምት ሳያስገባ በተግባር የዋለው ፌደራላዊው ሥርዓት ብዙ ፖለቲካዊ ምስቅልቅሎችን ወልዷል::በዚህም የተነሳ በአራቱም ማእዘን ያለው የሀገራችን ሕዝብ የመርገሙ ሰለባ ሊሆን ችሏል:: ስለዚህ ፌዴራላዊ ሥርዓቱ እነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎችን ወደ ጎን ሳይገፋ የሚካለልበት አማራጭ መኖር አለበት:: በተጨማሪ ትልልቅ የሀገሪቱን ዘውግ የግድ በአንድ የክልል ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ ማካተት መፍትሄ አይሆንም:: የግዛት አንድነታቸውን በማይናጋ መልኩ በተለያየ አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ እንዲታቀፍ በማድረግ የጎንዮሹን ጉዳት መቀነስ ይቻላል::

---

*ማስታወሻ:- በኬፕታውን ዩኒቨርስቲ ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ዮናታን ፍስሐ “The original sin of federalism” በሚል ርዕስ በእንግሊዘኛ ያቀረቡትን ዘለግ ያለ ትንታኔ ለአንባቢያን በሚመች መልኩ ተቀንጭቦ የቀረበ::*

# ፍሬ አልባው ኦነግና የኦዴፓ መቋጫ ያጣ ውዝግብ

ተስፋዬ ሽብሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ ከሰሞኑ ከመምህራን ጋር ባደረጉት ረጅም ሰዐት የፊጀ ውይይት በአገሪቱ እየተካሄደ ያለውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንስተው በስፋት መዳሰሳቸው ይታወቃል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትኩረት ሰጥተው ከተናገሩባቸው ጉዳዮች መካከል በዋንኝነት የሚጠቀሰው በምዕራብ ወለጋ ኦነግ እየፈጠረ ስላለው ሕዝብን የመበጥበጥና ሰላምን የማደፍረስ እንቅስቃሴ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ "ሃያ ዓመት ሠላሣ ዓመት የታገሉ፤ መታገል ብቻ አይደለም፤ የኢትዮጵያን ምድር መርገጥ ያልቻሉ ሰዎችን ይብቃችሁ ብለን ሕግ ቀይረን ባሉበት አናግረን ለምነን አምጥተን ልንወጋ አይገባም:: ትክክል አይደለም" በማለት ወደ ሀገር ቤት እንገቡ ያደረጉበትን ምክንያት ዘርዝረው ገልጸዋል:: ኤርትራ የነበረው ውጊያ፤ ሶማሌያ የነበረው ውጊያ፤ ወለጋ እንዲመጣ አይደለም የጠራናቸው ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐብይ አሁን በወለጋ ችግር የሚያደርሱት አካላት ኤርትራ ውስጥ ይህንን ሁሉ ዓመት ተቀመጡ እንጂ ፍሬ ማፍራት እንዳልቻሉ ተናግረዋል::

ጠ/ሚኒስትር ዐብይ ኦነግ በክልሉ እየፈፀመ ካለው አሳፋሪ ተግባር በፍጥነት መውጣት እንዳለበት አስታውሰው ከመንግሥት ጋር አለመግባባት ሲፈጠር ዘሎ ሀገርን ለማጥፋት የሚሰራ ከሆነ አልገባንም ማለት ነው ብለዋል:: " ወለጋ ላይ በፍፁም ክላሽ አያስፈልግም" ያሉት ጠ/ሚኒስትሩ የወለጋ ሕዝብ በከፍተኛ ደረጃ የመሰረተ ልማት ችግር እንዳለበትና ወለጋ የሚያምር፤ ነገር ግን መንግሥት ያለየው፤ መልማት ሲችል ያለማ አገር ነው ብለዋል:: ወለጋ ጭራሽ ጥይት መስማት አያስፈልገውም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ "የጭንቅላት ክላሽ እንጂ የራሺያ ክላሽ" እንደማያስፈልግ፣ ሀገርን እያመሱ ላሉት አካላት ግልጽ መልዕክት አስተላልፈዋል::

"ተፎካካሪ ፓርቲ ነኝ የሚል አካል ክላሹን አስቀምጦ የሀሳብ ክላሽ ታጥቆ መታገል ይኖርበታል" ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐብይ ከዚያ በፊት በሶስትና በአምስት ወራት መንግሥት እሆናለሁ የሚለው ግን የማይሰራ ቅዠት እንደሆነ አስረግጠው ተናግረዋል:: አሁን ያለው ጩኸት ይረግባል ያሉት ጠ/ሚኒስትር ዐብይ "ሆያ ሆዬ ለቡሄ ይሰራል እንጂ አይሻገርም፤ አገር ከሆያ ሆዬ በላይ" መሆኗን አስገንዝበዋል::

ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በመቀጠል ወቅታዊ የሀገሪቱ ጉዳዮች ላይ መግለጫ የሰጡት የመከላከያ ሚኒስቴር ኤታማጆር ሹም ጀኔራል ብርሀኑ ጁላ ናቸው :: የመከላከያ ሚኒስቴርን የ2011 ዓ.ም ግማሽ ዓመት የሥራ ክንውን ሪፖርት ለማቅረብ ከመከላከያ ሚኒስትሯ አይሻ መሐመድ (ኢንጅነር) ጋር በመሆን ታህሳስ 30 ቀን 2011 ዓ.ም በምክር ቤቱ የተገኙት ጄነራል ብርሃኑ የታጠቁ ኃይሎችን ትጥቅ በማስፈታት ረገድ መከላከያ ሰራዊቱ እያደረገ ያለውን ተግባር ዘርዝረዋል::

ኤታማጆር ሹሙ ቅድሚያ ትኩረት የሰጡት በምዕራብ ወለጋ ስለከተሰተው ችግር ነው:: በምዕራብ ወለጋ የተፈጠረውን ኢሰብኣዊ ድርጊት እንደተፈፀመ የተናገሩት ጄነራል ብርሃኑ "ለአንድ ሕዝብ ነፃነት የሚታገል ኃይል፣ በሚታገልለት ሕዝብ ላይ ጭካኔ የተሞላባት ዘግናኝ በደል እንዴት ሊፈፅም ይችላል?" በማለት ጥያቄ በማንሳት ነበር ንግግራቸውን የቀጠሉት:: ለረጅም ዓመታት በውትድርና ማገልገላቸውን ገልፀው ፣በወለጋ ከተፈፀመው በስተቀር መሰል ጭካኔ አይተው እንደማያውቁ አስታውቀዋል::

ባል ታስሮ ሚስት የምትደፈርበት ፣ሕዝብ ተጨንቆ በጉድጓድ የተደበቀበት፣ በርካታ ሰዎች ታግተው የተገኙበት ፣የመንግሥት ተሽከርካሪና የጦር መሳሪያ በሙሉ የተዘረፈበት እንደነበር ገልፀዋል:: የመከላከያ ሠራዊቱ ወደ ወለጋ ሲገባ የተገኘው ጉድ ዘግናኝ መሆኑን ያስታወሱት ጄነራሉ በምዕራብ ወለጋ የተፈፀመውን ጭካኔ በቅርቡ በቪዲዮ ምስል ጭምር ታዩታላችሁ በማለት የተፈፀመውን የጭካኔ ድርጊት ዘርዝረዋል::

በወለጋ የተከሰተውን ቀውስ የማስተካከል ሥራ የክልሉ የፀጥታ ኃይል እንጂ የመከላከያ ሰራዊቱ መሆን እንዳልነበረበት ፤ ችግሩን የፈጠሩት በአካባቢው የተሰማሩ ታጣቂዎች በሰላማዊ መንገድ ሊታገሉ የመጡ ናቸው ፣እንዳትነኳቸው በመባሉ የክልሉ የፀጥታ ኃይል ሽባ ሆኖ መገኘቱን ተናግረዋል:: የክልሉ የፀጥታ ኃይል ኃላፊነቱን በወቅቱ እንደወጣ ‹‹እንዳትነኳቸው›› የሚለውን ትዕዛዝ ማን እንዳስተላለፈ ኤታማጆር ሹሙ ሳይገልፁት አልፈዋል:: ከባኮ ጀምሮ መንቀሳቀስ የማይቻል እንደነበር የገለፁት ጄነራሉ፣ ሠራዊቱ ከገባ በኋላ የትራንስፖርት እንቅስቃሴ መጀመሩን ፣ሸሽተው ወደ አዲስ አበባ የገቡ ባለሀብቶችም ወደ አካባቢው በመመለስ ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል::

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሰሞኑን ባወጣው መግለጫ ኦነግ ከመንግሥት ጋር የፈፀመውን ስምምነት ሙሉ በሙሉ አለመተግበሩን በመጥቀስ የኦሮሞን ሕዝብ ሊሰብሩ የሚፈልጉ ኃይሎች ፍላጎትን ተሸክሞ ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ የኦሮሚያ ክልል ሰላም እየደፈረሰ መሆኑንም መግለጫው ይጠቁማል::

የኦሮሞ ሕዝብ ለውጡን ለማስቀጠል በጋራ እየተንቀሳቀሰ ባለበት በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ ሕዝብ ውስጥ በመንቀሳቀስ አደጋ ማድረስ፤ ለሕዝቡ የቆመን የፀጥታ ኃይል መግደል፤ የጦር መሳሪያ በመዝረፍ ሁከት መፍጠር እንዲሁም ጉዳቱን እያወቁ እያዩና እየሰሙ ኦሮሚያን የጦርነት አውድማ ለማድረግ አቅደው እንደሚሰሩ ኃይሎች "ኦሮሞ አገር መምራት አይችልም፤ የሽግግር መንግሥት ነው የሚያስፈልገው" በማለት ጭምር እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ በመግለጫው ተዘርዝሯል::

ኦዴፓ መግለጫውን ባወጣ ማግስት ታህሳስ 29 ቀን 2011 ዓ.ም ኦነግ መግለጫ አውጥቷል:: ኦነግ ጥሪውን ያቀረበው የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት፤ ኦነግ የክልሉን ሕዝብ ሰላም ከማወክ እንዲታቀብ የሚያሳስብ መግለጫ ኦዴፓ መስጠቱን ተከትሎ ነው::

ኦነግ በመግለጫው የኦሮሞ ሕዝብ የነጻነት ትግልና ሕዝባችን በተለይም ቄሮ በከፈለው ውድ መስዋዕትነት ኢሕአዴግ ተገዶ መልስ እንዲሰጥ በመደረጉ ላለፉት ስምንት ወራት ለሁሉም የሚጠቅም የሰላም መስኮት ዕድል የተከፈተ ወይም የተፈጠረ መስሎ ነበር:: ኦነግ መታደሱንና ለሰላም ዝግጁነቱን ከተናገረው የኢሕአዴግ መንግሥት ጋር በሰላም አብሮ ለመስራት ከስምምነት መድረሱን ኦነግ በመግለጫው አስታውሶ፣ አብሮ ለመስራት በሚያስችል ሥርዓት ውስጥ የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት በመወሰን በኢትዮጵያ መንግሥትና በኦነግ መካከል የነበረውን ጦርነት ለማቆም በጋራ ውሳኔ መሠረት አገር ቤት እንደገባ ገልጿል፡

የመንግሥት ከፍተኛ አመራሮች አባላት ሳይቀሩ በኦነግና በኦሮሞ ነፃነት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻና ፕሮፓጋንዳዎች እያካሄዱ መሆናቸውንም ይጠቅሳል ኦነግ በመግለጫው:: ጽህፈት ቤቶቹን ከፍቶ በአግባቡ እንዳይንቀሳቀስና እንዳይሰራ፤ ለማደናቀፍ፤ ለመገድብ ደባዎች እየተፈፀመበት እንደሆነ አትቷል:: ኦነግ በመግለጫው መፍትሄ የሚለውን ሀሳብም አቅርቧል:: ሶስተኛ ወገን በሚገኝበት ስምምነቱ እንደ አዲስ ውይይት ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስቧል::

ጀኔራል ብርሃኑ ጁላ ግን ለተወካዮች ምክርቤት ባቀረቡት ሪፖርት " ግንባሩ በመጀመሪያ ሕዝቡ በሬ ፤ በግና ዶሮ አርዶ ተቀበላቸው :: ደረጃ በደረጃ ሕዝቡን ወደ መዝርፍ ገቡ:: በመቀጠል በሬ አርዶ በተቀበላቸው ሕዝብ ላይ አሰቃቂ ድርጊት ፈጸሙ" በማለት የኦነግን አሰቃቂ ድርጊት በመዘርዘር አስረድተዋል::



መስፍን ጌታቸው

# ለእርቅ ለፍቅር ዘመን ከቶ አይመሸም

እንደ እድል  ሳይሆን እንደ ሥራ ምግባሩ አሳምር ብሎ በሕዝብ መታመን ብርቅ የሆነበት፣ ነገር ግን "ለሕዝብ መብትና ነፃነት ቆሜያለሁ፣ ከኔ በላይ ለሕዝብ ጥቅም የተሰዋ ወደፊትም ለመሰዋት ቁርጠኛ የሆነ ድርጅት በሻማ ቀርቶ በፓውዛ ተፈልጎ አይገኝም" በማለት፣ መደስኮር የማይሰለቸው ራሱን ከእውነት ጋር እስከ መጨረሻው ያፋታ ድርጅት ቢኖር ሕወሓት መራሹ ኢሕአዴግ ይመስለኛል::

መንግሥት ተሁኖ የአንዲት ታላቅ ሀገርን የመሪነት ሥልጣን ከተቆጣጠሩ በኋላ ራስን ማለቂያ በሌለው ሸፍጥና ውሸት ማጋነን ፣እንኳን ከመሪነት በጣም ተራ ከሆነ የተመሪነት ስብዕና የሚጠበቅ አይደለም::

እውነቱ ይህ ቢሆንም አገራችን ግን ለረዥም ዓመታት በዚህ እጅግ በወረደ ሥነልቦና ነበር ስትመራ የኖረችው::

የሕወሓት ኢሕአዴግን አልቦ ግብረ ገብነት ማሳየት የሚችሉ ማስረጃዎች ማቅረብ ካስፈለገ አንድ አይደለም አንድ ሺህ አንድ ማስረጃ መጥቀስ ይቻላል::

የሩቁን በመተው የትግራይ ሕዝብ ክፉኛ በተራበበት ወቅት ከለጋሽ አገሮች ለሕዝቡ ለማዳረስ የተሰጣቸውን የእርዳታ እህል ፣ገቢያ አውጥተው መቸብቸባቸውንና ከእነርሱ በተቃራኒ የቆሙ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ወንድም እህቶቻቸውን ስብሰባ ከጠሩ በኋላ በአንድ ሌሊት እንዳይሆኑ አድርገው የፈፀሙትን ክህደት፣ ትተን ከመንግሥትነት በኋላ የተፈጠረውን ሸፍጥ በግርድፉ ለመመልከት ብንሞክር እንኳን ከብዙ መራር ሐቆች ጋር ፊት ለፊት መላተማችን አይቀርም::

## ሕገመንግሥት እና ክልል

በሕግመንግሥት ማርቀቁ ወቅት ፌዴራል ሥርዓቱ፣ ቋንቋና ብሔርን መሰረት አድርጎ ይቋቋም የሚለው ሐሳብ ገገር እየሆነ ሲመጣ ፣ይሄ ዓይነቱ አከላለል የአገር አንድነትን ያናጋል፣ ብሔራዊ ስሜትን ያጠፋል፣ በሚል ሐሳብ ሥጋታቸውን ተጨባጭ በሆነ ማስረጃ በማስደገፍ ደጋግመው ቢያቀርቡም፣ ከሕወሓት መራሹ መንግሥት የተሰጠው መልስ ግን የሚያሸማቅቅ ነበር::

ታዲያ በወቅቱ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም ሆነ ከሌሎች አጋሮቻቸው አንደበት የማትጠፋ ተደጋግማ የምትነገር መከራከሪያ ነበረች::

መከራከሪዋ ‹‹እስካሁን ድረስ የነበረው አንድነት በሕዝቦች ፍላጎት ላይ የቆመ ሳይሆን በግድ የተጫነ ነው:: አሁን ግን ሕግ- መንግሥትን ተከትለው፣ ቋንቋና ብሔርን መሰረት አድርገው፣ የሚቋቋሙት ክልሎች ፣ሕዝቡ በማንነቱ ኮርቶ፣ በቋንቋው እየተናገረ የሚፈጥራትን አንዲት ሉአላዊነቷ የተከበረ፣ አንድነቷ እስካሁን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የጠነከረን ታላቅ ሀገር እውን ለማድረግ ይረዳል" የምትል ነበረች::

ይህ አባባል ግን ሕዝብን በሚያማልሉ ጣፋጭ ቃላት ተሞልቶ የቀረበ ውሸት እንጂ የተባለውን ዓይነት አገራዊ አንድነት ማምጣት የሚችል እውነት አልነበረም::

እናም ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል በሚል መርህ ይህ አስተሳሰብ ከጠቅላዩ ጀምሮ በሁሉም ባለሥልጣኖች አንደበት ተደጋግሞ ተደሰኮረ፤በሁሉም የገዢው ፓርቲ ልሳን በሆኑ ሚዲያዎች እንክንደነቁር ድረስ ተለፈፈ:: ውሸት የመንግሥት ሥራ ቋንቋ ሆነ:: አየሩ በውሸት መአዛ ዳር እስከ ዳር ታጠነ:: ይህን የታቀወሙ አካላት በሙሉ በጅምላ "ፀረ ሕዝብ" ተብለው ተወነጀሉ ፣ታሰሩ፣ ተሰደዱ፤ ገሚሶቹ ለከፋ ስቃይና መከራ ተዳረጉ፤ የተቀሩትም በግፍ ተገደሉ::

ሐቁ የታሳሪዎችና የተሰዳጆቹ ሆነ:: ሕግመንግሥትና በእርሱ አማካኝነት ተግባራዊ የተደረገው የክልሎች አከላለል ሕዝቡን በጠላትነት በማጋጨት የሥልጣን እድሜን በማራዘም አገርና ሕዝብን ያለ ርህራሄ በመጋት አደህይቶ የሚያስቀር እንጂ የተባለውን ታይቶ የማይታወቅ አገራዊ አንድነት ማምጣጥ የሚችል አልነበረም::

በዚህም ህሊና ካለው መሪና ድርጅት የማይጠበቁ በርካታ የጥላቻ መርዞች ያለማቋረጥ እንዲዘሩ በማድረግ ለቁጥር የሚታክት የሰው ሕይወት ተቀጥፏል:: በቢሊዮን የሚገመት ንብረት ወድሞ ሕዝብ ተፈናቅሎ ተሰዷል:: ኢትዮጵያችን አሁን እንደምናየው ፍፁም ለዜጎቿ የማትመች ብቻ ሳትሆን ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ መስራት ብርቅ የሆነባት አገር ለመሆን በቅታለች::

## የኢትዮኤርትራ ጦርነት

ከ1983ቱ ድል ማግስት የሕወሓትና የኢሕአዴግ ሊቀ መንበር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ምን ሰይጣን እንዳሳሳታቸው ባይታወቅም "ከእንግዲህ ከኤርትራ በኩል አንድም የጥይት ድምጽ አይሰማም" በማለት ደርግና የአጼው ሥርዓት የኤርትራን ጉዳይ በተመለከተ  ሲያራምዱት የነበረውን ፖሊሲ በመኮነን ፣እሳቸው የሚመሩት ድርጅት ግን አንድም የጥይት ድምጽ የማይስማበት፣ ዘላለማዊ የሆነ መፍትሄ እንዳመጡ ፣በፍፁም ኩራትና ልበ ሙልነት ነግረውን ነበር::

ብዙም ሳይቆይ ግን ትዕቢታቸው ገደል ገባ:: ኩራታቸው እና ልበ ሙሉነታቸውን ኩምሽሽ በሚያደርግ ሁኔታ ብዙዎች ‹‹ እንኳን ሰይፍ መዞ  ለመተላለቅ ቀርቶ ለመለስተኛ  የቃላት መራኮት የሚያበቃ ምክንያት የሌለው ያሉት የጅሎች ጦርነት" ተለኩሶ ከሰባ ሺህ በላይ የሆኑ ወጣቶች ያለ አግባብ ተሰው:: የአገር ሀብትና ንብረት ወደመ:: ሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦችም ምሽግ ቆፍረው  በጠላትነት ዕየተያዩ መኖር ጀመሩ::

ምናልባት ይሄን በእብሪት  የተሞላ ከንቱ ትንቢት ተራ  የአፍ ወለምታ ነው ብሎ ማለፍ ይቻል ይሆናል:: ማለፍ የሚከብደው ግን ከጦርነቱ በኋላ አልጀርስ ላይ የተፈረመውን ስምምነት መሰረት በማድረግ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ የተናፈሰው የውሸት ▶

> በወቅቱ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ስዩም መስፍን በኩራት ደረታቸውን ነፍተው በመውጣት ሕዝቡን እንኳን ደስ አለህ የአገርን ሉአላዊነት ለማስከበር በጀግንነት የተዋደቀክላት ባድመ በመጨረሻ ላንተ ተወስናልሀለች በሚል ታላቅ የምሥራች ከዳር እስከ ዳር በደስታ ጮቤ አስረገጡት

▶ድል አድራጊነት ነው::

በወቅቱ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ስዩም መስፍን በኩራት ደረታቸውን ነፍተው በመውጣት ሕዝቡን እንኳን ደስ አለህ የአገርን ሉአላዊነት ለማስከበር በጀግንነት የተዋደቀክላት ባድመ በመጨረሻ ላንተ ተወስናልሀለች በሚል ታላቅ የምሥራች ከዳር እስከ ዳር በደስታ ጮቤ አስረገጡት::

ደስታ በአገሩ ሰማይ ስር ከጥግ እስከ ጥግ ናኘ:: ጉሮ ወሸባዬ ተዘፈነ:: እልልታና ፉከራው ቀለጠ:: ከተሞች በሰላማዊ ሰልፎች ደማቁ:: የሚዲያ ተቋማት ድላችንና ጀግንነታችንን እየተቀባበሉ ከፍ አድርገው ለፈፉ::

የምሥራቹ ግን እውነት አልነበረም:: "ሉአላዊ ክብራችን ተደፍሯል " በሚል ጦር ያዘመትንባት፣ የእዚያ ሁሉ ወጣት ደም የፈሰሰባት ፣ ከግምት በላይ የሀገር ሀብት የወደመባት ባድመ ፣የእኛ ሳትሆን የኤርትራዊያን መሆኗን ነበር ፍርድ ቤቱ የወሰነው::

የተሰማው የድል ዜና ውሸት ነበር:: ያ ሁሉ እሳት፣ ያ ሁሉ ፉከራ፣ ያ ሁሉ ቀረርቶ፣ ውሸት ነበር:: በዚህም የተከፈለው እጅግ በጣም ውድ የሆነ መስዋዕትነት ከንቱ ሆኖ ቀረ::በሌላ አገር ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነቱ ትልቅ ውሸትና የአገር ክህደት ሥልጣን ማስለቀቅ ብቻ ሳይሆን በወንጀልም ያስጠይቅ ነበር:: የኛ የውሸት መሐንዲሶች ግን ይቅርታ እንዲጠይቁን የሚያበቃ የሞራል ልዕልና እንኳን አልነበራቸውም:: ይልቁንም ያለ ይግባኝ ሊቀበሉት ተስማምተው የፈረሙትን ውል በመካድ "ውሳኔውን በመርህ ደረጃ ተቀብለነዋል:: ተግባራዊ ለማድረግ ግን መደራደር እንፈልጋለን" የሚል ውሳኔ በፓርላማ በማስወሰን አገራችንን ለረዥም ዓመታት ለፈረመችው ውል የማትታመን ቃል አባይና ከሀዲ በሚል ስትከሰስ እንድትኖር አደረጓት::

## ምርጫ ዘጠና ሰባት

ሕወሓት መራሹ የኢሕአዴግ መንግሥት ቀደም ሲል የተቃዋሚዎችን ድራሽ በማጥፋት በፈፀመው እኩይ ድርጊትና በወቅቱ እዚም እዚያም ይታዩ በነበሩ መጠነኛ ድጋፎች የተነሳ የ1997 ዓ.ም ቱን ምርጫ እንደሚያሸጋግር በጣም እርግጠኛ ነበርን::

በርግጥም አንድም ጠንካራ ተቋማዊ ፓርቲ ባልነበራት ሀገር በፖለቲካ ተስፋ ቆርጦ ራሱን ባራቀበት፣ አብዛኞቹ የተማሩ ሰዎች አገር ጥለው በተሰደዱበት ወቅት፣ እንዲህ አይነት እርግጠኛነት ቢሰማው ብዙ ላይገርም ይቻል ይሆናል::

እናም ስለ አሸናፊነት መቶ በመቶ እርግጠኛ የሆነው ሕወሓት ኢሕአዴግ ምርጫውን መቶ በመቶ ነጻና ገለልተኛ አደርጋለሁ በማለት ቆርጦ ተነሳ::

ሕወሓት ይህን ያደረገው ለማንም ብሎ አልነበረም::ቀደም ሲል በፈፀማቸው ተደጋጋሚ ማጭበርበሮች ተስፋ ቆርጦ ጀርባውን የሰጠውን ሕዝብ ቀልብ ለመግዛት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ መቼም ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ሊሆን አይችልም›› በሚል ፊት የነሱትን መንግሥትና ዓለም አቀፍ ተቋማት በማግለል ዴሞክራሲያዊ መንግሥትነቱን ማስመስከር ነበር::

እኛም ሚዲያዎች በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ ተፈቱን:: ሲቪል ማኅበራት እንደልባቸው ሕዝቡ ጋር በማድረስ እንዲያስተምሩ መብት ተሰጣቸው:: የምርጫ ክርክሮች በተከታታይ ለሕዝብ እንዲታዩ ተደረገ::

ያኔ ሕወሓት መራሹ ኢሕአዴግ ብርክ ያዘው:: ቅንጅትና ኅብረት የተሰኙ ድርጅቶች በየመድረኩ የገዢውን መንግሥት ተወካዮች በዝረራ በማሸነፍ እርቃኑን አስቀሩት:: የሕዝቡ ተነሳሽነት በአስደንጋጭ ሁኔታ ተመነደገ:: የኢሕአዴግ መንደር በጭንቀትና በፍርሃት ተወረረ፤ የተቃዋሚው መንደርና የሕዝቡ መንፈስ በአንጻሩ በድል አድራጊነት ተሞላ::

ሚያዚያ 29 የተደረገው የድጋፍ ሰልፍ የኢሕአዴግ መንደርን በእፎይታ አስተንፍሶ በአሸናፊነት ስሜት ጮቤ አስረገጠ:: ይሄን የሕዝብ ማዕበል ይዘን ዛሬ ቀርቶ መቼም ቢሆን ማጭበርበር ሳያስፈልገን እናሸንፋለን የሚል የድል ዜና አስለፈፈ::

ይህ ደስታ ግን ከአንድ ቀን የዘለለ እድሜ አልነበረውም:: በሀገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሕዝባዊ ማዕበል በማግስቱ ተረታ::

ይሄ ማዕበል በሳምንቱ ከሌሊት ጀምሮ የአገሪቱን የምርጫ ጣቢያዎች በጠቅላላ በአስገራሚ ሁኔታ አጥለቀለቀ:: ድምጽ አሰጣጡም በአብዛኛው ቦታ በሕወሓት ኢሕአዴግ አስደንጋጭ ሽንፈት ተጠናቀቀ::ጠቅላይ ሚኒስትሩ ምሽቱን በቴሌቪዥን ቀርበው የድርጅታቸውን ሽንፈት ዐይናቸው ውስጥ በግልጽ እየተነበበ አሸናፊነታቸውን አወጁ::

ሌሊቱን ካድሬዎቻቸው በየምርጫ ጣቢያው በመሄድ በግድም ሆነ በውድ ኮሮጆ ለመቀማት ግዳጁ ተሰማሩ:: በጣም አሳፋሪ በሆነ ሁኔታም የግምባሩ ታላላቅ ካድሬዎች ሳይቀሩ በአደባባይ ድምጽ ሲዘርፉ ታዩ::

ከዛም ቀደም ሲል ጀምሮ የክፉ ቀን ደራሽ ይሆን ዘንድ ታስቦ በተቋቋመው ምርጫ ቦርድ አማካኝነት የሕወሓት ኢሕአዴግ አሸናፊነት ታወጀ:: ወዲያው ተቃውሞ በረታ፤ ጩኸት በረከተ፤ ዓለም አቀፍ ታዛቢዎች ክብረ ነክ በሆነ ሁኔታ በግልጽ ተወረፉ፤ እስርና ግድያ የእለት ተዕለት ተግባር ሆነ::

በጣም የሚያሳዝነው ግን የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መንግሥትና ፓርቲ አርፎ የተቀመጠውን ሕዝብ በግድ ቀስቅሶ ለምርጫ ካስወጣ በኋላ በገዛ ቅጥፈቱ ሳይፀፀት ድምፄ ይከበርልኝ በማለት አደባባይ የወጣውን ምስኪን ሕዝብ ግምባር ግምባሩን በጥይት አስደብድቦ ሲጥል ቅንጣት ያህል እንኳን አለማፈሩ ነው::

ውሸትና ቅጥፈቱ በዚህ ብቻ አያበቁም:: ከዚህም አልፎ ብዙ ርቀት ይጓዛል:: ሕወሓት ኢሕአዴግ የእውነትን አቅም ክፉኛ አመንምኖ ውሸትና ክህደትን ለማፈርጠም ሕግ ከማውጣጥ ጀምሮ ትላልቅ በጀቶች በመመደብ ግዙፍ የሆኑና ስማቸውን የማይመጥኑ የውሸት ተቋማትን እስከመመስረት ይዘልቃል:: ቀደም ሲል የተቀዋቀዋሙ ተቋማትንም በውሸት አጥምቆ ክፉኛ ያረክሳል::

ለዚህ እውነት ተጨባጭ ማሳያ መጥቀስ የሚያስፈልግ ከሆነ ፀረ ሙስና ተብሎ ከተቋቋመው ተቋም ጀምሮ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ሰብኣዊ መብት ኮሚሽን ምርጫ ቦርድ ወዘተ የተባሉትን ተቋማት መጥቀሱ ይበቃል::

እንግዲህ ያለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት የክህደትና የውድቀት ዘመን ለማሳየት እጅግ በጣም ከሆኑት ማሳያዎች መሀክል ከላይ በጥቂቱ የቀረቡት ማሳያዎች በቂ ይመስሉኛል::

ይህ የጥፋት ዘመን አገራችንን መቼም ሊተካ የማይችል እጅግ በጣም ውድ የሆነ ዋጋ አስከፍሎታል:: ህሊናውን በክህደት ያሳወረን መስረቅ የሚያሳፍረው፣ ወዳጁን በሐሰት በመወንጀሉ የሚኮራ፣ ወንድሙን በግፍ በመግደሉ ጀግንነት የሚሰማው አልቦ ግብረገብ የሆነ ትውልድ በመፍጠር አንድ ወርቃማ የሆነ የእድገትና የብልፅግና ዘመን ቅርጥፍ አርጎ አውድሟል::

ምንም እንኳን የዚህ ሁሉ ክፋት ተጠያቂ በአራት ድርጅቶች ኅብረት የተቋቋመው ኢሕአዴግ የተባለው ግምባር ቢሆንም የአምበሳውን ድርሻ በመወጣት ዋነኛ ባለቤት የሚሆነው ግን ሕወሓት መሆኑ ማንም ሊክደው የማይችለው እውነት ነው::ይህን ሐቅ ሕወሓት እራሱ በአደባባይ ካልሆነ በስተቀር ውስጥ ውስጡን የሚክደው አይመስለኝም:: እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ አሰተኔ ገፀ ባህሪ ተላብሰው የራሳቸውን ድርጅት እንኳን እንደፈለጉ የማጥራት ስልጣን ሳይኖራቸው የሕወሐት አማርኛ ተናጋሪ፣ ኦሮምኛ ተናጋሪ፣ ሲዳምኛ ተናጋሪ ክንፎች በመሆን በተላላኪነት ሲያጨበጭቡ ነው የኖሩት::

እዚህ ጋ "ለምን " የሚል ጥያቄ ማንሳት ክፉኛ ያስገምታል:: አንደኛ የነዚህ ድርጅቶች አባላት በአብዛኛው የሕወሓት ምርኮኛ እና ታማኝ እንዲሆኑ ተደርገው ነው የተፈጠሩት:: ሲቀጥል ቀና ለማለት ሲሞክሩ "ይቺ ባቄላ....." በሚል ይኮረኩማሉ:: አይ ካሉ ደግሞ ወይ ካርድ ይመዘዝባቸዋል ወይም ደግሞ ፈርጣማ በሆነው የማፍያ ጡንቻ ይደቆሳሉ::

በአሁኑ ወቅት ሕዝቡ የሕወሓትን ተደጋጋሚ ውትወታ አምኖ ለመቀበል የሚያስችል አቅም የለውም:: ምናልባት ሕዝብን አንዴም ፣ሁለቴም፣ ሦስቴም፣ አራቴም፤ ልትዋሸውና ልትክደው ትችል ይሆናል፤ ከዛ በኋላ ግን አምኖ ተቀብሎኛል በሚል ራስህን ነው የምታፅናና ፣ የምታታልለው:: የሆነውም ይህው ነው:: ደሞስ መንግሥት በከባድ ወንጀል ጠርጥሮ በሕጋዊ መንገድ የእስር ማዘዣ ያወጣባቸውን ወገኖች ደብቆ አሳልፌ አልሰጥም ከማለት የበለጠ ምን ዓይነት ሕግ - መንግሥታዊ ጥሰት ሊኖር ይችላል::

ስለዚህ የሕወሓት መሪዎች በታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ራሳቸውን ከእውነት ጋር አሳታርቀው፣ መንፈሳቸውን በንስሃ ፀበል በማንፃት ፣ከተደበቁበት ወጥተው ፣እውነቱን ፊት ለፊት በመጋፈጥ፣ ለፍርድ መቅረብ ያለበት ካለ አሳልፈው በመስጠት፣ ከሌላው ሕዝብ ጋር በይቅርታ በምህረት ሰላም አውርደው፣ አገሩንም ሰውንም በመካስ ፣ታሪክ ሊሰሩ ነው የሚገባቸው::

ለእርቅና ለሰላም መቼም ቢሆን አይረፍድም፤ የፍቅር መንገድ ሁሌም ቢሆን ቀና ነች:: ለክፋት ነው እንጂ ለፍቅርና ለይቅርታ የሚመሽ ዘመን አይኖርም::

ደሞም በሚሞት ሰውነት ነፍስን ሙት ለሆነ የጥላቻ መንፈስ አስገብሮ ማለቂያ የሌለው ጥፋትና እልቂትን ከመጥራት ይልቅ ህያው የሆነውን መልክታዊ ፍቅር ተላብሶ፣ ሰላምና መተሳሰብን አንግሶ ፣አገር የሚያጠግብ ወጋገን የሚያስከፋ ታሪክ መስራት ፣በጣም እጅግ በጣም ያስከብራል:: መንፈስን በእፎይታ በማሳረፍ እና በማደስ ስምንም ከመቃብር በላይ ከፍ አድርጎ ያስጠራል::

እናም "ሰይፍ የሚያነሱ በሰይፍ ይጠፋሉ" የሚለውን የመጽሐፍ ቃል አስታውሰን፣ የእልቂት ድቤ መደለቁ ለማንም እንደማይበጅ ተረድተን፣ ሁላችንም መጪውን የአገራችንን ዘመን በፍቅር፣ በሰላምና በይቅርታ እናጥባ::

የሚሆነውም ዳግም ይሄው ነው:: ለግዜው ቢጨልምም ብሩህ ቀን መንጋቱ በፍፁም አይቀርም :: ሰውዬው እንዳሉትም "እኛ እንፈርሳለን እንጂ ኢትዮጵያ አትፈርስም"::

## "ፀሐዩቱን ለማየት በቃሁ"

ወደ አገራችን ከተመለስኩ ጥቂት ቀናት ተቆጠሩ። እንኳን ለአገርህ አበቃህ፣ እንኳን ደኅና መጣህ.... የሚሉ እጅግ በርካታ መልእክቶቻችሁ ደርሰውኛል። ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፤ ሌላ ምን ይከፈላል!

እነዚህን ቀናት ምን ብሎ መጥራት እንደሚገባ ገና አላወኩም። ምናልባት የፈውስ ጅማሬ ሰዓታት ማለት ይቻል ይሆን?

ለማንኛውም የመጀመሪያዎቹን 3 ቀናት ከእናቴና በዙሪያዋ ካሉ ልቦች ጋራ አሳልፌ፣ የአገሬን አድባር አግኝቼ፣ ወደ ከተማው ተቀላቅያለሁ። 22ትን፣ ቦሌ መድኀኔዓለምን፣ ብሔራዊን፣ ፒያሳን በጨረፍታ አይቻለሁ። ገና ብዙ ይቀራል።

ቀድሞ በአካል የማውቃቸውንም ሆነ የማላውቃቸውን ወዳጆቼን በዚህ አጭር ጊዜ ማግኘት ባልችልም፣ ቢያንስ አንድ አገር ውስጥ አብሬያችሁ እንዳለሁ በማስታወስ የታሪክን ጉዞ አደንቃለሁ።

ልጄ አውሮፕላን ውስጥ ደጋግማ "አዲሳባ እየሄድን ነው?" እያለች ትጠይቀኝ ነበር። የጥያቄው ቅለትና ክብደት የሕይወትን ስሱ ውስብስብነት እንደተሸከመ አሁን ባይታያትም የጉዞው አካል ነበረች። እነሆ!

ሸገር ሬዲዮን እሑድ ጠዋት አዲስ አበባ ላይ ሆኜ ስሰማ፣ ጋዜጦቹን ብሔራዊ አካባቢ ቡና እየጠጣሁ ሳነብ... ልቤ "ስለመመለስህ ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ትፈልጋለህ?" ይለኛል። ቢሆንም ገና "ፀሐዩቱን ለማየት በቃሁ" (ከአገረ ሩሲያ የተተረጎመ መጻሐፍ ርእስ) ወደማለት አዘግማለሁ፤ በእርጋታ። በአዲሳባ ጎዳናዎች ብታዩኝ ይህንኑ እያደረኩ ነው።

መሄድም ሆነ መመለስ ረጅምና ውስብስብ ጉዞ ነው፣ አንድ ክስተት አይደለም። የጉዞውን የአደባባይ መልኮች በሂደት እናያቸዋለን።



እንኳን ደኅና ቆያችሁን!!!
መልካም እሑድ።
ቸር ዋሉ፣ ቸር ሁኑ።
አክባሪያችሁ!

*መስፍን ነጋሽ*

## ደማዊ ማንነት

ከሰዓታት በፊት በዋልታ ቲቪ ላይ ከአብን አመራሮች ጋር ጋዜጠኛ ስሜነህ በነበረው ቆይታ ከአመራሮቹ " አማራው ደማዊ ማንነቱን ጠብቆ" ወዘተ ሲባል የሰማሁ መሰለኝ። በነገራችን ላይ ደማዊ ማንነት የሚለው ትርክት የጥንት ትርክት ነው፣ አንድ ብሔር ከራሱ ብሔር ውጪ እንዳያገባ በሚከለከልበት (Endogamous) ዘመን የሚነገር ርዕሰ ጉዳይ ነው። ይህን አመለካከት የሚያረምዱ ወገኖች የጋራ ደማዊ ማንነት እንዳላቸው(Shared ancestry) የሚያምኑ ናቸው። ችግሩ ግን የጋራ ደማዊ ማንነቱ ዕውን የሚሆነው እስከ ስንተኛው አያት ቅድመ አያት....ድረስ ነው? የሚል ነው። አሁን ላይ ግን በአማራ ደማዊ ማንነት ላይ የኦሮሞው፣ የትግሬው፣ የጉራጌው ወዘተ ደም በብሔር ዘለል ጋብቻ(Exogamous) ተቀላቅሏል፤ ጥርት ስላለ ደማዊ ማንነት ብቻ ሳይሆን በግልፅ የተሰመረ ባሕላዊ ማንነት ስለመኖሩም ሽንጣችንን ገትረን የምንሟገትበት ዘመን ላይ አይደለንም... አለ ካልንም ሙግቱ ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ በፖለቲከኞች የሚቀነቀን ነው።

*ጌታሁን ሄራሞ*

## አበበ ቶላ

የምር ግን አቶ ጌታቸው በሰላም ባስ በሰላም እጃቸውን ቢሰጡ እና ከነዳጅም ከጭቅጭቅም ቢገላግሉን ምን አለበት?




## እንግዳማ እንቀበላለን ራሳችንን መቀበል ነው ያቃተን!

በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ልጆቻችንን አረብ አገር ልከን ፍዳቸውን እየበሉ መቶ የማይሞሉ ያውም አገራቸው በጦርነት እሳት እየተቃጠለ ያለ ሚስኪን የአረብ አገራት ዜጎች አገሩ ላይ ሲያይ <<እንግዳ ተቀባይ ደግ ህዝብ እግዜር የመረጣት አገር >> ብሎ ራስን ማታለል ምን ይሉታል ! ሲጀመር አሁን ያለነው ኢትዮጲያን ዜጎች ከዳር እስከዳር እንኳን እንግዳ ራሳችንንም መቀበል የከበደን ሁነናል! ሲቀጥል እነዚህ ዜጎች ወደአገራችን የመጡት አገራችን የተሻለች ስለሆነች አይደለም!! ልክ ድንገት ቤታችሁ እሳት ቢነሳነባችሁ ለማዳን ጎዳና ላይ ከነቃችሁ እንደምትወጡት አይነት ከበጣም መጥፎ መጥፎውን የመምረጥ ጉዳይ ብቻ ነው! በጦርነት ውስጥ ሁነው እንኳን በኢኮኖሚ ከኛ የተሻሉ ጦርነቱ ከቆመላቸውም ከኛ በብዙ እጥፍ በፍጥነት ማገገም የሚችሉ ዜጎች ናቸው! ይልቅ አገራችን አሁንም አገር ውስጥ ብቻ በማይረባ



እንቶፈንቶ በሚሊየን የሚቆጠር ቤት ንብረቱን ትምህርተና ስራውን ጥሎ የሚፈናቀል ስደተኛ ያላት አገር ያለን ህዝቦች መሆናችንን ሳንረሳ የራሳችንን ፎቶ እያየን ራሳች እንረጋጋ ! በመላው አገር ደም እያለቀሰ የሚኖር ሚሊየን ስደተኛ እንዳለን ሳንረሳ!

*አሌክስ አብርሃም*

ከዛሬ ጀምሮ "ተከበናል" የሚል የማደናገርያ ፖለቲካ አይሰራም። የትግራይ ክልሉ ዶር ደብረፅዮን ከፌደራል መንግስት ዶር ዐቢይ አሕመድ፣ ከኤርትራው አቶ ኢሳይያስ አፈወርቂ እና ከአማራ ክልሉ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ጋር ተደምሮ ሰላም ፈጥሯል ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ ህዝባችን ሆይ! አትስጋ! የህወሓት ካድሬዎች የስጋት የውሸት ፕሮፓጋንዳ አትስማ። ትግራይ ከፌደራል መንግስት ወይ ከአማራ ክልል ወይ ከኤርትራ የሚሰነዘር የጥቃት ስጋት አይኖራትም። ሰላም ለሁላችን! It is so!!!



*አብርሃ ደስታ*

## "እግዜር ሊቀጣ ሲል ያደነቁራል!" አፄ ሚኒሊክ!!!
## ሁመራ የጎንደር፣ አሰብ የአፋር መሆኑ ተመስክሯል!!

1. ኤርትራ #ሁመራ የጎንደር መሆኑን #በአምባሳደሯ በኩል እውቅና ሰጥታለች። የተከፈተው ኢትዮጵያን #የተንሰይ_ጎንደር መስመር የሚያገናኘው መንገድ በዛሬው ዕለት መከፈቱን አምባሳደር #እስጢፋኖስ ገልጠዋል። ሀቅ ነው። ሁመራ የጎንደር/የአማራ ነው።
2. ሁሌም ውሸት ስትናገር አንዳንዴ በድንገት #sub_consciously እውነቱ ያመልጥሀል፡ ፡ በዛሬው ዕለት የሆነው ይሄ ነው - #የህወሓት ኮካዎች እውነቱ በድንገት አምልጧቸው ይፋ ወጣ ። በትግራይ በኩል ያለውን #የዛላንበሳ እና #ራማ መንገድ ተዘግቶ #በጎንደር እና #በአሰብ በኩል ያለው መከፈት የለበትም ብለዋል። ወይ #ሁሉም_ይዘጋ አሊያም #ሁሉም_ይከፈት የሚል ዘመቻ ጀምረዋል። ስለዚህ ሁመራ ሆነ አሰብ የእነሱ አለመሆኑን በግልፅ አስመስክረዋል። "እግዜር ሊቀጣ ሲል ያደነቁራል!" አሉ አፄ ሚኒሊክ!!



*ስዩም ተሾመ*



ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)

# ሀገራችን እንዴት ከመስቀልያ ትውጣ?

የሀገራችንን የፖለቲካ መልክዐ ምድር የገለባበጠው የለውጥ ገሞራ ሰከነ ሲባል እየተናወጠ ፣ ከሰመ ሲባል እሳትና ረመጥ እየተፋ ፣ ተስፋና ስጋት እያፈራረቀ ስምንተኛ ወሩን እያገባደደ ነው:: በአጠቃላይ ሕዝባዊ ኃይል ወደሥልጣን ያመጣው የለውጥ መንግሥት በዚህች አጭር እድሜ የሀገሪቱን የመፈራረስና የእልቂት ግስጋሴ (state collapse) በመግታት ረገድ ያከናወናቸው ተግባራት አይናቁም:: ከመርዛማው ዘውጋዊ የጥላቻና የከፋፋይነት ፖለቲካ ወደ አዎንታዊና ሃላፊነት የሚሰማው ሀገራዊ የፍቅርና የአንድነት ፖለቲካ ዞሯል:: የህሊና እስረኞችን ፈትቷል:: ያለገደብ ለሁሉም ተቃዋሚ ኃይሎች እጁን በይቅርታ ዘርግቷል:: እንዲህ ያሉ መደላድሎች ሳይደረጉ ወደ ብሄራዊ እርቅም ሆነ ወደ ብሄራዊ መግባባት መሄድ አይታሰብም::

ከዚህም በላይ መንግሥት ሀገሪቱንም ራሱንም ከውድቀት (state failure) በዘለቄታው ለማውጣት ቀስ በቀስ መሰረቶችን እየጣለ መሆኑ አያጠራጥርም:: የሕወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ የጭቆና ፣ የአፈናና የዝርፊያ መዋቅሮችን በማሻሻል በምትካቸው ቁልፍ ሕጋዊና ተቋማዊ ሥርዓቶችን እየዘረጋ ነው:: ለአብነት ብሔራዊ መከላከያውን ፣ የፋይናንስ ፣ የፍትሕና የምርጫ ሥርዓቶችን ብንወስድ የለውጡን አቅጣጫ በግልፅ የሚያሳዩ ናቸው:: ይሁን እንጂ የተጀመረው እርምጃ ገና በርካታና ውስብስብ ፈተናዎችና እንቅፋቶች ተጋርጠውበታል:: መንግሥት ገና የራሱን ህልውና በማስከበር ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት አልተሻገረም:: በግዛቱ ውስጥ ሉኣላዊ ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ አላረጋገጠም::

ስለዚህም በብሔራዊ ሰላምና ደህንነት በኩል ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦብናል:: ግጭት ፣ ሞት ፣ ዝርፊያና መፈናቀል በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል አለ:: በየአካባቢው ከቁጥጥር ውጭ የሆኑ የጋንግስተር ቡድኖች የተለያየ ታርጋ እየለጠፉ ጥቃቅን መንግሥታት ሆነዋል:: ወጣቶችን እየሰበሰቡ የጦር ሥልጠና የሚሰጡ ህቡዕ ማዕከላት እንደ አሸን ፈልተዋል:: ሰላምና ደህንነትን ማስከበር ያቃተው መንግሥት የሕዝብ አመኔታን ሊያጣ ስለሚችል ከመስቀልያው የመውጣት እድሉ ያጠራጥራል:: በተለይ ሁለት ቀንደኛ የስጋት ምንጮችን በተመለከተ የሚወስዳቸው እርምጃዎች ወሳኝ ናቸው::

## የአኩራፊዋ ሕወሓት ተግዳሮት

አደጋ ቁጥር አንድ የለውጡ ማዕበል ከመሃል ወደ ዳር የገፈተራት ሕወሓት ናት:: የጠ/ሚ ዐቢይ መንግሥት ከቀላል ወደ ውስብስብ የመሄድ ስልት መርጧል:: ከመንበረ ሥልጣን በቅሌት ተባርራ ከነግብረአበሮቿ መቀሌ የመሸገችውን የሕወሓትን ጉዳይ በማሳደር በቅድሚያ ሌሎች አጣዳፊ ችግሮቹን በማቃለል ተጠምዷል:: የተደቀነበትን ፖለቲካዊ ፣ ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ አረጋግቶ እርካቡን በአስተማማኝ እስኪያጠብቅ ድረስ ሕወሓትን ነጥሎ ማቆየትና በየክልሉ የዘረጋችውን ጥገኛ መዋቅሮቿንና መረቦቿን ማፈራረስ የመረጠ ይመስላል::

በሌላ በኩል ሕወሓት ዞሮ ተራዋ እስኪደርሳት እጇን አጣጥፋ አልተቀመጠችም:: ከአንገት በላይ ማስተባበያ እየሰጠች በተንዳኝ ማዕከላዊው መንግሥት ሰላም አግኝቶ እንዳያድር ፣ ሥልጣኑ እንዳይረጋጋና እንዲፈርስ የተቻላትን ሁሉ ትጥራለች:: በመላ ሀገሪቱ የዘረጋቻውን መረብ በማንቀሳቀስ በየአቅጣጫው እሳት ትለኩሳለች፣ ታስለኩሳለች:: በተለይ ደግሞ ለ27 ዓመታት በዝርፊያና በደም ያደፈ እጇን በትግራይ ሕዝብ ጨርቅ ለመጥረግ ተንኮል ትጎነጉናለች::

የዛሬ ስምንት ወር ድንገት ያሽቀነጠራትን ለውጥ ‹‹ከኛው አልወጣም›› ፣ ‹‹ዴሞክራሲን በተግባር እያስተማርን ነው›› በሚል ማስተባበያ ነበር የተቀበለችው:: እያደር ለውጡ እየከረረ የእርምትና የማሻሻያ እርምጃዎች ሲወሰድ ከፈር አይልቀቅ የሚል አቤቱታም ፣ ተማፅኖም ዛቻም ማቅረብ ጀመረች:: አካሄዱ ባይመቸንም ከእኛው እውቅናና ስምምነት ውጭ የተደረገ አይደለም ብላ ተፅናናች:: እንዲያውም ጠንሳሾቹም እኛው ነን ብላ አፅናናች::

የሕወሓት አውነተኛ ማንነት የተገለጠው የኢትዮ- ኤርትራ ፍቅር ▶

በጎረቤት መንደር ሲናፈስ ነበር:: አሁን በትግራይነቴ ከበባ እየተደረገብኝ ነው ማለት ጀመረች:: ጭራሽ ለውጡ ወደ መሰረታዊ ጉዳዮች መዝለቅ ሲጀምር ሕወሓት በቀጥታ እንደመጣባት በማመኗ ኩርፌያና ትዕቢቷ አደባባይ ወጣ:: የኢሕአዴግን ህልውና ጭምር መጠራጠር ጀመረች:: ለውጡን በትዕምርተ ጥቅስ ውስጥ አስገብታ ማዕከላዊ መንግሥቱን መገዳደር መናቅ አበዛች:: ሙሉ በሙሉ ፊቷን ወደ ትግራይ ሕዝብ አዞረች::

አሁን የሕወሓት ትርክትም ተቀየረ:: ተቃውሞዋ እንደ ሉአላዊ መንግሥት በትግራይ ሕዝብ ስም ሆነ:: ይህቺን ሀገር ባሰለጠንክና ከሰው ተርታ ባሰለፍክ ውለታህን ተከድተሃል:: ታሪካዊ ጠላቶችህ ‹‹ትምክህተኞች›› አንሰራርተዋል:: የደማህበትን የማፍረስ ሌጋሲህን የመቀልበስ ዘመቻ ታውጆብሃል:: ከማዕከላዊ መንግሥት የሚመጣው ነገር ሁሉ አደጋ ስለሆነ እፋለመዋለሁ ተከተለኝ በማለት የትግራይን ሕዝብ ከለውጡ በተቃራኒ ለማሰለፍ ላይ ታች አለች::

ይህ በከፍተኛ ደረጃ የተጠናና የተቀናጀ አካሄድ ነው:: ከዶ/ር ደብረፂዮን ጀምሮ በሀገርም በባህር ማዶም የትግራይ ምሁራንና አክቲቪስቶች በየመገናኛ ብዙሃኑ እየተቀባበሉ የሚያራግቡት ‹‹ትግራይ ተጠቃች›› ሎሉታ በተርታው ሕዝብ ዘንድ ተአማኒነት እያገኘ ይመስላል:: እንደምናየው ባለፉት 8 ወራት የትግራይ ክልል ጉዳይ ከዕለት ዕለት እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል:: በማዕከላዊው መንግሥትና በክልሉ መካከል ያለው ግንኙነት ከሰላማዊ ሰልፍና ውግዘት አልፎ በሕግ ለሚፈለጉ ወንጀለኞች ከለላ እስከመስጥና የመከላከያ ኃይሉን እስከማገት ደርሷል::

## የኦነግ ግራ የገባው ተግዳሮት

አደጋ ቁጥር ሁለት የለውጡ ሂደት ከዳር ወደመሃል ያመጣው ኦነግ ነው:: ኦነግ እንዲህ ዓይነት እድል ሲያገኝ ሁለተኛ ጊዜው ነው:: በመጀመሪያ የዛሬ 27 ዓመት ከድል አድራጊዎች ጋር አዲስ አበባ ሲገባ በአካልም በሥነልቡናም ለኢትዮጵያ አልተዘጋጀም ነበር:: ይህንን ድክመቱን በፍጥነት ተረድቶ እንደመፈወስ ይባስ ብሎ በፖለቲካ ጨዋታ ሕግ የተከለከሉ ሁለት ፋውሎችን ሰራ::

አንደኛ አለቅጥ አመነታ:: ኦነግ ለዓመታት ያለውጤት የተዋጋበትን ‹‹የቅኝ ተገዛሁ ልገንጠል›› ጥያቄ እስከ ደርግ መውደቅ ዋዜማ መስከረም 1983 ዓ.ም ድረስ ለመተው አንገራግሮ ነበር:: መቼም ሥልጣን በሯን ወለል አድርጋ ስላማለለችው ያለብዙ እጅ ጥምዘዛ ወደ ሽግግር መንግሥቱ ገባ:: ነገር ግን በገዛ ቤቱ ባይተዋር መሆንን መረጠ:: ሁለተኛ አለቅጥ ተኮፈሰ:: ኦነግ ራሱን እንደብቸኛው የኦሮሚያ ባለቤት አድርጎ ቆጠረ:: በእርግጥም የኦሮሚያን ወጣት ቀልብ መሳብ ቢችልም ፤ ይህንን መንፈስ ወደ አዎንታዊ ንቅናቄ የሚለውጥበት አቅምም ብልሃትም አልነበረውም:: መሬት ላይ ያለው የፖለቲካ እውነታ ሳይሆን የልቡ ጀብደኝነት አሸነፈው:: በትንሽ በትልቁ አኩራፊ ሆነ:: በይፋ እስከለቀቀበት ሰኔ 16 ቀን 1984 ዓ.ም ድረስ የሥልጣን እድሜው ከአንድ ዓመት አልዘለቀም::

> ኦነግ ለዓመታት ያለውጤት የተዋጋበትን <<የቅኝ ተገዛሁ ልገንጠል>> ጥያቄ እስከ ደርግ መውደቅ ዋዜማ መስከረም 1983 ዓ.ም ድረስ ለመተው አንገራግሮ ነበር። መቼም ሥልጣን በሯን ወለል አድርጋ ስላማለለችው ያለብዙ እጅ ጥምዘዛ ወደ ሽግግር መንግሥቱ ገባ። ነገር ግን በገዛ ቤቱ ባይተዋር መሆንን መረጠ

ዘንድሮ ኦነግ ለሁለተኛ ጊዜ ተአምራዊ እድሉን ሲያገኝ በርካታ ነገሮች ተገለባብጠዋል:: በዋነኝነት በወያኔ ተፈጥሮ ኦነግን ያባረረው ኦሕዴድ ፈጣሪውን አባርሮ ሥልጣን ተቆናጥጧል:: ኦሕዴድ አፍንጫውን ተፎንኖ የተያዘበትን የጎሳ ቀለበት ሰብሮ ወጥቷል:: ከቁጥር ብዙሃንነት ወደ ሥልጣን ብዙሃንነት ተሸጋግሯል:: ስለዚህም በኦሮሞ ሕዝብ መካከል አጋር ቢሆነኝ በሚል በተለይ ለኦነግ በልዩ ሁኔታ የሰላም እጅ ዘርግቶለታል:: ኦነግም ያለብዙ ማንገራገር ተቀብሎ ወደ ሀገር ቤት ተመልሷል::

ነገር ግን ኦነግ አሁንም የጥንቱን ስህተቶቹን በአሳዛኝ ሁኔታ እየደገመ ወደዳግም ውድቀት አፋፍ ደርሷል:: አሁንም አለቅጥ ያመነታል:: የዐቢይና የለማ ኦፒዲኦ በግልፅ እንዳይቃወመው ኦሮሞ ፤ በሙሉ ልብ እንዳይደግፈውም ኢትዮጵያዊ ሆኖበታል:: ስለዚህም በኦሮሞነትና በፖለቲካ ፍላጎቱ መካከል በሽምግልና እየተዳለለ ይዋልላል:: በተጨማሪ ለሰላማዊ ሀገራዊ ፖለቲካ በቅጡ አልተዘጋጀም:: በአንድ እጁ ሀገራዊ ሚና የሚሻ ተፈካካሪ ይመስላል:: በሌላው እጁ ደግሞ ያችንው ‹‹የተገንጣይነት›› ካርድ ገባ ወጣ ያደርጋል::

በተለይ ደግሞ አጅግ አለቅጥ ይኮፈሳል:: አሁንም በሕዝብ ልቡና ውስጥ አለኝ በሚለው ተቀባይነትና በድርጅታዊና ወታደራዊ አቅሙ መካከል ያለውን የሰማይና የምድር ልዩነት በውል የተገነዘበ አይመስልም:: ራሱን በመንግሥት ውስጥ ያለ መንግሥት አድርጎ ይመለከታል:: ‹‹ብፈልግ ኦሮሚያን ከመቅፅበት መገንጠል እችላለሁ›› ፤ ‹‹በጡንቻዬ ራሴን አስከብራለሁ›› እያለ ይግደረደራል:: አሁንም ‹‹እውነተኛ መስዋዕትነት የከፈልኩት እኔ ብቻ ነኝ›› ፤ የኦሮሞ ህዝብም ቄሮም የኔው ብቻ ነው በሚል አጉል ስሜት ይናውዛል:: ከታሪክ የማይማሩ ታሪክን ለመድገም እንደተፈረደባቸው ግልፅ ነው::

## ምን መደረግ አለበት ?

መንግሥት በመጀመሪያ ደረጃ የሀገሪቱን ህልውና የሕዝቡን ደህንነት አደጋ ላይ የጣሉትን ቀንደኛ ችግሮች የማያዳግም መፍትሄ መስጠት አለበት:: በዚህ ረገድ በኦነግ ላይ ከእልህ አስጨራሽ ትዕግስትና ኪሳራ በኋላም ቢሆን መውሰድ የጀመረውን ሥርዓት የማስያዝና ሕግ የማስገባት እርምጃ አጠናክሮ መቀጠል የግድ ነው:: ነገር ግን ትልቁ አደጋ ራሱን በትግራይ ሕዝብ መካከል የመሰገው ሕወሓት መሆኑ ግልጽ ነው:: መንግሥት የለውጡ ጠላትና ሀገሪቱን ለእርስ በርስ ጦርነት የሚያዘጋጅ ፤ በየአቅጣጫው ቅጥረኞቹን እያሰማራ እሳት የሚለኩስ ይህ ሃይል እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል:: ይህን ቡድን ያለመቅለስለስ እገሌ ብሎ በመጥራት ከሕዝብ የሚነጥል ሰፊና ያላሰለሰ ዘመቻ ማድረግ ለነገ የማይባል ተግባር ነው::

ሕዝብ ሰላሙን ከማረጋገጡ ጎን የሚበላው ይፈልጋል:: በኤኮኖሚ ረገድ አሁንም መንግሥት በይደር ያልተነካ ትልቅ ፈተና ይጠብቀዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመችቶት ሳይሆን 27 ዓመት በታጠፈ አንጀቱ ነው እየደገፈው ያለው:: በየእለቱም ሰላም በጠፉ ፤ አሻጥር በተስፋፋ መጠን ሕዝቡ ሊታገስ የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል:: ለቀልባሽ ኃይሎች የተመቸ ይሆናል:: በዚህም ረገድ ሕዝብን የሚጠቅሙ እርምጃዎችን ሳይንቁ በአስቸኳይ መተግበር ፤ የሚጎዱ ነገሮችን ደግሞ ማስወገድና ችግሮችን መፍታት የግድ ነው::

ሰላሙ የተረጋገጠለትና የሚበላው ያገኘ ሕዝብ ደግሞ ሌሎች ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ መብቶቹን መጠየቁ አይቀሬ ነው:: አዲሱ መንግሥት ካለፈው የተለየ መሆኑን የሚያደበዝዙ የግልፅነት ፤ የተጠያቂነት ጉዳዮችን በጥንቃቄ መያዝ አለበት:: በድብቅ ጓዳ ለጓዳ የሚደረጉ ውሎችና ድርድሮች ፤ ከሕዝብ እውቅና ውጭ በእኔ አውቅልሃለሁ የሚደረጉ ምርጫዎች ፤ ሹመቶች ፤ ወዘተ ማስቀረት አለበት:: የለውጡ ዋነኛ ክንድ የሆነውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ተስፋ እንዳይቆርጥ ፤ እንዳይዘናጋ ፤ ልቡ እንዳይከፈልና ለሴረኞች እንዳይመች በቁርጠኝነት ከጎኑ ማሰለፍ አለበት::

ለማንኛውም ዶ/ር ዐቢይ ካሮቱም ቆመጡም በእጃቸው ነው:: የተደቀነባቸው ችግር በዘገምታና በቁጥቁጥ እንደማይዘለቅ አይስቱትም:: በየስፍራው በየዕለቱ የሚሞተውና የሚፈናቀለው ዜጋ እንቅልፍ የሚነሳ ኃላፊነት ተሸካሚ ናቸው:: ስለዚህም ራሳቸውንና መንግሥታቸውን ከጡት ልጅነት ሥነልቡና አላቅቀው ፤ ይዋል ይደር ሳይሉ የዘንዶውን አናት ጎሬው ድረስ ዘልቀው መምታት አለባቸው:: ዋነኛው ክንዳቸው የሆነውን ሕዝብን ይዘው በመላ ሀገሪቱ የተሰገሰጉትን ፀረ-ለውጥ ኃይሎች በማፅዳት ሀገራችንን ከመበታተንና ዜጎቿን ከእልቂት አደጋ ለማዳን ይቻላል:: በተረፈ ለውጡ እዚህም እዚያም ተፈጥሯዊ መንገራገጭ ቢያሳይም በትክክለኛው ጎዳና ላይ መሆኑ አያጠራጥርም!!

# ጌታቸው አሰፋና የሕወሓት “የክፉ ቀን” የቤት ሥራ

<u>*ሮቤል ምትኩ*</u>




ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን መውጣታቸውንና የለውጡ የፊት መሪ “ቲም ለማ” በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን ተከትሎ፣ ከጅምሩ የከረረ ውዝግብ ውስጥ የወደቀው ሕወሓት ከመንበረ ሥልጣኑ ተገፍትሮ ከተጣለ በኂላ፣ በመሸገበት ትግራይ ውስጥ ሆኖ ለውጡን ለማደናቀፍ ባለ በሌለ ኃይሉ ደፋ ቀና ሲል ከርሟል:: አሁንም በዚሁ የጥፋት መንገድ መባዘኑንና መውተርተሩን ቀጥሎበታል::

የእነ አቦይ ስብሃት ነጋ ሕወሓት ኢትዮጵያውያንን አንገታቸው ላይ ቆሞ “በግድ እኔ ያልኩትን ተቀበል” ከማለት ባሻገር ሀገሪቷን ያለ ርህራሄ፣ቤተሰባዊ ዝምድናን መሠረት ባደረገ ቡድን ተዋቅሮ ሲመዘብራት ከርሟል:: በጥቂት ቡድኖች ተጠቃሚነትና የበላይነት ሲዘወር የከረመው ኢሕአዴግ በአራት ድርጅቶች የተዋቀረ ነው ቢባልም ሦስቱ (ብአዴን፣ ኦህዴድ፣ ደኢህዴን) ሕወሓት ለእሱ በሚመች መልኩ ጠፍጥፎ የሰራቸው፣ በድርጅቱ ነባር ታጋዮች ቀጥተኛና ስውር እጅ የሚሽከረከሩ፣ “ሲጠሯቸው አቤት የሚሉ ሎሌዎች” እንደሆኑ አይካድም::

ኢሕአዴግ በወርሃ ግንቦት በ1983 ዓ.ም አዲስ አበባን ከያዘበት ማግስት አንስቶ ትኩረት ሰጥቶ የሰራበት የዘረኝነት ፖለቲካ፣ ዛሬ አድማሱን አስፍቶ ከዘውግ ማንነቱ ይልቅ ኢትዮጵያዊነቱን የሚያስቀድመው የአማራ ሕዝብ እንኳን በስሙ ሲነገድበት ዝም እንዲል ተገዶ ነበር:: ፍፁም ባልተጠበቀ ሁኔታ የመጣውን ለውጥ ለመቀልበስ በተቃራኒው ጎራ የተሰለፈው ሕወሓት ይህቺን ሀገር በታትኖ፣ አንድነቷን አፈራርሶ በሚፈጠረው ክፍተት እንዳለፉት ዘመናት ሁሉ ራሱን በመንበረ ሥልጣኑ ላይ ለማስቀመጥ እየተጠቀመበት የሚገኘው የዘር ፖለቲካ መሆኑን በገሀድ ተመልክተናል::

ወያኔ “ለክፉ ቀን” ያስቀመጠው የቤት ሥራ እስከመስል ድረስ ዛሬ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ብሔር ተኮር ግጭቶችን እየቀሰቀሰ፣ በተወሰኑት ቦታዎች ላይ ራሱን እያሳተፈና በመላ ኢትዮጵያ ለሚከሰቱ ግጭቶችና እልቂቶች የፕላቲኒየም የክብር ስፖንሰር እየሆነ ይገኛል:: ሕወሓት ለውጡን እንደማይቀበል በተግባር ከማሳየቱም ባሻገር፣ የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት ከሙስናና ከሰብኣዊ መብት ጥሰት አኳያ እየወሰደ ያለውን ሕጋዊ እርምጃ ከአንድ ብሔር ጥቃት ጋር በማያያዝ፣ የትግራይን ሕዝብ ለአመፅና ለጦርነት በመገፋፋት ለፌደራል መንግሥቱ አልታዘዝም ባይነቱን አሳይቷል::

በሀፍረት መሸማመቅና የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ ይገባቸው የነበሩት የሕወሓት ባለሥልጣናት በአደባባይ የለውጡን ቡድን ያብጠለጠሉበት፣ ጨካኝና አረመኔነታቸውን እንደ ጀብዱ የተረኩበት መንገድ በትግራይ ሕዝብ ስም የሚነግዱትን ጥቂት ቡድኖች ማንነት ያጋለጠ ትእይንታዊ ድራማ ነበር:: የክልሉ ሕዝብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ ክፋይ የመሆኑን ያህል ፋሽስታዊ ድርጊት በወገኖቹ ላይ ፈፅመው በጉያው የተደበቁት ወንጀለኞችና ሌቦች፣ በተጀመረው ትክክለኛ የሕግ መስመር ውስጥ እንዲገቡና ለፍርድ እንዲቀርቡ ፣የሚታየው የለውጥ ተስፋም የበለጠ እንዲያብብና ያማረ ኢንዲሆን የሚታይ ድጋፍ ያለማድረጋቸው ጉዳይ ግን ለብዙዎች አሁንም ዕንቆቅልሽ ሆኗል::

የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት ተፅዕኖ ውስጥ ወድቋል፣ በኃይል ተይዟል እየተባለ በሚነገርበት ወቅት ሰሞኑን በክልሉ የተለያዩ ከተሞች ላይ ሲንቀሳቀስ የነበረውን የሀገር መከላከያ ሠራዊት “አናስወጣም፣ አናስገባም” ሲሉ አንዳንድ የትግራይ ወጣቶች ያደረጉት እንቅስቃሴ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ያስገድዳል:: ከባድ መሳሪያዎችን የታጠቀውና የጫነውን ሠራዊት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለማስቆም የተሄደበት መንገድ በእጅጉ አሳዛኝ ነበር ማለት ይቻላል:: ለጥቂት ግለሰቦች አጀንዳ ማስፈፀሚያ በሆነ መልኩ ያልተገባ ተቃውሞ ሲደረግም ታዝበናል::

አንዳንድ የትግራይ ተወላጆች በተሳሳተ ፖለቲካ ተነድተው ራሱን በሚጠብቁት የመከላከያ ሠራዊት አባላት ላይ ያሳዩት ያልተገባ ድርጊት፣ በጦር መኪኖቹ ላይ ወጥቶ ከመንጠልጠልና ከመጮህ ሊዘል ያልቻለው፣ በሰራዊቱ ታጋሽነትና በፌደራል መንግሥቱ አስተዋይነት ነው:: ድርጊቱን ከዳር ሆነው ከሚመለከቱት፣ አመጽ እንዲነሳ ቡድን መስርተው በእንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ እስከነበሩት የሕወሓት አፍቃሪዎች መሀል በትግራይ ምድር እንደ አምዶም ገብረስላሴ ያሉ ለእውነትና ለፍትሕ የቆሙ፣ በፈታኙና ከባዱ ሰዐት እንኳን ከሞትና አምባገነኖች ጋር ፊት ለፊት ሆነው ሐቅን የሚመሰክሩ ጥቂት ወጣቶች መኖራቸውን ስናስብ፣ ብዙኃኑ ኅብረተሰብ በቅርቡ ፍርሀቱን ገፎ ሕወሓትን በማውገዝ ለለውጡ ቡድን ድጋፉን ይሰጣል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

ሕወሓት በ27 ዓመት የሥልጣን ዘመኑ እንደ ኦሮሞና አማራ ሕዝብ ከባድ ግፍ የፈፀመበት ባይኖርም፣ “ወክዬዋለሁ” የሚለውን የትግራይን ብዙኃኑን ሕዝብ አለመጥቀሙም ሐቅ ነው:: መለስ ዜናዊ፣ ስብሐት ነጋና አቦይ ፀሀዬ ከጦር ጀነራሎቻቸው ጋር በመሆን የሚያሽከረክሩት ሥርዓት ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ በተለያዩ አጋጣሚዎች በርካታ ዜጎችን ሲገድል፣ ሲያስር፣ ዘር ሲያመክን፣ ጥፍር ሲነቅልና አካል ሲያጎድል ምክንያቱ የሥልጣን የበላይነቱንና ዘራፊነቱን ላለመነጠቅ ብቻ መሆኑ ደግሞ ያሳዝናል:: የሚቃወሙትን በሙሉ አምርሮ የሚጠላው ወያኔ ይህን ግፍ ሲፈፅምና እውነታው ገሀድ ሲወጣ ለመመስከርም ሆነ ለማውገዝ ዘር መስፈርት ሊሆን አይገባውም:: ሰው መሆንና ጥሩ አዕምሮ መያዝ በራሱ ፍትህ መጓደሉን ለመናገር በቂ ነውና::

ከላይ የተፈፀሙት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ገሃድ መውጣት በጀመሩባቸው ባለፉት ሰባት ወራት ውስጥ ስማቸው በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት እነዚህ የሕወሓት ቱባ ባለሥልጣናት ለዓመታት ለፈፀሙት ኢ -ሰብዓዊ ጥሰትና የሌብነት ወንጀል መጠየቃቸው እንደማይቀር ሲረዱ፣ አንድም በቂ ማስረጃ በሚያዙ ሰዎች አማካይነት ሾልኮ እንዳይወጣ፣ ሁለትም የአልሞት ባይ ተጋዳይነታቸውን ለማመላከት በወንጀል የሚጠረጠሩ ሰዎችን አሳልፎ ላለመስጠት የትግራይ ክልል በእምቢተኝነቱ ገፍቶበታል::

በተለይም ዋናው ወንጀለኛና የደህንነት ኃላፊ የነበረው የጌታቸው አሰፋ ጉዳይ በእጅጉ አነጋጋሪ ሆኗል:: ከደህንነት ሥራ በተለየ መልኩ ልዩና አፋኝ የማፊያ ቡድን መስርቶ ንፁሃን ዜጎችን ከአማራ፣ ከኦሮሞና ከአዲስ አበባ እያፈነ ሲገድልና ሲያሰቃይ የነበረው ይህ ሰው በቁጥጥር ስር ውሎ ለሕግ እንዳይቀርብ የሕወሓት ነባር ታጋዮችን ጨምሮ የክልሉ መንግሥትና አፍቃሪ ሕወሓቶች የወረደ ተግባር በመፈፀም የፌደራል መንግሥቱን ክፉኛ እየፈታተኑና አላስፈላጊ ዕልቂት እንዲፈጠር እያደረጉ ይገኛሉ::

ባሳለፍነው ሳምንት መገባደጃ በማኅበራዊ ድረ ገፆች አቶ ጌታቸው አሰፋን አስመልክቶ የወጡ ያልተጨበጡ መረጃዎች ደግሞ ጉዳዩን እንደ አዲስ አቀጣጥለውታል:: የፌደራል አቃቤ ሕግ ጌታቸው አሰፋ በትግራይ መኖሩን እንዳረጋገጡና የክልሉ መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆኑን መግለፁን ተከትሎ “ጌታቸው አሰፋ በመኖሪያ ቤቱ በፌደራል ፖሊሶችና በሰሜን ዕዝ መከላከያ ሠራዊት ተከቧል” የሚሉ መረጃዎች ከተለያየ አቅጣጫ ወጥተው ነበር ፤ ዘግየት ብሎ ደግሞ “ሕወሓት ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ ሰጥቷል” የሚል ያልተረጋገጠ መረጃ መሰማቱ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ የተለያዩ ቡድኖች ጎራ ለይተው ግልጽ ወደ ሆነ ስድብና መበሻሸቅ ገብተው፣ የብሔርተኝነት ፖለቲካ የበለጠ እንዲንሰራፋ በር ከፍቷል:: ማኅበራዊ ሚዲያዎች ያላቸው ጠቀሜታ የጎላ ቢሆንም፣ እንዲህ ያለው ከባድ ጉዳይ ሕዝብን የበለጠ ስሜታዊ ያደርጋልና በሚወጡ መረጃዎች ላይ ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም መሆኑን እየገለፅን፣ የጌታቸው ጉዳይ በፍጥነት ዕልባት እንዲያገኝ ዛሬም ለሚመለከተው አካል ጥሪ እናቀርባለን:: ማንም ሰው ከሕግ በላይ ሆኖ በዚች ሀገር ላይ ሊኖር አይገባውምና:: ወንጀል ፈፅሞ በህዝብ መሀል የተደበቀ ግለሰብን አሳልፎ ለመስጠት የማይፈልግ አካል የወንጀሉ ተባባሪ ያህል በመሆኑ ጠንከር ያለ ዕርምጃ መንግሥት በፍጥነት ሊወስድ ይገባል::

# አንደበት



"ኦነግ የተመሰረተው ወለጋ ነው:: ሲመሰረት እኔንም ጋብዘውኛል:: ገንዘብም ጠይቀውኝ አንድ ሁለቴ ጊዜ ትንሽ ገንዘብ ሰጥቻቸዋለሁ:: ከዛም የኦሮሞ ነፃ አውጪ ግንባር ተብሎ ተመሰረተ:: ይሄ ምን ለማድረግ ነው? ብዬ አቶ ገለሳ ዲልቦን ጠየቅኩት:: ኦሮሞ እስከ መቼ ተጨቁኖ፣ መሬቱን ተቀምቶ ለሌሎች እንደ ባሪያ ገብሮ ይኖራል አለኝ:: ይሄ ጥሩ ነው:: ነገር ግን ከኢትዮጵያ ተለይቶ መኖር አይችልም አልኩኝ:: እነርሱ ጋር ያልገባሁትም ኦሮሞ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ሌላ አገር ይሆናል የሚለውን ተቃዋሚ ነው::"

***አቶ ቡልቻ ደመቅሳ***
***አዲስ ዘመን ጋዜጣ ታህሳስ 27 ቀን 2011 ዓ.ም***



"በጥበቃ አናምንም:: የጥበቃ ኃይል ተመድቦ፣ እየተጠበቅን አድዋ መግባት ለኛ ሽንፈት ነው:: ለኢትዮጵያም ኪሳራ ነው:: እኛ የምንፈልገው ሰው አቀባበል፤ አሸኛኘት እንዲያደርግልን ነው እንጂ ማንም እንዳይነካን በጠመንጃ ተጠብቀን ማለፍ አንፈልግም:: የኛ ፍላጎት ሀገራችን ሰላም መሆኗን ማረጋገጥ እንጂ በጠመንጃ አፈሙዝ ተከበን፣ ሰላም ሆነን መግባት አይደለም:: ይሄ የሽንፈት ሰላም ነው::"

***አርቲስት ያሬድ ሹመቴ***
***አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታህሳስ 27 ቀን 2011 ዓ.ም***



"የግዕዝ ፊደል ብሄር የለዋም:: የግዕዝ ፊደልን የፈለሰፉ ሰዎች ዘራቸው ምን እንደሆነ ማን ያውቃል? መፈልሰፉን እና በጥቅም ላይ መዋሉን ነው የምናውቀው:: መጀመሪያ የተጠቀሙበት ሕዝቦች፣ በጦርነትም ይሁን በሌላ ምክንያት ሲፈልሱ ፊደሉን እያስተማሩ፣ ከሌሎች ጋር እየተቀላቀሉ እና ሌሎችም ፊደሉን እየለመዱት ሄዱ:: ፊደሉ እስከ ጋሞ ጎፋ፣ እስከ ባሌ ተስፋፍቶ ነበር:: ባለቤቱ አንድ ብሔር ነው የሚባለው ስህተት ነው:: ግዕዝ አፍሪቃዊ ቋንቋ ነው::"

***ዶክተር እርቁ ይመር***
***ኢትዮጲስ ጋዜጣ ታህሳስ 27 ቀን 2011 ዓ.ም***



"ጋሽ አያልቅበት በጣም አምባገነን ሰውዬ ናቸው፤ ተንኮልን ሥራዬ ብለው የሚሰሩ ሰውዬ ናቸው:: ግን እንዳልከው ሰው ልብ ውስጥ ያሉ ሰው ናቸው መሰለኝ ጋሽ አያልቅበትን ብዙ ሰው አይጠላቸውም:: በሆነ መንገድ የሚያውቀውን ሰው ወይ ራሱን አገናኝቶ ያስባል እንጂ አይጠላቸውም:: አንዳንዴ እኩይ ገፀ ባህሪይ ስትሰራ ሰው ይጠላሃል:: መንገድ ላይ ሲያይህም "ይሄ ክፉ" ምናምን ነው የሚልህ፤ ለኔ ግን ተመልካች እንደዛ ዓይነት ነገር የለውም:: አምባገነንነታቸውን ሳይደብቁ ፊት ለፊት የሚያደርጉ ሰው ስለሆኑ የሕይወት አንድ አካል እንደሆኑ አስቦ ብዙ ሰው ዘና ሲልባቸው ነው የማየው::"

***አርቲስት ሚካኤል ታምሬ***
***አዲስ ማለዳ ጋዜጣ ታህሳስ 27 ቀን 2011 ዓ.ም***



"ለፍርድ ቤት ተነገረ የተባለው ነገር ፍርድ ቤቱ ውድቅ እንዳደረገው ሰምቻለሁ:: ምክንያቱም የሚቀርብ ማስረጃ ስለሌለው:: ዜናው በወቅቱ በኢሳት ላይ ሁሉ ቀርቦ ነበር፤ ግን እንደ ሚዲያ ማጣራትና እኔን መጠየቅ ሁሉ ይቻል ነበር:: ቢጠይቁኝ ኖሮ ምላሼ ግልጽ ነው:: ኢሳት በአሸባሪነት የተፈረጀ ስለነበር አልቻለም:: በቅርቡ ከኢሳት ጋር ተነጋግረን ተማምነናል:: አንደኛ የሰው ልጅ በአስተሳሰቡና በአመለካከቱ ሳቢያ የዚህ አይነት ጭካኔ የተሞላበት ድርጊት ሊፈፀምበት አይገባም የሚል እምነት ያለው ሰው ነኝ::"

***የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ የነበሩት አቶ መለስ ዓለም***
***ቁም ነገር መጽሔት ታህሳስ 2011 ዓ.ም***

# ጠቅላላ እውቀት

- ሳቅ በሽታን የመቋቋም አቅምን ይጨምራል፡፡ ካንሰርን ጨምሮ!!!
- ሳቅ የሰው ልጆች ምስጢራዊ የህመም ማስታገሻ ነው፡፡
- ሲጣሉ እርስ በርሳቸው የሚሰዳደቡ እንስሳት ጎሬላ እና ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡
- የጎሬላ እና የሰው ልጅ ዘረ መል ወይም ዲ.ኤን.ኤ በ98 ፐርሰንት ደረጃ ይመሳሰላል፡፡
- መሳርያ በመጠቀም አደን ላይ የሚሰማሩ እንስሳት ሰው እና ፒምፓንዚ ብቻ ናቸው፡፡
- እርስ በርስ ቅማል በመቀማመል፣ አንዱ የሌላውን ፀጉር በማበጠር እና አንዱ ሌላዋን በመኳኳል በጋራ የሚዋቡ እንስሳት ሰው፣ ኾርንጀሮ እና ቺምፓንዚ ናቸው፡፡
- በጀርባው መተኛት የሚችል ብቸኛው እንስሳ ሰው ነው፡፡ ሰው በጀርባው ተኝቶ በርካታ ሥራዎችንም መሥራት ይችላል፡፡
- ራሳቸው በመስታወት ዐይተው መልካቸውን መለየት የሚችሉ ፍጥረታት ሰው እና ቺምፓንዚ ብቻ ናቸው፡፡

## የሐበሻ ጸሎት

‹‹በጽልመት መኖሩ፣ መች እኛን ጨነቀን
ብርሃን ማየት ነው፣ ወትሮም የናፈቀን፡፡››
እያለ የሚኖር፣
በብርሃን እጦት፣ ፀሎቱ ያረገ
በእርግማን ብዛት፣
ፅልመትን ይገፋል፣ ሀገሩ እያደገ፡፡
በጨለማ ብዛት፣
መኖር የሰለቸው፣ በደስታ ሚጮኸው
የጠፋበት መብራት፤
ባላሰበው ሰዓት፣ ድንገት ሲመጣ ነው
ብርሃን አይቶ መጮህ፣ ሌላኛው ፅልመት ነው፡፡
እናም ይሄ ጩኸት…
ቅኔ እየሆነበት፣ የጠፋበት ወርቁ
ያገሬን ሰው ሁሉ…
ሰሙን እያበራ፣
ብርሃንን የሚያይ፣ ጨለማ ነው ትጥቁ፡፡

*የወፍ ጎጆ ምህላ*
*ኤፍሬም መኮንን 2011 ዓ.ም*

# መጽሐፍ

## ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው
## 18 83-1955ዓ.ም

| | | |
|---|---|---|
| የድሆች ከተማ | | 1943 ዓ.ም |
| ሐሳብና ሰው | ልብ ወለድ | 1943 ዓ.ም |
| ግልሰዊ ምሬት | | 1943 ዓ.ም |
| የደም ድምጽ | ተውኔት | 1940 ዓ.ም |
| ጣይቱ ብጡል | ተውኔት /ታሪካዊ/ | 1950 ዓ.ም |
| አልሞትኩም ብዬ አልዋሽም | | |
| አርሙኝ | ልብ ወለድ | 1947 ዓ.ም |
| ዓለም ወረተኛ | ልብ ወለድ | |
| የህልም ሩጫ | ልብ ወለድ | 1949 ዓ.ም |
| የደም ምንጭ | ልብ ወለድ | 1939 ዓ.ም |
| የደም ዘመን | ልብ ወለድ | 1947 ዓ.ም |
| የፍቅር ጮራ | ልብ ወለድ | 1949 ዓ.ም |

# አባባል

"በአንድ የገቢ ምንጭ ላይ ብቻ የሙጥኝ አትበል፤ ሁለተኛ አማራጭ ለመክፈት ያለህ የሌለህን አቅምህን አሟጠህ ተጠቀም፡፡" ዋረን ቡፌት
"ስኬት እንደ ተዓምር መወሰድ የለበትም፤ የትጋት፣ የምርጫና የጽናት ጉዳይ ነው፡፡" ሚሼል ኦባማ
"መልካም አጋጣሚዎች እንደ ጠዋት ፀሐይ ናቸው፡፡ ብዙ ከጠበቀናቸው እናጣቸዋለን፡፡" ዊሊያም አርተር ዋርድ
"በሕይወት ውስጥ ማስመዝገብ የምትፈልገው ድል ከአፍንጫህ ስር ነው ያለው፡፡ በፍፁም እጅ እንዳትሰጥ፡፡" ኒኪ ሚናጅ

# መንግሥት በይቅርታው ገፍቶበታል፤

ሮቤል ምትኩ

ሕወሓት/ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥት ለ27 ዓመታት ሥልጣን ላይ ከቆየባቸው ዓመታት ሁሉ የመጨረሻዎቹ ሁለትና ሦስት ዓመታት፣ሥርዓቱ በሕዝብ ጫናና ግፊት በሚመጡ ጠንክር ያሉ ተቃውሞዎች ከመንገዳገድ አልፎ ከባድ አጣብቂኝ ውስጥ የገባበት ነበር ማለት ይቻላል:: ዜጎች የመናገርና የመጻፍ፣የመደራጀት መብታቸው ተገፎ፤ለይስሙላ በተቀመጠ ዴሞክራሲ ውስጥ ሲዳክሩ፣ የሕግ የበላይነት ተጥሶ፣ ፍትሕ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ሲጓደልና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱ ወደ ተወሰኑ ቡድኖች ሲያዘነብል፤ማንነትን የተመረኮዙ ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ ምላሽ ሊሰጣቸው ሲገባ ወደ ብሔር ተኮር የጥቃት ዘመቻ መሸጋገራቸው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምባገነኑን የኢሕአዴግ ሥርዓት አምርሮ እንዲጠላ ካደረጉት ዘርፈ ብዙ ችግሮች መሀል ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው::

በዚህን መሰሉ ግርግርና መንገዳገድ ውስጥ ሆኖ ከጎንደር እስከ መላ ኦሮሚያ የደረሰውን ተቀጣጣዩን የሕዝብ ተቃውሞ፣ ጥይት እንደ ዝናብ ሲወርድበት ያላፈገፈገውን የነጻነት ተጋድሎ፤ ኢሕአዴግ በለመደው ድርጅታዊ ዘዬ ለማርገብ በመሞከር (የአራቱ ድርጅቶች የጋራ ውሳኔ መሆኑ ይታወቃል) አምርሮ ይጠላቸው የነበሩና በሽብርተኝነት የፈረጃቸው እስክንድር ነጋ፣ አንዷለም አራጌ፣ ዶ/ር መረራ ጉዲናና በቀለ ገርባን የመሰሉ ጥቂት ታዋቂ ፖለቲከኞችን በመፍታት ነገሩን ለማለዘብና ሕዝባዊ አመጹን ለማዳፈን ሞክሯል::

በርግጥ በጊዜው በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲፈጠር፣ በሕወሓት መራሹ መንግሥትም በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን ማሰር፣ማፈንና መግደሉን እንዲያቆም በመጠየቃቸው፣ በመፃፋቸው ለእስር የተዳረጉ፤ በሰላማዊ ትግል የሚንቀሳቀሱ ፖለቲከኞች ከእስር እንዲፈቱና ካሉበት የመከራ ሕይወት እንዲወጡ ተደጋጋሚ ጥያቄዎችን አቅርቧል:: ጥቂት የፖለቲካ እስረኞች በተፈቱ ማግስት ከጠ/ሚኒስትርነታቸው መልቀቃቸውን የነገሩን የአቶ ኃ/ማሪያም መንግሥት በወቅቱ የሕዝብን ጥያቄ ለማደመጥ የሞከረ መስሎ ቢቀርብም እውነታው ግን ከዛ ያፈነገጠ ሆኖ በግልጽ ታይቷል::

ስማቸው የገነነና በተለይም በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የመታሰራቸው ጉዳይ አነጋጋሪ በመሆኑ ኢሕአዴግን በተደጋጋሚ ሲያስተቹት ከነበሩት የፖለቲካ ሰዎች መሀል የተወሰኑት በይቅርታ መለቀቃቸውና ብዙዎች ፍትሕን ሳያገኙ በእስር መማቀቃቸው፤ በዛው ሰሞን ጠንከር ባለ ዘመቻና አስቀድሞ በተቀመጠው የኮማንድ ፖስት አዋጅ በሺዎች የሚቆጠሩ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች (በተለይም ወጣቶች) በጅምላ መታፈሳቸው፣ መደብደባቸውና መገደላቸው፤ ኢሕአዴግ ለመለወጥ ያልፈለገና በሕወሓታዊው “ጨፍልቀህ ግዛ ” ፖለቲካ ውስጥ ሌላ ዘመን ለመኖር የሚጓጓ ፀረ ሕዝብ ድርጅት መሆኑን አጋልጧል::

የሕዝብ ጥያቄና ግፊት ማየሉን ተከትሎ በድርጅቱ ውስጥ ከዘር፣ ፖለቲካና “ከአምልኮተ ወያኔ ሥርዓት” ባፈነገጠ መልኩ ኢትዮጵያዊነትን፣አንድነትን፣መደመርንና ሕዝባዊ ፍቅርን መሰረት አድርገው አስገራሚ በሆነ ሁኔታ አፈንግጠው የወጡትና ባልተጠበቀ አጋጣሚ በኢሕአዴግ ውስጥ የበላይነቱን የጨበጡት የቲም ለማ ቡድን አባላት፣ ከላይ የተጠቀሱትን የፖለቲካ ዕስረኞች ጨምሮ በርካታ የነጻነት ታጋዮችና የኅሊና እስረኞች ከበረታ ስቃይ ውስጥ እንዲወጡና የሰላም አየር እንዲተነፍሱ አይነተኛ ሚና ከመጫወት ባሻገር ለ27 ዓመታት ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የቆየው ሕወሓትና ጀሌዎቹን አስገድደዋል ማለት ይቻላል::

> በመደመር ዘመን በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች፣ በሙስና፣ በታክስ ማጭበርበርና በአራጣ ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ፤ እንደዚሁም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው በርካታ ግለሰቦች በምህረትና ይቅርታ አሰጣጡ ውስጥ ተካተው በተለያዩ ጊዜያት ከእስር እንዲፈቱ ተደርገዋል

በተለይም ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ በትክክልም የፖለቲካ እስረኞች ነጻ መውጣት ችለዋል::የመደመርና የይቅርታ መርህን በአደባባይ ያስተጋቡት ጠ/ሚኒስትር አሕአዴግ በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘብ በማውጣት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ከሰው ሀገር አፍኖ በማምጣት ለአስከፊ እስር የዳረገውንና እውነተኛው የነጻነት ታጋይ አንዳርጋቸው ፅጌን ከመፍታት አልፈው፣ በብሔራዊ ቤተ መንግሥት በመጋበዝ የተለጠፈበት የሽብርተኝነት ታፔላ የወያኔ የፈጠራ ክስ እንደሆነ፣ግለሰቡ ለሀገሩና ለሕዝቡ ካለው ፅኑ ፍቅር የተነሳ ዕድሜውን ሙሉ ለከፈለው መስዋዕትነት ክብር የሚገባው ታላቅ ሰው መሆኑን በግልጽ በሚታይ ቅንነት አረጋግጠዋል::

በመደመር ዘመን በተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች፣ በሙስና፣ በታክስ ማጭበርበርና በአራጣ ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙ፤ እንደዚሁም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈባቸው በርካታ ግለሰቦች በምህረትና ይቅርታ አሰጣጡ ውስጥ ተካተው በተለያዩ ጊዜያት ከእስር እንዲፈቱ ተደርገዋል:: የጠ/ሚኒትሩን ሹመት ተከትሎ እስከ 2011 ዓ.ም ዘመን መለወጫ ድረስ በተለያየ ዙር በቃሊቲና ቂሊንጦ፣ዝዋይና ሸዋሮቢት ማረሚያ ቤቶች ይገኙ የነበሩ ብዙ የአማራና የኦሮሞ ተወላጆችም የፍርድ ውሳኔያቸው እየተሻረ፣ ክሳቸው እየተቋረጠ ነጻነትን ሲቀዳጁ ተመልክተናል::

እስከ ጥቅምት 30 ድረስ በቆየው ልዩ የይቅርታ አሰጣጥም እንዲሁ ዜጎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከእስር ተፈትተዋል:: የለውጡ ቡድን ይዞት የመጣው የይቅርታና የመደመር መንፈስ ለሁሉም ዜጋ በረከት መሆኑ ባያጠራጥርም በሕግ አስፈፃሚዎች በኩል ግን የተለያዩ ክፍተቶች ታይተዋል:: የገቢዎችና ጉምሩክ ም/ዳይሬክተር የነበሩት እና አቶ ገብረዋህድ እና ዝነኛ የሀገራችን ባለሀብቶችን በይቅርታ የለቀቀው የፍትሕ ሥርዓት፣ የይቅርታ ቦርዱና አጋር ተቋማት ጥቂት ግለሰቦች ብቻ ተነጥለው ከተመሳሳይ የክስ ባልደረቦቻቸው ውጭ በሆነ መልኩ ፍትሕን እንዳያገኙ ሲደረጉ ለምን? የሚል ጥያቄ አለመቅረቡ ሥልጣን ላይ ላለው መንግሥት በዙሪያው ብዙ እንቅፋቶች እንደተሰገሰጉበት አመላካች ድርጊት ሆኖ ታይቷል::

በተለይም ከስምንት ዓመት እስር በኋላ በይቅርታ ተለቀው የነበሩትና ከተፈቱ ከአስር ቀን በኋላ ከመንገድ ታፍነው የታሰሩት፣ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት እንደ ዕቃ በአደራ ይቀመጡ የተባሉት አዛውንቱ አቶ ከበደ ተሠራ በርካታ ግለሰቦች በይቅርታ ሲፈቱ እሳቸው ግን ሆን ተብሎ ለአራትና አምስት ዙሮች ከይቅርታው መዘለላቸው፣የፍትሕ ሥርዓቱን ከሕወሓት ተፅዕኖ ያልተለቀቀ፣አልያም ለሌላ ነገር የተጋለጠ ነው የሚል ግምት በብዙዎች ዘንድ እንዲፈጠር አድርጓል:: ግለሰቡ ያለአግባብ ሊያጠቋቸው በሚፈልጉና ሀብታቸውን በተቀራመቱ ቡድኖች ቀጥተኛ ተፅዕኖ ግፍ እየተፈፀመባቸው መሆኑን በርካታ መገናኛ ብዙኃን (በተለይ የነፃው ፕሬስ ውጤቶች) በተደጋጋሚ ከመግለፃቸው ባሻገር የተሰራባቸውን ሸፍጥ በሙሉ ለኅብረተሰቡ አሳውቀዋል::

ለቲም ለማ፣ ለጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እንዲሁም ዜጎች ትክክለኛ ፍትህን እንዲያገኙ ለሚደክሙና ለውጥ ናፋቂ ሆነው በአዲስና ትክክለኛው መንገድ ብቅ ላሉ የሕግ አስፈፃሚዎች እንዲሁም ለይቅርታ ቦርድ ምስጋና ይግባና በመጨረሻ እኚህ አዛውንት ከብዙ እንግልትና ስቃይ በኋላ ድምፃቸው ተሰምቶ፣ ታህሳስ 27 ቀን 2011 ዓ.ም ከአስር ተፈትተዋል:: በአጠቃላይ ለዐሥር ዓመት ያህል (ጥቂት ወራት ቢቀሩትም) የታሰሩትን አቶ ከበደ ተሰራን አስመልክቶ ግዮን መጽሔት ከዚህ ቀደም ከቤተሰቦቻቸውና ከሕግ ባለሙያው አቶ ታምሩ ወንድማገኘሁ ጋር ልዩ ቃለ ምልልስ በማድረግ በቂ መረጃ ለአንባቢያ ማድረጓ ይታወቃል::

# አዲስ አበባ ላይ የሚደመሩት መቀሌ ላይ የሚቀነሱት ደብረጺዮን

*ተስፋዬ ሽብሩ*

የምስራቅ አፍሪቃ አገራት የሆኑት ኢትዮጵያና ኤርትራ ወደ ቀድሞ ግንኙነታቸው ከተመለሱ የመንፈቅ ዕድሜ አስቆጥረዋል:: በነዚህ ጥቂት ወራቶች ግንኙነታቸውን ወደላቀ ደረጃ ለማሳደግ ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ::የሁለቱ አገራት ግንኙነት ፈር ይዞ ሕጋዊ ሥርዓት ተበጅቶለት መካሄድ እንዳለበት በርካታ ምሁራን አስተያየት ሲሰጡበት ከርመዋል:: እርግጥ ነው ምሁራኑም ሆኑ ሌሎች የፖለቲካ ተንታኞች ውትወታቸው ተገቢነት ያለው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም:: አገራቱን ወደ ጦርነት የከተታቸውና ከሁለቱም ወገን ለብዙ ሺህ ወጣቶች ሕይወት መቀጠፍና በቢሊዮኖች ለሚገመት የንብረት ውድመት ምክንያት የሆነው ፈሩን የሳተ ግንኙነታቸው እንደነበር አይዘነጋም::

ከ20 ዓመት በኋላ አዲስ ለተጀመረው ግንኙነት ሕጋዊ ሥርዓት እና ገዢ የሆነ ሕግ ይበጅለታል የሚል እሳቤ እንዳለ ይታመናል:: የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ከሕወሓት መራሹ መንግሥት የተሻለ ትምህርት በማግኘት ግንኙነቱን የሰመረ ያደርገዋል ተብሎ ይጠበቃል:: ጠ/ሚኒስትር ዐብይ በአገራቱ መካከል የተጀመረው ግንኙነት በኤፌሴላዊ የስምምነት ማእቀፍ ውስጥ እንዲሆን የጋራ ኮሚቴ ተዋቅሮ እየተሰራ መሆኑን መናገራቸው ፣ይህንኑ አመላካች ነው::

እንደታሰበው ግንኙነቱን የሰመረ ለማድረግ ቀላል ነው ማለት ግን አይቻልም:: የሕወሓት ኤርትራ ግንኙነት፤ የሕወሓት ከፌደራሉ መንግሥት የመራቅ አዝማሚያ እና ሌሎች ሊገመቱ የማይችሉ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ነገሩን ወደ ኋላ ሊጎትቱትና አሉታዊ ጥላ ሊያጠሉበት እንደሚችሉ ይገመታል:: “በፖለቲካ ዘላቂ ወዳጅና ዘላቂ ጠላት የለም” የሚሉት የዲፕሎማቶች ይትበሃልም፣ ሊታወስ ይገባል::

አገራት በግንኙነታቸው ሳቢያ ሕዝብና መንግሥታቱ የጋራ ጥቅም (mutual benefit) ሊያተርፉበት ይገባል::ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ባላት ግንኙነት ምን ታተርፋለች? ኤርትራስ ከኢትዮጵያ ጋር ባላት ግንኙነት ምን ትጠቀማለች? የሚለውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጥቅሞቻቸውን ማስላት ግድ ይላል::

ሰሞኑን ለ20 ዓመታት ገደማ ተዘግቶ የነበረው የሁመራ ኦማህጃር ድንበር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ በተገኙበት ተመርቆ ተከፍቷል:: በምረቃው ላይ የአማራ እና የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ርእሰ መስተዳድራን አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ዶ/ር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል ጨምሮ የአገር መከላከያ ጠቅላይ ኢታማጆር ሹም ጄነራል ሰዓረ መኮንን ተገኝተዋል:: በኤርትራ በኩል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኦስማን ሳልህ ፤ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ አማካሪ አቶ የማነ ገብረ አብ እና የኤርትራ ሠራዊት የምስራቅ እዝ አዣዥ ብርጋዴር ጀነራል ተክሌ ክፍላይ ተገኝተው ነበር::



የኢትዮጵያና ኤርትራ ባለስልጣናት በኦምሃጃር-ሁመራ ድንበር ሲከፍቱ

የድንበሩ መከፈት የሁለቱ አገራት የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ይበልጥ ከማጠናከር በተጨማሪ በሂደት የድንበር ተሻጋሪ የንግድ እንቅስቃሴን ያቀላጥፋል ተብሏል:: በኤርትራ በኩል በተሰንኤና ጋርሴት፤ በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ በኦምናሃጃር-ሁመራ ድንበር እየተካሄዱ ያሉ የልማት ፕሮጀክቶች በኢትዮጵና ኤርትራ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የሚደረገው ጥረት አካል መሆናቸው ተገልጿል::

የድንበሩን መከፈት አስመልክቶ ታዋቂው የኤርትራ ፕሬስ ድረገጽ የሚከተለውን ቁምነገር አስፍሯል:: “በማሳረጊያው ደብረጺዮን ተደመረ፤የወያኔ ደጋፊዎች የአደጋ ምልክት እየበራባቸው ነው::ደብረጺዮን የሁመራ ድንበር መከፈትን ተከትሎ ከአማራ ክልል መስተዳደር ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው ፎቶ መነሳታቸው በሕወሓት መንደር መጠነኛ ጫጫታ ፈጥሯል::የመሪያቸውን በጎ ጅምር በማንቋሸሽ ጉዳዩን ከኤርትራው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ ስውር ተጽእኖ ጋር ለማያያዝ ሞክረዋል::በትግራይ ኦፌሴላዊ ገጽ ላይ የድንበሩን መከፈት በይፋ የሚኮንኑ ጽሑፎች ናቸው በስፋት የተንሸራሸሩት ::”

በዚሁ ገጽ ላይ የድንበሩ መከፈት ኤርትራዊያን ላይ የፈጠረው የመነቃቃት መንፈስ ተንጸባርቋል፤ “የጎንደር-ኦመጀሀር ተሰኔ መንገድ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን ለማጠናከር ይረዳል::የዚህ መንገድ መከፈት ኤርትራን በጤፍ እና በስንዴ ምርቶች ከሚታወቁት ከአማራ ከተሞች ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ በመሆኑ ፋይዳው የላቀ ነው:: ”

## የሕወሓት ካድሬዎች ጫጫታ

ጠቅላይ ሚንስትሩ የሁለቱን ክልሎች ርዕሰ መስተዳድራን አስከትለው ወደ ኦምናሀጀር ባደረጉት ጉዞ የሕወሓት ካድሬዎች ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድንና አቶ ገዱ አንዳርጋቸውን በስም እየጠሩ “ሌባ” በማለት ሲንጫጩ ተስተውሏል:: የካድሬዎቹ ጫጫታ እና ለቅሶ ብዙም የሚያስደንቅ አይደለም፤ የሚጠበቅ እንጂ:: ለዘመናት ሲዘርፉና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲገድሉ የኖሩት አለቆቻቸው መውጫ መግቢያ ጠፍቷቸው አንገታቸውን ደፍተው በመቀሌ ተሸሽገው እንደሚገኙ የሚያውቁት እነዚህ ካድሬዎች የሚሰሩትን የሚያውቁ አይመስሉም:: ከአለቆቻቸው የወረደላቸውን ቀኝን ትዕዛዝ ሳያላምጡ በመትፋት፤ ኢትዮጵያን የታደጓትን ጀግኖች ሊያዋርዱ ሞክረዋል:: ጨዋውን የትግራይ ሕዝብ ደጋግመው ገድለውታል፣ አዋርደውታል:: በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ባዶ ጫጫታ ያሰሙት የሕወሓት ተላላኪ ካድሬዎች የሌብነት ትርጉም የተዛባባቸው የአእምሮ ሕሙማን ወይም ዐይን ያወጡ አስመሳዮች ከመሆን ያለፈ ቦታ የሚሰጣቸው አይደለም:: ሌብነትንና ዝርፊያን ከአለቆቻቸው በላይ ማን ሊነግራቸው ይችላል?

የትግራይ ጭቁን ገበሬ ዛሬም ድረስ በድህነት የሚጠበሰው እኮ ሕወሓት ውስጥ ባሉ ጥቂት ስብስቦች እንደሆነ የትግራይ ሕዝብ አይስተውም:: ለ27 ዓመታት ሥልጣንን ▶

◀ተቆጣጥሮ የኖረ አካል የሚመራውን ሕዝብ ሰቆቃ ማየት እንደተሳነው በተደጋጋሚ ተነግሯል:: ዶ/ር ዐቢይን በሌብነት መጠርጠር አለቆቻቸው ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ አለማየት ይሆናል:: ለነገሩ የዘረኝነት በሽታ የተጠናወተው ቡድን ነገሮችን የሚያየው ሸውራራ በሆነው የዘረኝነት መነጽር ስለሆነ መፍረድ ያስቸግራል:: የትግራይ ደሀ ሕዝብ ለጊዜው ቢታገስም ዐይኑን የገለጠ ቀን ሌቦቹና ነፍሰ ገዳዮቹ ምድር ተከፍታ ብትውጣቸው የሚመርጡበት ቀን ይመጣል::

## የማይጨበጡት ዶ/ር ደብረጽዮን

የትግራይ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር የሆኑት የዶ/ር ደብረ ጽዮን ገ/ሚካኤል ጉዳይም አወዛጋቢ እንደሆነ ቀጥሏል:: ዶ/ር ደብረፅዮን እነ ዶ/ር ዐብይን ሲያገኙ ይደመራሉ ወደ መቀሌ ሲመለሱ ደግሞ ይቀነሳሉ::ርዕሰ መስተዳድሩ እንደ ፔንዱለም ማዶ ለማዶ የሚላጋ አቋም አላቸው ብለው የፖለቲካ ታዛቢዎች ጊስ ያቀርቡባቸዋል:: ባለ ሁለት ፊቱ ደብረጽዮን እንዲህ ዓይነት አጣብቂኝ ውስጥ የገቡት በተለያዩ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል::

ጠቅላይ አቃቤ ሕጉ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ክልሉ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የወጣባቸውን በሌብነትና በሰብዓዊ መብት ጥሰት የተጠረጠሩትን የቀድሞ የደህንነትን መስሪያ ቤት ዳይሬክተር ጌታቸው አሰፋንና ሌሎችንም ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆኑን እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መናገራቸው ይታወሳል:: ተጠርጣሪዎቹ በመቀሌ መክተማቸውን የተናገሩት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊው እነርሱን ለመያዝ መሳሪያ መተኮስ አስፈላጊ አለመሆኑንም ኃላፊነት በተሞላው መልኩ ተናግረዋል::

ይህንን ሁሉ ሕጋዊ ጥያቄ የሰሙትና የሚያውቁት ዶ/ር ደብረጽዮን "የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ" በሚል ዝምታን መርጠዋል:: አንዳንድ ጊዜም ለተጠርጣሪዎች መከላከል በሚመስል መልኩ ግራ የተጋባ አስተያየት ሲሰጡ ይደመጣሉ:: ጉዳዩ ከሕጋዊ መፍትሄ ይልቅ ፖለቲካዊ መፍትሄ እንዲሰጠው የሚፈልጉት በመቀሌ የመሸጉት የሕወሓት አባላት ለዓመታት ለፈፀሙት የክፋት ድርጊት ከሕጋዊና የተፋጠነ ተመጣጣኝ ቅጣት ውጪ ሊሆኑ እንደማይችሉ ሊረዱት ይገባል:: የኢትዮጵያ ሕዝብም የሚጠብቀው ፍትህ ይህን ነው:: የሕግ የበላይነት ተከብሮ አጥፊዎች ከህግ በታች ሲንበረከኩ ማየት የዘውትር ምኞቱ መሆኑን ለአፍታ መዘንጋት አይቻልም::

ጠ/ሚኒስትር ዐቢይም ሆኑ ሌሎቹ የለውጡ ኃይላት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ እያሳዩት ያለውን የማስመሰል ጨዋታ ጠንቅቀው ይረዱታል፤ አስታመው የያዙበት መንገድም ለጊዜ ጥሩ ይመስላል:: ፕሬዚዳንቱ በያዙት የማስመሰልና የሚዋልል የፖለቲካ ጨዋታ የት ድረስ ይጓዙ ይሆን? ጠ/ሚኒስትር ዐቢይስ አሁን በያዙት የማስታመምና የማባባል መንገድ እስከ መቼ ይጓዙበታል? የሚለው የብዙ ፖለቲካ ተንታኞች ጥያቄ ነው::

## ከሰራዊቱ ጋር የተፈጠረው ትንቅንቅ

ከሁለቱ አገራት መልካም ግንኙነት በኋላ የኢትዮጵያ መንግሥት በድንበሩ ዙሪያ የሰፈሩ ሠራዊቱን እና መሣሪያዎችን ማንቀሳቀስ መጀመሩን ተከትሎ በቦታው ውጥረት ነግሶ ሰንብቷል:: ሰሞኑንም ይኸው ውጥረት አገርሽቶ በድንበሩ አካባቢ በተለይ በሽሬ የሚገኙ ነዋሪዎች መንግሥት የወሰደውን እርምጃ በመቃወም ተሽከርካሪዎቹ እንዳይንቀሳቀሱ ሲያስተጓጉሉ ተስተውሏል:: እነዚህ የአካባቢው ነዋሪዎች ድርጊቱን የሚፈጽሙት በሕወሓት የተንኮል ሴራ ተጠምደው ይሁን የዋህ በሆነ ፍራቻ ምክንያት ለጊዜው የታወቀ ነገር ያለ አይመስልም::

ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ መንግሥት ቀደም ሲል በጠቅላይ ሚኒስር ዐቢይ አሕመድም ሆኑ የመከላከያ ምክትል ኤታማጆር ሹም ኃላፊው ብርሃኑ ጁላ ሰሞኑን ለተወካዮች ምክር ቤት ባቀርቡት የመሥሪያ ቤታቸው የ6 ወር ሪፖርት፤ የፌደራል መንግሥት ያለማንም ጣልቃ ገብነት መከላከያ ሠራዊትንም ሆነ ተሽከርካሪዎቹን በፈለገው ጊዜ የማንቀሳቀስ ፍፁማዊ ሥልጣን እንዳለው አስረድተዋል::

የትግራይ ክልል ም/ርእሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል ጥር 1 ቀን 2011 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ የመከላከያ ሠራዊት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ሕጋዊ እና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችል ነው ብለዋል:: የሕገ መንግሥት ይከበር ጥያቄ የሚጀምረው እራስ ከማክበር መሆኑንም ጠቅሰዋል::



*አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ዶ/ር ደብረጽዮን ገ/ሚካኤል በኦምሃጀር-ሁመራ ድንበር*

## የሁለቱ አገራት ግንኙነት የመሪዎች ብቻ?

የቀድሞ የሕወሓት አመራር አባላት ሜጀር ጄነራል ፃድቃንም ሆኑ አቦይ ስብሃት እንዲሁም አሁን በስልጣን ያሉት አንዳድ የሕወሓት አመራሮች የኢትዮጵያ መንግሥት ከኤርትራ መንግሥት ጋር የጀመረውን ግንኙነት በበጎ ዓይን የሚመለከቱት አይመስልም:: እንደውም ከመንግሥታትና ከሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት አውርደው የሁለት መሪዎች ግንኙነት ነው እስከማለት የደረሰ ደፋርና ሁኔታውን ያላገናዘበ አስተያየት ሲሰጡ እየተደመጠ ነው::


እየሆነ ያለው ነገር ግን እነርሱ እየሰጡት ካለው በተቃራኒ ነው:: የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በተለይ ደግሞ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የጠበቀ የሥነ ልቦና፣የባህል እና የታሪክ ቁርኝት አለው:: ይህም ግንኙነት ድንበሩ በተከፈተበት ቅጽበት የአገራቱ መንግሥታት ባሳለፉት ውሳኔ ምን ያህል እንደተደሰቱ የታየ ሀቅ ነበር::

ሌላው የሚያስገርመው ነገር የሁለቱ አገራት ግንኙነት ዳግም ሲጀመርና ድንበሮች በየጊዜው ሲከፈቱ የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶ/ር ደብረጽዮን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ ጋር መገኘታቸው ነው:: ቀድሞም ሆነ አሁን ግንኙነቱ ከፍተኛ የሆነ ደስታ እንደሰጣቸው በመጥቀስ መናገራቸውን ማስታወስ ይገባል:: አሁንም በአምሃጆር ሁመራ የመንገድ መከፈት ባደረጉት ንግግር ለሁለቱ አገራት ሕዝቦችና ለትግራይም ሕዝብ መልካም የንግድና የማኅበራዊ ትስስር ይፈጥራል ነበር ያሉት:: የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ጉዳይ አድርገው ለማሳነስ የሚሞክሩት ይህ ግንኙነት ራሳቸው በአፋቸው የመሰከሩት ሐቅ እንደሆነ በተደጋጋሚ ከተናገሩት ንግግር መረዳት ይቻላል::



ብሩክ መኮንን

# ኢትዮጵያዊው የነጻነት ታጋይ ሐኪም



የሕክምና ባለሙያ ዶ/ር መላኩ በያን

ከአገራችን ነጻነት አንድነትዋ መጠበቅና ለዳር ድንበሯ መከበር ታግለው አያሌ መስዋዕትነት የከፈሉ፣ በተለያዩ ሙያዎች ተሰማርተው ያገለገሉ አያሌ ብሔራዊ ጀግኖች አሉ። የእነዚህ ብሔራዊ ጀግኖች ሕይወት፣ እምነት እና ተግባር ለቀጣዩ ትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ በትውልድ ቅብብሎሽ ተተኪዎችን ለማግኘት ያስችላል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሥራቸው እና ያራምዱት የነበረው አቋም እምብዛም የማይታወቅ ነገር ግን በዓለም አቀፋ ደረጃ በፓን አፍሪቃ ርዕዮት አራማጆች፣ በአፍሪቃ አሜሪካውያን ዘንድ የሚታወቁት ኢትዮጵያዊው የነጻነት ታጋይና የሕክምና ባለሙያን ዶ/ር መላኩ በያን ሕይወትና ሥራን የቃኘንበትን ጥንቅርን እንዲህ አቅርበነዋል።

መላኩ በያን በቀድሞው ወሎ ጠቅላይ ግዛት ሚያዚያ 21 ቀን 1892 ዓ.ም ከግራዝማች በያን እና ከወይዘሮ ደስታ ነበር ይህቺን ምድር የተቀላቀለው።ገና በልጅነቱ ወደ ሐረር ተወስዶ፣ የዚያን ጊዜው የሐረርጌ ገዢ በኋላም አልጋወራሽና የኢትዮጵያ ንጉሠነገሥት በሆኑት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግቢ ተላላኪ ሆኖ አደገ።

መላኩ በሐረር በሚገኘው የደጃዝማች ተፈሪ መኮንን በኋላ ላይ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መኖሪያ ግቢ በተላላኪነት እያገለገለ፣ በጊዜው ይሰጥ የነበረውን የቤተክህነት ትምህርት በመከታተል መጻፍና ማንበብ ቻለ። ትምህርት ለመማር ያለውን ተነሳሽነት እና አስተዋይነቱን በቅርበት ያውቁ የነበሩት አልጋ ወራሹ ራስ ተፈሪ መኮንን መቀመጫቸውን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ እንዲዛወር አደረጉት።

አልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን የተለያዩ የአውሮጳ ሀገራትን ለመጀመሪያ ጊዜ ጎብኝተው ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱ ብዙም ሳይቆዩ ወደ ተለያዩ ሀገራት ለትምህርት ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን መላክ የጀመሩት የዚሁ ዕድል ተጠቃሚ ከሆኑት አንዱ መላኩ ነበር።

ለትምህርት ወደ ባህር ማዶ ለመላክ ያስቻለው አጋጣሚን በተመለከተ መላኩ እንዲህ ሲል ነበር የገለፀው ፡አንድ ቀን አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኮንን ፊታቸው በፈገግታ ተሞልቶ ጠሩኝና ‹‹መላ ወደ አውሮፓ ለትምህርት ብሰድህ ምን ይመስልሃል›› ሲሉ ጠየቁኝ፡

‹‹ጌታዬ እርስዎ ካሰቡልኝ እኔ ፈቃድዎን እፈፅማለሁ›› አልኳቸው

‹‹ከነወርቁ ጎበና በሻጎ ውረድ ሀብተወልድ ጋራ ትሄዳላችሁ ጥራቸው›› ብለው አዘዙኝ

አልጋወራሹ መላኩን የሕክምና ትምህርት እንዲማር እንደሚፈልጉ ገልፀው እሱንና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን የእንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲማሩና ለቀጣዩ ከፍተኛ ትምህርት ዝግጁ እንዲሆኑ በመጀመሪያ ወደ ሕንድ ተላኩ።

በሕንድ ትምህርቱን መከታተል የጀመረው መላኩ እና ሌሎች ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በወቅቱ የእንግሊዝ ቀኝ ግዛት የነበረችው ሕንድ በሚያዩት የእንግሊዛውያን ፈር የለቀቀ የበላይነትና ዓለም በእንግሊዝ መንግሥት ቁጥጥር ስር እንደሆነች ተደርጎ የሚነዛው ፕሮፓጋንዳ አላስደሰታቸውም። በሚማከሩበት ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ እንግሊዛውያን፣ ኢትዮጵያም ብትሆን በእንግሊዞች ኃይል መዳፍ መደቆሰዋ አይቀሬ ነው እያሉ በነመላኩ ላይ ሰፊ የሥነ ልቦና ተፅዕኖ ያደርሱባቸው ነበር።

ይህ የመምህራኑ ድርጊት ያስቆጣቸው መላኩ እና ጓደኞቹ በሕንድ መቆየት ስላልፈለጉ ጓዛቸውን ሸክፈው ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ወሰኑ።

እነ መላኩ በያን መሳሪያቸውን ለኢትዮጵያዊ አልጋወራሽ ለተፈሪ መኮንን አሳወቁ። አልጋወራሹ የእነመላክ በያንን ውሳኔ በመቀበል ወጣቶቹ ወደ አሜሪካ ተጉዘው በዚያ የከፍተኛ ትምህርት እንዲከታተሉ ሽኝ ደብዳቤና የገንዘብ ድጋፍ ሰደውላቸው ወጣቶች ወደ አሜሪካ እንዲያቀኑ አደረጉ።

አሜሪካ የደረሱት መላኩ እና ጓደኞቹ በወቅቱ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዋረን ሀርዲንግ ፊት በመቅረብ ከአልጋወራሹ የተላከላቸውን ደብዳቤ ሰጥተዋል።ፕሬዚዳንቱ ደብዳቤውን ከተቀበሉ በኋላ በነበራቸው ቆይታ ▶

ኢትዮጵያውያን ለከፍተኛ ትምህርት ለመማር ወደ አሜሪካ መምጣጣቸውን ሲሰሙ ራሳቸው የተማሩበት በኒውኮንኮርድ አሀዮ በሚገኘው መስክንግሃም ኮሌጅ እንዲገቡ ሁኔታዎችን አመቻቸላቸው።

መላኩ እና ሁለቱ ጓደኞቹ ወደዚህ ኮሌጅ በማምራት የሁለተኛ ደረጃ የኮሌጅ ትምርታቸውን ተከታተሉ። በ1925 ዓ.ም መላኩ በኬሚስትሪ የመጀመሪያ ዲግሪውን አገኘ በመቀጠልም በአሀዮ ዩንቨርስቲ ለአንድ ዓመት ትምህርቱን ሲከታተል ከቆየ በኋላ ወደ ዋሽንግተን በመዛወር በዚያ በሚገኘው የሐዋርድ ዩንቨርስቲ በመግባት ትምህርቱን መከታተል ቀጠለ።

መላኩ ከትምህርቱ ሌላ በወቅቱ በአሜሪካ እና በመላው ዓለም ነግሶ በነበረው የቀለም ልዩነት፣ የዘር መድሎ ሰለባ የሆኑ የጥቁር ሕዝቦች ላይ የሚደርሰውን ግፍ በደል ያስቆጨው ለእነዚህ ወገኖች በተለያየ መንገድ ድገፋን አጋርነቱን ያሳይ ነበር።

በሀዋርድ ዩኒቨርስቲ የሕክምና ትምህርቱን እየተከታተለ እያለ በኢትዮጵያ በየሳምንቱ ይታተም በነበረው የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ የተለያዩ መጣጥፎችን በመላክ ይታተምለት ነበር።ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ተሰማርተው የኢትዮጵያን መንግሥት ለማገልገል ፍቀደኛ የሆኑ አፍሪቃ አሜሪካውያን ባለሙያዎችን ወደ ኢትዮጵያ ይልክ ነበር።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ የብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴን ልጅ ለማግባት አጭቶ የነበረው መላኩ በያን አፍሪቃ አሜሪካዊቷን ወይዘሪት ድሮቲ ሄድሊን በ1931 ዓ.ም አግብቶ ትዳር መሰረተ።

ለአራት ዓመታት ሲከታተለው የነበረው የሕክምና ትምህርት አጠናቆ በ1935 ዓ.ም የሕክምና የዶክትሬት ዲግሪውን ከክብር ጋራ በማግኘት በአሜሪካ ዩኒቨርስቲዎች ታሪክ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ በመሆን ስሙን ማስፈር ቻለ።

ዶክተር መላኩ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ ነበር ሚስቱን የመጀመሪያ ልጁን ይዞ ወደ ሀገሩ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው፡ ፡ መላኩ ወደ ሀገሩ ሲመለስ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያ የወረረችበት ወቅት ነበር። በጊዜው ሀገርን ከጠላት ወረራ ለመመከት ሲደረግ የነበረ የጦርነት ዝግጅት ድጋፍና እርዳታ በማሰባሰብ ንቁ ተሳታፊ ነበር። ዶክተር መላኩ በአሜሪካ ካሉ ባልንጀሮቹ ጋራ በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች በርካታ አፍሪቃ አሜሪካውያን ከኢትዮጵያ ጦር ጋራ ተሰልፈው ለመዋጋት ፍቃደኝነታቸውን በማሳየት በመመዝገብ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተንቀሳቅሰዋል።

የኢጣልያ ጦር ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በመዝለቅ በሦስት ግንባሮች የከፈተው ፍልሚያን ለመመከት ወደ ማይጨው የዘመቱት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የግል ሐኪምና ልዩ ረዳት በመሆን መላኩ ዘመተ፡ ፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከጦርነቱ በኋላ በአሳተሙት የሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ በተሰኘው መጽሐፋቸው ዶክተር መላኩ በጦርነቱ ወቅት ከጎናቸው ሳይለይ ሊያገለግላቸው እንደነበር አውስተዋል።

በማይጨው ላይ በደረሰው ከፍተኛ ጉዳት የኢትዮጵያ ጦር ወደ ኋላ ማፈግፈግ መበተንን ተከትሎ የፋሽስት ጦር በአውሮፕላን በመጠቀም በሚያዘነበው የመርዝ ጋዝ ጥቃት የተነሳ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ሀገራቸውን ለቀው ወደ እንግሊዝ ሀገር በመሰደድ በዚያ የዲፕሎማሲ ትግል ለማካሄድ ሲወስኑ ዶ/ር መላኩ ወደ አሜሪካ ተመልሶ በመሔድ የአሜሪካውያንን ድጋፍ ለማግኘት ሁኔታዎችን እንዲያመቻች ጠይቀውት ነበር።

ዶ/ር መላኩ እሳቸው በነበሩበት ሁኔታ ሊለያቸው ፍቃደኛ ባለመሆን አብሯቸው ወደ እንግሊዝ ሀገር አመራ። በእንግሊዝ ሀገር ኃይለ ሥላሴ የስደት ሕይወታቸውን መኖር ከጀመሩ በኋላ ከረዳቶቻቸው ከአቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ከአቶ ሎሬንሶ ትዕዛዝ መብራቱ ከሌሎች ባደረቦቻው ጋራ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ካረጋገጠ በኋላ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልዩ መልዕተኛ በመሆን ለኢትዮጵያ ድጋፍ የማሰባሰብ ኃላፊነት ትዕዛዝ ተስጥቶት ከነቤተሰቡ ወደ አሜሪካ ተጓዘ።

ዶ/ር መላኩ አሜሪካ ሲደርስ በኒውዮርክ በርካታ አፍሪቃ አሜሪካውያን ተሰብስበው አቀባበል አድርገውለት ነበር። በመላኩ እና ለቤተሰቡ እንዲያርፉበት በቅድሚያ ተይዞላቸው የነበረው የኒውዮርኩ ዲላኖ ሆቴል በቆዳ ቀለማቸው ምክንያት ተቀብሎ ሊያስተናግዳቸው ፍቃደኛ ባለመሆኑ ወደ ሌላ የግል ማረፊያ ቤት ለመዘዋወር ተገደዱ።

በአሜሪካ ያለው የቀለም የዘር መድሎ እንዲህ መባባሱ ያስገረመው በእንቅስቃሴው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ቢያደርሱበትም ዶ/ር መላኩ እና ጓዶቹ በአንድ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ‹‹ዩናይትድ ኤይድ ቱ ኢትዮጵያ ኤንድ ፒፕልስ ኦፍ አፍሪቃን ዲሴንት›› ቡድን በሀርለም ሮክላንድ ፓላስ ሶስት ሺኅ ሕዝብ የታደመበት ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ አዘጋጁ።

በስብሰባው ላይ በመገኘት ዶ/ር መላኩ ንግግር እንዲያደርግ ሁኔታዎችን ያመቻቹት የቡድኑ አመራሮች የዶክተሩ ንግግር ለማድመጥ የታደመው ታዳሚ ገንዘብ እየከፈለ እንዲገባ ያቀረቡት ሐሳብን መላኩ፣ የለም እኔ ለንግግሬ ገንዘብ አላስከፍልም በሚል ተቃወመ።

የገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያስችለው አማራጭ ሐሳብንም ዶክተር መላኩ ያቀረበ ሲሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አፄ ኃይለ ስላሴ የፈረሙባቸው የአፄ ኃይለ ስላሴ የፎቶግራፎችና የኢትዮጵያ ቴምብሮችን ይዘው መምጣታቸውን እነርሱን በሽያጭ በማቅረብ ገንዘብ ማሰባሰብ እንደሚቻል ያቀረበው ሐሳብ ተቀባይነት አገኘ።

የሀርሊሙ የሮክላንድ ፖሊስ ሕዝባዊ ስብሰባ መካሄዱን ተከትሎ በዶ/ር መላኩ አስተባባሪነት የኃይለ ሥላሴ ፈንድ የእርዳታ ማሰባሰቢያ ፎረም ተመሰረተ።

ይህ የገቢ አሰባሰብ አካል በእንግሊዝ ሀገር በስደት ያሉት አፄ ኃይለ ሥላሴ እና ቤተሰባቸው ለኑሯቸው የሚበቃ ገንዘብ እንደሌላቸው ስለሚታወቅ እሳቸውን እና በኬኒያ፣ በጅቡቲ ፣በሱዳን እና በኢየሩሳሌም በስደት ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ በሀገር ውስጥ የሚካሄደውን የኢጣልያ ጦር ላይ የሚሰነዘረውን የሽምቅ ውጊያ የሚካሄዱ ተዋጊዎችን መርዳትን ዓላማው ያደረገ ነበር።

በዶ/ር መላኩ አስተባባሪነት የተዋቀረው የኃይለ ሥላሴ የእርዳታ ማስተባበሪያ ፈንድ እንቅስቃሴ እጅግ የተገደበና ከአሜሪካ መንግሥት ሕግ ጋራ እንዳይጣረስ በጥንቃቄ ነበር ሲንቀሳቀስ የቆየው።

ዶክተሩ በአሜሪካ ለአንድ ዓመት ያህል እንደቆየ የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ኅብረት የተሰኘ አዲስ ድርጅት በመመስረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ቅርንጫፎቹን በአሜሪካና በካሪቢያን ሀገሮች ለመክፈት ያስቻለ ውጤታማ እንቅስቃሴን ይመራ ጀመር።

ለዚህ የኢትዮጵያ ወርልድ ፌደሬሽን የተሰኘው ድርጅት ፋሽስት ኢጣልያ ጦር አዲስ አበባን ሲቆጣጠር በኢትዮጵያ የነበሩ ወደ መቶ የሚጠጉ አፍሪቃ አሜሪካውያን በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ አስገዳጅነት ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ እንዲመለሱ የተደረጉ ግለሰቦች ንቁ ተሳትፎ ያደርጉበት ነበር።

ዶክተሩ በፋሽስት ኢጣልያን በግፊ የተያዘች ሀገሩን ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የሚያደርገውን ትግል በመቀጠል በ1937 ዓ.ም የኢትዮጵያ ድምፅ ቮይስ ኢፍ ኢትዮጵያ የተሰኘ ጋዜጣ ማተም ጀመረ። ጋዜጣው የኢትዮጵያ ወርልድ ፌዴሬሽን ልሳን ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የጋዜጣው አርማ ‹‹ ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሄር ትዘረጋለች›› የሚል ነበር።

የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ የእለት ተዕለት ሥራን የዶክተር መላኩ ባለቤት ወይዘሮ ዶሮቴ በበላይነት ትመራው ነበር። ጋዜጣው ‹‹ ጠይቁን እንመልሳለን›› ኢትዮጵያን እናስተዋውቃችሁ›› ስለ ታዋቂ የአፍሪቃ አሜሪካውያን ግለሰቦች ሥራና ሕይወት የታሪክ አምድ የመጽሐፍ ግምገማ በወቅቱ በኢትዮጵያ ይካሄዱ ስለነበር የአርበኞች የነፃነት ተጋድሎ የአውደውጊያ ዜናዎች የሚያወሱ ዘገባዎች ይቀርቡበት ነበር።

የኢትዮጵያ ድምጽ ሶይስ አፊ ኢትዮጵያ ጋዜጣ በሁለት ሳምንት አንዴ የሚታተሙ ሲሆን ዋጋው እንደ ቦታው እርቀት ከሶስት ሳንቲም እስከ አምስት ሳንቲም ይሸጥ ነበር።

ከአያሌ አፍሪቃ አሜሪካውያን ጓዶቹ ጋራ የኢጣልያ ወረራ በተፈፀመባቸው አራት አመታት ከባለቤቱ ወይዘሮ ዶሮቲ ጋራ ያለ እረፍት የኢትዮጵያ ነፃነት ዳግም ይረጋገጥ ዘንድ ሲታገል ሲወጣና ሲወርድ የነበረው ዶክተር መላኩ በያን ገና በለጋ እድሜው በአርባ አመቱ ሜይ 4 ቀን 1940 ኒውዮርክ ውስጥ በኒሞኒያ በሳምባ ምች በሽታ ተይዞ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

አጼ ኃይለ ሥላሴ “ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ወቅት ሀገሩን ኢትዮጵያን እና እኛን ንጉሠ ነገሥቱን ለማገልገል መጥቶ ከእኛ ሳይለይ እስከ ማይጨው ዘመቻ በጦርነቱ የቆሰሉትንም ወታደሮች በትጋት ለመርዳት ፍላጎቱ ስለሆነ በቀዶ ጥገና ሕክምና የፈፀመው ብዙ አገልግሎት ተመልክተናል። ዶክተር መላኩ በያን ከጦርነቱ በኋላ እኛን ተከትሎ ወደ እንግሊዝ ሀገር መጣ። ከዚያም ወደ አሜሪካ ሄዶ ሀገሩን ለመርዳት በሚቻለው ሁሉ ያለገግል ጀመር….” ሲሉ በሕይወቴና ኢትዮጵያ እርምጃ በተሰኘ የግል ታሪክ መጽሐፋቸው ላይ አውስተውታል።

የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በኋላም ለኢትዮጵያዊው የነፃነት ታጋይ እና ሐኪም ለዶክተር መላኩ በያን መታሰቢያ በቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለ ሠላሴ ሆስፒታል የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል ውስጥ የአንደኛ ማዕረግ ሕሙማን መኝታ ክፍሎችን የያዘ ክንፍ በስሙ ተሰይሞለታል።

ዶክተር መላኩ በያን ከፈርጀ ብዙ ትግሉ እንቅስቃሴው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቢያርፍም የፈፀመው ታሪክ እና ተግባር ግን ለዘላለም በታሪክ ፊት ሕያው ነውና ከ79 ዓመት በኋላ እነሆ ዛሬ እንዲህ ዘከርነው።



ጥላሁን መሸሻ

# አዲስ አበባ

## ያረጠችው ከተማ

እሁን ከጊዜ ወደጊዜ እያደገችና እየሰፋች የምትሄደውን አዲስ አበባን አስረውና ተብትበው ከያዟት የመሰረተ ልማት ችግሮች እንዴት እንታደጋት? ነው የሐሳቡ መነሻ:: አዲስ አበባ ዱሮ ከነበረችበት በአስር ዕጥፍ ከዚያም በላይ ሳትሰፋ አትቀርም:: የመስፋቷ ሂደት በአሁኑ ጊዜ ወደላይም ወደጎንም ሆኗል:: ታላላቅና ረጃጂም ሕንፃዎች ተገንብተዋል፣ እየተገነቡም ናቸው:: መንገዶችና ቪላዎች በስፋትና በብዛት ተሰርተዋል፣ እየተሰሩም ናቸው:: በዚሁ መጠን ሰዎች ከየአቅጣጫው ወደከተማይቱ ይገባሉ፣ ይህ ወደፊትም ይቀጥላል:: በዚህ መልኩ የአዲስ አበባም ዕድገት ይቀጥላል፣ ሕንፃዎችዋና መንገዶችዋ ያለማቋረጥ ይሰራሉ፣ ሕዝቦችዋም በቁጥር፣ በዕውቀት፣ በባህልና በሳይንስ እያደጉ ይሄዳሉ:: ይህ ተፈጥሯዊ በመሆኑ ማንም ሊያቆመው የሚችል ኃይል የለም:: ይልቁንም አስተዳደሩ ከዚህ ዕድገት ጋር በተያያዘ የከተማይቱን የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ በተመለከተ ከዕድገቷ ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ የማሳደግ ረዕይ አለው ወይ? ለዚህስ በእቅድና በሙሉ ዝግጁነት እየሰራ ነው ወይ? ወይስ እንዲሁ እንደአሁኑ በግፊት፣ በጭቅጭቅና በሮሮ ይቀጥላል? እነዴትስ ነው ይህን የሚሊዮኖችን ጥያቄና ፍላጎት፣ በማያቋርጥ ሁኔታ የሚያድግ ፍላጎት ሊያሟላ የሚችለው? ነው ወይስ አዲስ አበባ ከዚህ በኋላ ወዴትም አትሄድም አርጣለች፣ የምትስፋፋበት መሬት የላትም ብለው ያስቡ ይሆን?

አዲስ አበባ እንደሰው አድጋ፣ አርጅታ አትሞትም እንጅ ማደጓንማ ምንም ኃይል ሊገድበው አይችልም:: የሰው ልጅ ያለው አማራጭ ከአካባቢው ጋር አብሮ ማደግና አብሮ መለወጥ እንጅ የተፈጥሮ ሂደትን ማቆም አይችልም:: የከተማ መፈጠር፣ ማደግና መስፋፋት የሥልጣኔ ውጤት ነው:: ከተሞች የሚፈጠሩት በግብርና ሕይወት ውስጥ የንግድና ልውውጥ ሥራዎች ሲፈጠሩና እየተስፋፉ ሲሄዱ ነው:: ከንግድና ከተማ መመስረት፣ ማደግና መስፋፋት ጋር ተያይዞ ኢንዱስትሪዎች ይፈጠራሉ፣ ይስፋፋሉ:: ሕዝቦችም ወደአዲሱና ዘመናዊው የሥልጣኔ ሕይወት ይሳባሉ፣ ይሄዳሉ:: ቀደም ሲል በቦታውና በአካባቢውም ይኖሩ የነበሩ በግብርና ይተዳደሩ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ወደ አዲሱ የከተማ ሕይወት መሳባቸው አይቀሬ ነው፣ አለበለዚያም ባሉበት ይከስማሉ:: ምክንያቱም ከነሱ በኋላ የሚመጣ ትውልድ አዲሱንና ዘመናዊውን ሕይወት ይከተላል እንጅ ወደኋላ አይሄድማ! ስለዚህ አዲስ አበባ ማደጓና መስፋፋቷ አይቆምም:: ሁሉም የዓለም ከተሞች ያደጉት እንደዚሁ በተመሳሳይ ሁኔታ ነው:: በዚህ ምክንያት በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ ገበሬዎች ሁሉ ወደፊት ወደከተሜነት ይለወጣሉ፣ አለበለዚያ ደግሞ ባሉበት ይከስማሉ:: ምክንያቱም

> **አዲስ አበባ እንደሰው አድጋ፣ አርጅታ አትሞትም እንጅ ማደጓንማ ምንም ኃይል ሊገድበው አይችልም። የሰው ልጅ ያለው አማራጭ ከአካባቢው ጋር አብሮ ማደግና አብሮ መለወጥ እንጅ የተፈጥሮ ሂደትን ማቆም አይችልም። የከተማ መፈጠር፣ ማደግና መስፋፋት የሥልጣኔ ውጤት ነው**

ልጆቻቸው ከተሜነትን ይመርጣሉ:: ስለዚህ ነው የአዲስ አበባን ዕድገትና መስፋፋት ማቆም የማይቻለው:: ይልቁንም መሪዎች፣ አስተዳዳሪዎችና ባለድርሻ አካላት ሁሉ ገበሬዎች ተፈናቀሉ፣ መሬታቸውን ተነጠቁ፣ ወዘተ እያሉ ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ የሚሆን ፕሮፓጋንዳ ከሚቀምሩና የሕዝብን እድገት መንገዱ ላይ እየቆሙ ከሚያደናቅፉ ራእይን ሰንቀው፣ ከሚመሩት ሕዝብ ቀድመው አመራር ይሰጡት:: ሕዝብ እርስ በርሱ የሚጣላውና የሚፋጀው ራእይ ያለው መሪ ሲያጣና ወደፊት መሄድ ሲያቅተው፣ እድገቱም ባለህበት እርገጥ ሲሆን ነው:: ስለዚህ ታላቋ ከተማችን አዲስ አበባ ባለራእይ መሪ ይስጣት ብለን እንፀልያለን::

ስለዚህ መሰረተ ልማትን በሚመለከት የአዲስ አበባ መሪዎችና አስተዳዳሪዎች ስለእድገቷ፣ ስለመሰረተ ልማቷና ዘመናዊነቷ ብዙ ሊያስቡና ትልቅ ባለራእይ ሊሆኑላት ይገባል:: ዘመናት በተቀያየሩ ቁጥር ከተማዋም እየተለወጠችና እያደገች ትሄዳለች:: አምና የነበረው ዘንድሮ እነደነበር አይሆንም:: ቁጥር ይጨምራል፣ ፍላጎት ይጨምራል፣ አስተሳሰብ ይጨምራል፣ ሁሉም ነገር በዓይነትም ሆነ በመጠን እጨመረና እያደገ ይሄዳል:: በጊዜና በቦታ መኖር መለወጥና ማደግን ያመጣል:: ስለዚህ አዲስ አበባ በማያቋርጥ ሁኔታ ታድጋለች፣ ከዘንድሮ ለከርሞ የበለጠ ውሃና የውሃ አገልግሎት ያስፈልጋታል፣ የበለጠ መብራትና መብራት ኃይል ያስፈልጋታል፣ የበለጠና የተሻለ መንገድ ያስፈልጋታል፣ የተሻለና ዘመናዊ የባህል ማዕከል ያስፈልጋታል:: የከተማዋ አቀማመጥ ያማረና የፀዳ መሆን አለበት፣ መኖሪያ ብቻ ሳይሆን የመዝናኛና የአዕምሮ ተሀድሶ የምትሰጥ ከተማ መሆን አለባት፣ ለመኖርና ለመስራትም ጭምር የምትመረጥ ውብና ፅዱ ከተማ መሆን አለባት አዲስ አበባ::

በዓለም ላይ ያሉ ትልልቅ ከተሞች ምን እንደሚመስሉና ተቋሞቻቸው እንዴት እንደሆኑ፣ እንዴትስ እንደተስፋፉና እንደተሟሉ ማየትና ዱካቸውንም መከተል ያስፈልጋል:: የተወሰኑትን ለምሳሌ ያህል ብናይ፣ ውሃ ለአንድ ትልቅ ከተማ ለመጠጥ ብቻ ሳይሆን ለብዙ ነገሮች ወሳኝና አስፈላጊ ነው:: ለመጠጥ፣ ለመዋኛ፣ ለመዝናኛ፣ ለንግድ ወዘተ እጅግ ብዙ ለሆኑ ጉዳዮች ውሃ ▶

አስፈላጊ ነው:: በአውሮጳ ያሉ ከተሞች ምሳሌ ብንወስድ፣ ፓሪስ ፈረንሳይ፣ ፍራንክፈርት ጀርመን፣ ብራሰልስ በልጂዬም ወዘተ ሁሉም በከተማዎቹ መሀል ትልልቅ ጅረቶች አቋርጠው ይፈሳሉ:: የውሃ ፍላጎትን አስተማማኝ ከማድረግ ባሻገር ሁሉም ትልልቅ ጀልባዎችና መለስተኛ መርከቦችን ያስተናግዳሉ:: በውሃ ላይ ጉዞ ቱሪስቶችን ያዝናናሉ፣ ለከተሞቹም ውበት ይሆናሉ:: በተለይ ብራሰልስ አስገራሚ የሆነ ስራ በመስራት ነው ይህን አገለግሎት ሊሰጥ የሚችል ሰው ሰራሽ ጅረት የፈጠሩት:: ትልቅ ግድብ በመስራትና በከተማው መሀል ትልቅ ቦይ በመስራት ነው ትንንሽ መርከቦችና ጀልባዎች በከተማው መሀል እንዲርመሰመሱ ያደረጉት:: ለንደን ባሕር ላይ የተሰራች ከተማ ነች፣ ዋሽንግተን፣ ኒዮርክና ቦስተን አትላንቲክ ውቅያኖስ ጫፍ ላይ የተሰሩ ከተሞች ናቸው:: በሚኒሶታ ዋና ከተማው ሚኒያፖሊስ በአሜሪካ ትልቁ የሚባለው ወንዝ ሚሲሲፒ በመሀሉ አቋርጦ ነው የሚፈሰው::ሚኒሶታ እንደውም ዐሥር ሺህ ሐይቆች አሉባት ይባላል:: አሜሪካ ውስጥ እጅግ ብዙ ሰው ሰራሽ ሐይቆች አሉ:: ይህን ሁሉ የጠቀስኩት የውሃ አስፈላጊነት ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ለመግለፅና በንጽጽር የእኛ ከተማ አዲስ አበባ ምን ያህል ድርቅ ላይ እንዳለች ለማሳየት ነው:: እነዚህ ሁሉ አሁን በእጃችን ያሉ ሕንፃዎችና ወደፊትም የምንሰራቸው ሰማይ ጠቀሶቻችን እንዴት አድርገን ነው የምንኖርባቸው? አሁን ባለውና በሚታየው የከተማችን የውሃ ድርቅ? ሌሎችንስ ከተሞቻችን ስናያቸው ምን ያህል ያሳዝናሉ? አንዳንዶቹ፣ እረ እንደውም ብዙዎቹ በትንንሽ የውሃ ምንጮች አጠገብ ተሰርተው በውሃ ወረፋና ዕደላ የሚሰቃዩ ስንት ናቸው? አዲስ አበባስ እንዲህ በፍጥነት እያደገ የሚሄደውን ሕዝቧን ከየት አምጥተው ነው ውሃ የሚያጠጡት? የከተማዋንስ ፅዳት የሚጠብቁት? ይህ ነው እንግዲህ የገራችን የከተማ ምስረታ ታሪክ::

ስለዚህ አዲስ አበባ ዛሬ፣ አሁን ስለውሃ ያልተጨነቀች መቼ ነው የምትጨነቀው? እነዚህ የምንኖርባቸው ሕንፃዎች ያለውሃ ስንት ቀን ነው የምናድርባቸው ነው ወይስ በቦቴና በጀሪካን እየታደልን ነው ፅዳታችን የሚጠበቀው? ይህን ጥያቄ እንግዲህ የከተማው ባለስልጣናት ይመልሱት:: እኔ በበኩሌ ይህ እጅግ ብዙ ያስጨንቀኛል:: እንደሚመስለኝ አሁን በፍጥነት፣ ያለምንም መዘግየት አዲስ አበባ ላይ ብዙ ትልልቅ ጅረቶች/ሐይቆች(large streams/lakes) መፈጠር አለባቸው:: በክረምት ሰዐት መድረሻ የሚያሳጡንን ውሃዎች ገርተንና አላምደን (domesticating the wild water) ኗሪና ቋሚ የውሃ ሀብቶች ማድረግ አለብን::


በአንድ በኩል በምሥራቅ አዲስ አበባ ለገዳዴንና ገባሮቹን ወደአቃቂ አካባቢ ገድበን፣ በዚህ ተፋሰስ ያሉትን ወንዞች ሁሉ በዶዘር አርሶ ማገናኘትና ትልቅ ሰው ሰራሽ ጅረት/ሐይቅ (አነስተኛ መርከብና ጀልባ የሚያንሸራሽር ጅረት/ሐይቅ) መስራት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በምዕራብ አዲስ አበባ የገፈርሳን ግድብ አካቶ በወጨጫ ጋራ ላይ ገቶና በሦሥተኛ በኩል ደግሞ በለቡ በኩል አቃቂ አካባቢ የሚገደቡ ጅረቶችን በተመሳሳይ የመስራት ራእይ ይታየኛል:: ይህን የመሰለ ቅዠት ወደትልቅ ሀብት ሊለወጥ ይችል ይሆናልና መንግሥት ቢያስጠናው ሳይጠቅመን አይቀርም ብዬ አስባለሁ:: አለበለዚያ ግን አዲስ አበባችንን ወይ አዋሽ፣ ወይ አባይ ላይ ወይም ደግሞ ከነዚህ ከሁለቱ ወንዞች በአንዱ ገባር ላይ መገንባት ነበረብን! መቼም ውሃና የኤሌክትሪክ ኃይል አይነጣጠሉምና ይህ ዓይነቱ ፕሮጄክት የሁለቱንም ችግር በአንድ ጊዜ የሚፈታ ይመስለኛል:: የአሁኑን አላውቅም እንጂ ዱሮ ደሴ ቦርከና ወንዝ ላይ የተሰራ የራሱ ኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ ነበረው:: በሌላ በኩል ግን የሰው ኃይላችንን የማብቃት ስራ መስራት ደግሞ ለነገ የማይባል አጣዳፊ ጉዳይ ነው::

የመብራት ኃይላችንም እጅግ የሚያሳዝነኝና የሚገርመኝ፣ እንቆቅልሽም የሆነብኝ ጉዳይ ነው:: መ/ቤቱን ጠላት ወረረው ልበል ወይስ ምን? መልስ ያጣሁለት ጉዳይ በመሆኑ ለጊዜው የሚመለከተው ክፍል አንድ ይበለው እላለሁ:: የአገራችን ሀብት በውጭ ምንዛሬ የፈሰሰባቸው የመብራት አቅም ማሳደጊያና ማጎልበቻ ልዩ ልዩ እቃዎችና ትራንስፎርመሮች በየቦታው ወድቀውና ሳር በቅሎባቸው የአገሪቱ ሕዝቦች በኃይል ዕጥረትና በጨለማ ሲሰቃዩ ማየት ለሰሚው ግራ ነው:: እኔ ዘወትር በዋናነት የሚያሳስበኝ የውሃ ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ ውሃን ያስቀደምኩት፣ የውሃና የመብራት ጉዳይ በሰብኣዊ መብት ጥሰት ወደዓለም አቀፍ ፍ/ቤት የሚያስኬድ ነው:: ቤታችንን ፎቅ አድርገን፣ የምግብ ማብሰያችንን ኤሌክትሪክ አድርገን ዘመንኛ ኗሪዎች ከሆን በኋላ ውሃና መብራት ማጣት (lack of water and power means deprivation of life) ማለት በርግጥም የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፣ በርግጥም ወደዓለም ፍ/ቤት የሚያስኬድ ነው::

የዚህ ችግር መንስኤው ሁለት ይመስለኛል:: አንዱ ምናልባት የነበረው ሥርዓት ሠራተኞችን በተለያየ ምክንያት (በዋናነት ከዘረኛ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ) ከየመሥሪያ ቤቱ ሲመነጥር እንደነበር ይታወቃል:: ይህ ሁኔታ አገሪቱን እጅግ በርካታ የሰለጠኑና ረጅም ዓመታት የሥራ ልምድ ያካበቱ ሠራተኞችን አሳጥቷታል:: የነበረው መንግሥት ቂመኛና ለሀገር ዋጋ የማይሰጥ ስለነበረ፣ ስለሚጠፋውም ሆነ በሀገር ላይ ስለሚደርሰው ውድቀት ፈፅሞ የማይጨነቅ ስለነበር፣ በተለይ ኢትዮጵያዊነት ስሜትን ከማጥፋትና ማዳከም አንጻር ተግቶ ይሰራ ስለነበር ይችን ሀገር ቢያንስ ወደሚቀጥለው ዘመን ሊያሸጋግሯት ይችሉ የነበሩ ሰዎችን አሳጥቷታል (ለዚህ በአሜሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ የተበተኑ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠራተኞች ጥሩ ምሳሌ ናቸው):: ይህ ዘመቻ በሁሉም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በከፍተኛ ሁኔታና በተደራጀ መልኩ የተከናወነ ይመስለኛል:: ይህ ድርጊት አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ድርቅ ዋና ምክንያት ነው ብዬ አምናለሁ:: ሁለተኛው ያው ሁሉ ሰው እንደሚያውቀው በዘመኑ የሰፈነውና የተንሰራፋው የሥነምግባር ችግርና ደካማ የሰው ኃይል ሥልጠና ነው የሚሆነው:: በመጀመሪያ ደረጃ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ለሚገዛት ሀገር ምንም ደንታ ሳይኖረው ሕዝብን ያለያያል ብሎ በሚያስበው መንገድ ሁሉ የሚከፋፍልና የሚለያይ ከሆነ ሰዎች ለሀገራቸው ምንም ዓይነት የጋራ ራእይ አይኖራቸውም:: ይህ የጋራ ራእይ ከሌለ ደግሞ የጋራ ሀገራዊ ፍቅርም ሆነ የኃላፊነት ስሜትም አይኖርም:: በዚያ ላይ በአጠቃላይ በሀገሪቱ ውስጥ የተደራጀ የሥነምግባር ጥሰትና ዝርፊያ እነደነበር መንግሥት ራሱ ያረጋገጠውና እያረጋገጠውም ያለ ሂደት ነው:: ለዚህ ጉዳይ በግሌ የማየው ሁኔታ ማለትም በአንድ ሰፈር ውስጥ የሚታየው አገልግሎት አሰጣጥ መዘበራረቅ የሥነምግባር ችግር ለመኖሩ አመላካች ነው:: አንዱ ሕንፃ ላይ መብራት አለ፣ ከጎረቤት ያለ ሌላ ሕንፃ ላይ ግን መብራት የለም:: ይህ ደግሞ የአንድ ቀን ወይ የሁለት ቀን ክስተት አይደለም፣ ሁልጊዜም በዚህ መልክ ነው የምንቀጥለው:: ሁልጊዜ ስናስመዘግብና ሁልጊዜ ስንሄድ ባለሥልጣናቱ "ይህ ነገር ለምንድን ነው ሁልጊዜ እንዲህ የሚሆነው" ብለው አይጠይቁም:: "ሂዱ ይሰራላችኋል" የዘወትር የባለሥልጣናቱ መልስ ነው::

> የአዲስ አበባ መንገዶች አንድም ተጀምረው በአግባቡ የማያልቁ ወይም ደግሞ ሲሰሩ ውልግድግዳቸው የወጣና አገልግሎት ላይ በዋሉ በጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈራርሱ ናቸው

በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ መንገዶች አንድም ተጀምረው በአግባቡ የማያልቁ ወይም ደግሞ ሲሰሩ ውልግድግዳቸው የወጣና አገልግሎት ላይ በዋሉ በጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈራርሱ ናቸው:: የሚገርመው ደግሞ በተለያዩ የማቋረጫና መታጠፊያ መንገዶችን ተከትሎ ወደመንደር ውስጥ የሚያስገቡ መንገዶች ከመታጠፊያው መስመር የራቁ፣ የተንሸዋረሩና ትይዩ ባለመሆናቸው የተነሳ አሽከርካሪዎች ተቃራኒ መንገዶችን በመጠቀም ወደሚፈልጉት ሰፈር ውስጥ መግባት የሚገደዱበት ሁኔታ ነው ያለው:: ይህ ሁኔታ ለግጭት የሚዳርግ በመሆኑና በመንገዶች መሳለጥ ላይ የመጨናነቅ ችግር የሚፈጥር ስለሆነ በተሽከርካሪዎች መተላለፍ ላይ እንቅፋት ሆኗል:: ስለዚህ የመንገድና ድልድይ ሥራ መሀንዲሶች፣ እንዲሁም የመንገድ ሥራ ተቋራጮች እባካችሁ ለሀገራችሁ፣ ለታሪካችሁና ለትውልድ እያሰባችሁ ስሩ::



ተሾመ ሺፈራው

# ስርዓት አልባዋ ሀገር

> ከሰማይ ወዲህ ለሚሆን በደል መካሻው፤ ጊዜ የመረጠው ሹመኛ በበታቾቹ ለሚያዘንበው የግፍ ጎርፍ ማክሰሚያው ሕግ ነው፤ ሕግ የመጨረሻ ፍትህ፤ ሕግ የመጨረሻው ዳኝነት ነው፡፡ የተበደሉ የሚካሱበት፤ በባለቀን ሹማምንት እንባውን ጢቅ አድርጎ የረጨ ምስኪን ዜጋ እምባውን የሚጠርግለት ሕግና ስርዓትን በምታስጠብቅ ሀገር ነው

### እንደመንደርደሪያ

ቆስቋሽ ይፈልጋል፣ የሰው ልጅ እንደ እሳት ብለዋል፣ የሥነምግባር እና የሞራል ገጣሚ ናቸው የሚባሉት ጋዜጠኛ እና ገጣሚ ክቡር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል፡፡ እውነት ነው የሰው ልጅ ቀስቃሽ -ቆስቋሽ ፈላጊ ነው፡፡ ከነበረበት ሁኔታ (bad situation) ወደ ሌላ አዲስ ምዕራፍ ወይም በአዲስ የሕይወት ባቡር ተሳፍሮ ወደ ፊት ለመሸምጠጥ ወትዋች ጎትጓች ይፈልጋል፡፡ እኛም በአእምሯችን ውስጥ የሚብላላው መልካም ምኞት በሀገራችን ሰማይ ስር ተፈፅሞ እስክናይ 'በሰዎች ሀገር የምናየው የምንሰማው መልካም ነገር ሁሉ ይሄ መከረኛ ሕዝባችንም እንደሌሎች ዓለም ሀገራት ሕዝቦች ደጉ ሁሉ ደርሶት አይናችን እስከሚያይ መጮሀችንን እንቀጥላለን፡፡ ወትዋች መሳሪያ' መቀስቀሻ ኃይል የሆነውን ብዕራችን ቀለም እየነከርን እንኩላለን፣ ስለ ሀገር ስንል የብዕራችን ቀለም ከመቃው እያወጣን ሰፊው ብራና ላይ እናስከፋለን፣ ፊደላት እንደ ጡብ እንደረድራለን፡፡

ምክንያቱም መንግሥትም እንደ ሰው ቆስቋሽ ይፈልጋልና፡፡ ብዙ ጦማሪያን አንድም በማኅበራዊ ድረ ገጽ ሁለትም በየጋዜጣና በየመጽሄቱ ስለዚች ችግሯ እንደ ሸንፍላ ጠርቶ ስለማያልቀው ውድ ሀገራቸው ይሄን ብዕራቸውን ተግተው እያሰለቀሱት፤ የቋጠሩትን የሃሳብ ስልቻ እያወጡ በምድሪቱ እየዘሩት ነው፡፡ ያው እኔም እንደነሱ ስለሀገሬ የሚሰማኝን 'የውስጥ ህመም ሲያገረሽብኝ አወጣዋለሁ፡፡ ያው ስለ ሀገሬ ቀናኢ መሆኔ እንጂ አዲስ ሐሳብ የሚያፈልቅ ብቁ ብዕረኛ ሆኜም አይደለም፣ ከነዚህ ሀገር ወዳድ ጦማሪያን የተለየ ሀሳብ አልኩልም፤ አዲስ መንገድ አልጠቁምም፤ አዲስ ትንቢት አላሰማም፤ አዲስ መላ አላሳይም፡፡

ይልቁን እየተደረደሩ ባሉት የሀሳብ ጡቦች ላይ የራሴን የሀሳብ ጠጠር ጣል ማድረግ እንጂ፤ ከጤፍ ቅንጣት እንኳ ሺህ እጥፍ የምታንስ አእምሮዬ ውስጥ ሃሳብ ለመዝራት ነው፡፡ ወይም የጩኸቱን ድምፅ ማብዛት፣ ተደምሮ ኡኡ ማለት፣ እናም በሀገሬ ተስፋ ላይ የሚታይ የስጋት ደመና ጨርሶ ከጦቢያ ምድር ላይ ተገፎ እንደ ብናኝ (እብቅ) ብን ብሎ ድራሹ ይጠፋ ዘንድ የዜግነት ድምጼን አሰማለሁ፡፡ ኦዎ ወቅታዊ የመደመር ፅንሰ ሀሳብ ወይም ፍልስፍና ይኸው አይደል፤ ስንደመር ዋጋችንም፤ ሀሳባችንም ከፍ ይላል፡፡ እናም በብዕራቸው ከሚጮሁት ጋር እጮሀለው፤ ስለ ሀገሬ እንዲህ እላለሁ.....

### ከመጋረጃው በስተጀርባ፡-

"ለዚህ ቤት የማይነገር፤ የማይዘረዘር ብዙ ችግር፣ብዙ ፈተና አለ" የምትለው የጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ከሁለት ወር በፊት ከሀገሪቱ ጦር ሃይል ወደ ቤተ መንግስት አራስ ነብር ሆኖ መሸምጠጥ ጋር ተያይዞ የተናገሩት ንግግር ነው፡፡ ከዚች የንግግር ሀረግ ውስጥ ሀሳብ እንደ አለት ስር ምንጭ ፍልቅ አለችልኝና ብዕሬን ቀለም ሞላሁ፡፡ መቼም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ንግግር ሲያደርጉ ከፊታቸው ላይ የተመረገው ሀዘን የሚረሳም አይደል፡፡ እጅግ በሚያሳዝን፤ ጥልፍልፉ የፖለቲካ ሴራ ያደከመው፤ በሀገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ምክንያት የመከራ ቀምበሩ ያጎበጠው ሰው አይነት ስሜት እየተነበበባቸው ለሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ የተናገሩት ይህ ንግግር ብዙ ትርጉም ሰጥቶኝ አልፏል፤ ያው ብዙ የፖለቲካ ብዕረኞች እንዳሉት ሀገሪቱ ያለችበትን የተንሻፈፈ ቁመና ቦግ አድርጎ የሚያሳይ ከተማረረ መሪ የወጣ የመረረ ንግግር ነው፡፡ እናም የዚህ ንግግር ሀረግ የውስጥ ስሜቱ ሲመረመር፤ በቃላት የተጀቦነው ይህ እውነት የውስጥ ሞራው ሲነበብ ህዝብ ከሚያየው፤ ሀገር ከሚያውቀው ቀውስ ይልቅ ከመጋረጃው በስተጀርባ፤ በቤተ መንግስቱ ቅጥር ዙሪያ ምን ያክል የተጠላለፈ ረቂቅ የፖለቲካ ድራማ እየተመደረከ እንደሆነ በአደባባይ ይፋ አውጥተውታል፡፡

እንዴው ይቺ በግማሽ መፍረስና በግማሽ መገንባት መካከል ላይ ያለችው አገራቸው ነገረ ስራዋ (ሁኔታዋ) አስጨንቋቸው እንጂ ከመጋረጃ በስተጀርባ የሚጎነጎነው የፖለቲካ ገመድ መከራ ውስጥ እየጨመራቸው መሆኑን እጅግ በተከፋ ሰው ስሜት ውስጥ ▶

ሆነው ነግረውናል፡፡ ጨርሶ ባለየለት እንደውም ጨርሶ ድፍርስርስ እያለ ባለ ማኅበራዊ ቀውስ ውስጥ የተከተተው ህዝባቸው መጨረሻ እጣ ፈንታው ከልብ እንቅልፍ አላስተኛ ብሏቸው እንጂ በመንበሩ አካባቢ የሚቆሰቆሰው እሳት እጅጉን እንዳስከፋቸው ለሚወዳቸው እና ለሚወዱት የኢትዮጵያ ህዝብ እወቁልኝ ብለዋል፡፡ በፖለቲካዊ ንግግር ወይም ትርጉም የሕዝብን ድጋፍ (ተባባሪነት) ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደሚፈልጉ የተናገሩበት አጋጣሚ ነው፤ ብቻ ህዝቡ አብሮኝ ይቁም እንጂ ‘ሌላው ሌላው ሁሉ እዳው ገብስ ነው’ አይነት ስሜት ነው ያሰሙ፡፡ እርግጥ ነው፤ በሚታይና በማይታይ ፖለቲካዊ ውጥንቅጥ ውስጥ እንደከተተችናቸው እናውቃለን፡፡ ይህ የሴራውን ጠርዝ መንካት፤ የፈተናውን መደራረብ ከአንደበታቸው (from the hours mouth) እንደሚባለው መስማታችን እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገና ሀገሪቱን ሲቀበሉ ነው ፈተናዋንም አብረው የወሰዱ፡፡

አሁን ባለው ተጨባጭ የሀገሪቱ socio polotics ሁኔታ system (የተዋቀረ ስርዓት) የለም፡፡ ማለትም ሀገር በዚህ ወቅት ህግና ስርዓትን በሚያስከብር ተቋም ሳይሆን በአንድ ሰው ሃላፊነት ስር ወድቃለች፡፡ ስለዚህ የተበላሸሸው ተስተካክሎ፤ የወደቀው ተነስቶ፤ የደመነው የፖለቲካ ሰማይ ጠርቶ፤ ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ ሀገር እስክትፀና፤ የሀገሪቱ ሁኔታ ፍፁም በሚባል ደረጃ የመረጋጋት መልክ እስኪይዝ፤ በተቋማት መተዳደር እስክትጀምር ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ እጅ ላይ የወደቀውን የአሁኗ ኢትዮጵያ መሪዋን ከዚህ ከመጋረጃው በስተጀርባ ከሚጠነሰሰው የሴራ ፖለቲካ መታደግ ይኖርበታል፡፡ አዎ የጠቅላይ ሚኒስትሩን እዳ ለማቅለል፤ የውስጥ ፈተናውን ለመቀነስ መፍትሄውን ማስቀመጥ ግድ ነው፡፡

## ሕግ አስከባሪነት

በቅርቡ ነው፤ ከየትኛውም የመጽሔት ወይም የጋዜጣ ገፅ ላይ እንዳነበብኳት እንጃ እንጂ፤ ስለ እውነት እና ስለ ሥነ ጥበብ፤ ስለ ሕይወት እና ስለ እውቀት ህያው የሆነ ፍልስፍናዊ ፅንሰ ሀሳቦችን ለአለም ያበረከቱትን የጥንት የአቴና /የግሪክ/ ሊቆችን በምንጭነት በመጥቀስ ‘የሰው ልጅ ከፈጣሪው እና ከህግ በታች ነው- ንጉስንም ጨምሮ’ የምትል የህግን ልዕልና፤ የሕግን የበላይ ጠቅላይነት አይተኬ በሆነ ፍልስፍናዊ ሀረግ ተቀንብባ ቀርባለች፡፡ ከሰማይ ወዲህ ለሚሆን በደል መካሻው፤ ጊዜ የመረጠው ሹመኛ በበታቾቹ ለሚያዘንበው የግፍ ጎርፍ ማክሰሚያው ሕግ ነው፤ ሕግ የመጨረሻ ፍትህ፤ ሕግ የመጨረሻው ዳኝነት ነው፡፡ የተበደሉ የሚካሱበት፤ በባለቀን ሹማምንት እንባውን ጢቅ አድርጎ የረጨ ምስኪን ዜጋ እምባውን የሚጠርግለት ሕግና ስርዓትን በምታስጠብቅ ሀገር ነው፡፡

በነሱ ወርድና ቁመት ልክ ከርክመው በሰሩ ሕግ እየታጀቡ በገዛ ምድራቸው፤ በገዛ ስጋቸው ላይ ዳርቻ የሌለው ግፍ ሲያደርሱ የኖሩ የምድር ነገስታት በደላቸውን መመከቻ ብቸኛው ጋሻ ሕግና ሕግ ብቻ ነው፡፡ ይህ ግን እውነት የሚሆነው በአንድ ሀገር ውስጥ በትክክል እንዲህ አይነቱን በራስ ወገን እና በራስ ሀገር ላይ የሚፈፀመውን ወሰን የለሽ ወንጀል በትክክል መከላከል የሚችል የሕግ ተቋም ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ እውነት የሚሆነው በኋሮ በር ተሸሽገው በኢኮኖሚ ብዛት ወይም ስልጣን ባመቻቸላቸው ዕድል ተጠቅመው የፍትህ ተቋማትን እጅ መጠምዘዝ ከሚችሉ ስብስቦች ነፃ የወጣ የሕግ ተቋም ሲቆም ነው፡፡

አንዲት ሀገር በእውነትም እንደ ሀገር የሚያስቆጥራትን ሙሉ ሉአላዊነት አላት የሚባለው፤ በአንዲት ሰፊ ሀገር ጥላ ስር ተጠልለው የሚኖሩት ዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብታቸው ተከብሮላቸው የመኖር ዕድል የሚጎናፀፉት፤ የአንድን ሀገር socio politics ቁመና ወደ ሰፊው ህዝብ በማድረስ የዛች ሀገር ዜጎች በሀገራቸው ሁለንተናዊ ሁኔታ አሪፍ ንቃተ ህሊና ይጎናፀፉ ዘንድ ተግተው የሚሰሩ የፕሬስ ተቋማት ሊያቆጠቁጡ የሚችሉት ከላይ የተባለው እራሱን ችሎ የቆመ የሕግ ተቋም ካለ ብቻ ነው፡፡ አዎ በተጨባጭ ይች ሀገር አጥታ ያለችው ይህንን ትልቅ ሀገራዊ ፀጋ ነው፡፡ የተለያየ መልክና ቅርፅ እየያዙ የሚፈፀሙት ግለሰባዊና ተቋማዊ ጥቃቶችን መመከት የሚችል የሕግ አስፈፃሚ ተቋም እጦት አለባት፡፡

ይህንን ሀገራዊ ችግር ደግሞ አመራር ላይ ያለው አዲሱ የሽግግር መንግስት አምኖ ተቀብሏል፡፡ ለዛም ነው በየሁለት አመቱ በሚደረገው የኢህአዴግ ድርጅታዊ ጉባኤው ላይ የድርጅቱ አባላት ሰፊ ጊዜ ወስዶ ከተነጋገረባቸው ወቅታዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ውስጥ አንዱ የመንግስት ህግ አስከባሪነት ጉዳይ የነበረው፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ የህግ የበላይነት ወይም የህግ አስከባሪ ተቋማት ፈተናው ውስጥ ገብተዋል፡፡ በህዝቦች ዘንድ የሚፈፀመውን ኢ-ህገ መንገስታዊ ትዕይንት እና ራሳቸውን ከህጉ በላይ ባደረጉ ራስ ወዳድ ዜጎች በደል ሲፈፀም ከማንም በፊት ቀድመው ሊደርሱ የሚገባቸው የሕግ አስፈፃሚ አካላት ነገርየውን ከዳር ቆመው በትዝብት ለመመልከት ተገደዋል፡፡ አዎ የሰው ልጆችን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ ስጦታዎች (መብቶች) በማስጠበቅ ትጉ ዘብ ሆነው ባለመቆማቸው ምክንያት ነው ከቅርብ ጊዜ ወዲ እያሳዘነን ያለውን በደል በራሳችን ሰዎች ሲፈፀም አይተን አንገት ከመድፋት በቀር ችግሩን ከምንጩ ማድረቅ ያልቻልነው፡፡

በራሱ የሚመራ ህግ አስከባሪ ተቋማት ቢኖሩ ኖረው ከዚችው ኑሮችንን ከመሰረትንባት አዲስ አበባ ትንሽ ራቅ ብላ ከምትገኘው ቡራዩ ላይ የአንዲት ሉአላዊት ሀገርን ህገ መንግስት ፍፁም በተቃራኒ መልኩ አንዲት የዩንቨርስቲ ሴትን አስገድደው ከደፈሩ በኋላ እራሷን ስታ በተጋደመችበት ቀጥቅጠው እስከመግደል የሚያደርስ ከሞራል እና ከሰብዓዊነት በታች የሆነ ነውር አይፈፀምም ነበር፤ በእርግጥም ነፃ የህግ አስፈፃሚ አካላት (ተቋማት) ቢኖሩ ኖሮ በሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስም የሚተዳደረው የጦር ሰራዊት የራሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ለማጥቃት አፈ ሙዙን ወደ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት አነጣጥሮ ሲተም አይናችን ባለየ ነበር፤ ከተፅዕኖ የፀዳ የፍትህ (የህግ አስፈፃሚ ተቋም) ሀገሪቱ ቢኖራት ኖሮ ሀገሪቱን በጎሳ ትርምስ ለማጥፋት ከመጋራጃው በስተጀርባ ሆነው (አድፍጠው) እሳት የሚጭሩ የፖለቲካ ሴረኞችን ከየስርቻቸው እየመዘዘ ከህግ ፊት እንዲቆሙ በማድረግ በዚህ መከረኛ ህዝብ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ በቀነሱት ነበር፡፡ ራሱን አርነት ያወጣ የፍትህ ተቋም ወይም የመከላከያ ተቋም ቢኖር የማንንም ይሁንታ ሳይጠብቅ፤ ከማንም ወገን ፊሽካ ሳይነፋለት ህግና ስርዓት ተጣሰ፤ ማህበራዊ ሰላም ደፈረሰ ብሎ ባመነበት ቦታና ሁኔታ ሁሉ ደርሶ ቀውስ ከመሆኑ በፊት ስርዓት ባስከበረልን ነበር፡፡

በዘመኑ ሀገራት እና ዲሞክራሲ በሰረፀባቸው አካባቢዎች እንዳለው አይነት የነፃ ተቋማት አሰራር ስርዓት ቢኖር ኖሮ ይሄው ህግ አስከባሪው አካል አፍንጫው ስር ህግ ሲጣስ እያየ፤ በየአቅጣጫው ህገ መንግስት ‘ቫይዌሌት’ ሲደረግ እየተመለከተ አይቶ እንዳለየ፤ ጆሮ ዳባ ብሎ ባልተቀመጠ፡፡ በርግጥ አንድ የሚስማማ ሀቅ አለ፤ አንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ ቀድሞ ከነበረበት የ socio politics ርዕዮት ወጥቶ የአዲስ ፖለቲካ ርዕዮት በር ሲቆረቁር (ሲያንኳኳ) በዛች የቅብብሎሽ ወቅት ያለ ማኅበረሰብ የሚከፍለው ዋጋ እንደሚኖር አለማቀፋዊ እውነት ነው፤ ይህ በብዙ የምድራችን አብዮቶች ወቅት የተከሰተ ፖለቲካዊ ተፈጥሮ ነው፡፡ የብዙ አለም ሀገራት የስልጣኔ ገድላቸው ገለጥ ገለጥ ሲደረግ የምናገኘው የሽግግር ወቅት መስዋዕትነት አለው፡፡ ለዚህ ደግሞ ከአህጉራችን ደቡብ አፍሪካ ብንነሳ፣ ሩዋንዳ፣ ቻይና፣ እነሩሲያ፣ እነፈረንሳይ ዛሬ ላይ ለደረሱበት ቁሳዊ እና ሁሉን አቀፍ ስልጣኔ እጅግ እጅግ አሳዛኝ የተባለለት ዋጋ ገብረዋል፡፡ ምን ግዜም ቢሆን በለውጥ ፈላጊዎች እና በለውጥ ቀልባሾች መካከል አሰልቺ ግብግብ፤ የሚታይ እና የማይታይ ፍትጊያ ውስጥ መግባታቸው ተጠባቂ ነው፡፡

ከከፋፍለህ ግዛ (Divided and Rule) ስርዓት አቀንቃኙ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ወደ ግለሰባዊ ነፃነትን ወደ ሚያጎናፅፈው Libirelism ስርዓት ለመሸጋገር ይበልጥ ከባድ የሚሆነው ደግሞ ህግ አስከባሪ የሚባሉ የህግ አስፈፃሚ ተቋማት ነፃ አለመውጣታቸው ነው፤ በአንዲት ሀገር የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ የአንዲት አገር ሉአላዊነት በማንም ራስ ወዳድ ፖለቲከኛ ስር እንዳትወድቅ እንደነዚህ አይነት ተቋማት ከመቼውን ጊዜ ይልቅ በእንደዚህ ዓይነት ግርግር ወቅት ተቋማዊ ግዳጅ አለባቸው፡፡ በእንደዚህ አይነት ሀገራዊ ቀውስ ጥርስ አልባ መሆን ነገርየውን በሰንበት ላይ ደብረዘይት እንደሚባለው ነው፡፡ በአንድ ፈተና ላይ ለሌላ ፈተና፡፡ ያለፈው 27 ዓመታት የኢትዮጵያ ምድር ላይ ስር የሰደደው የአቢዮታዊ ዲሞክራሲ ልጆች (ፍሬዎች) እራሳቸውን እንደተጨቋኝ ሌላውን ደግሞ ጨቋኝ ብሎ በመመደብ በዳይና ተበዳይ ህብረተሰብ እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡

ስለዚህም ከስታሊናዊ የፖለቲካ ንድፈ ሀሳብ ወደ ማዕከላዊነት ለማምጣት ሀገሪቱን ትንሽ ድንግዝግዝ ውስጥ እንደሚያስገባ የሚጠበቅ እውነታ ነው፡፡ ከነበረው የፖለቲካ ስርዓት ፍፁም ተቃራኒ ወደ ሆነ ‘ኢትዮጵያዊነትን’ ወደ ሚያስቀድም ስርዓት በመሸጋገር ላይ ያለው ህዝብ የሚከፍለው ዋጋ ተመጣጣኝ ይሆን ዘንድ ህግ አስፈፃሚ አካላት (ተቋማት) ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የቤት ስራቸውን መስራት አለባቸው፡፡ ይህ ካልሆነ በነባሩ የብሔር ፖለቲካ አቀንቃኙ እና በዜግነት ፖለቲካ አራማጁ በሚያደርጉት ፍትትጎሽ ሀገር መከራዋ ይራዘማል፡፡

# በአቶ ጌታቸው አሰፋ ጉዳይ ፖለቲከኞች ምን ይላሉ?

የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ አቶ ብርሃኑ ፀጋዬ ከጥቂት ቀናት በፊት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመስሪያ ቤታቸውን የአምስት ወራት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት የእስር ትዕዛዝ የወጣባቸውን እና መቀሌ የሚገኙትን የቀድሞው የደህንነት መስሪያ ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው አሰፋን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ከትግራይ ክልላዊ መንግሥት በኩል ትብብር አለማግኘታቸውን ገልፀዋል።

ከክልሉ ይሁንታ ካለመገኘቱም ጋር ተያይዞ "እሳቸውን ለመያዝ ሌላ ሰው መግደል የለብንም" በማለት ጠቅላይ አቃቤ ህጉ የፌደራል መንግሥቱን አቋም አንጸባርቀዋል።

ይህንንም ተከትሎ በአንድ አገር ላይ የፌደራል መንግሥት በወንጀል የተጠረጠረን ግለሰብ ሲጠይቅ ክልሎች ያለምንም ማንገራገርና ለህገ መንግሥቱ ታዛዥ በመሆን አሳልፈው ሊሰጡ ይገባል የሚሉ እንዳሉ ሁሉ፤ የክልሉ መንግሥትና የፌደራል መንግሥት ተቀራርበው በመስራት ለጉዳዩ ፖለቲካዊ መፍትሄ ሊያበጁለት እንደሚገባ አስተያየታቸውን የሚሰጡም አሉ።

"ጌታቸው አሰፋ ለምን የትግራይ ክልል ጉዳይ ሆኑ?"

በሰብኣዊ መብት ጥሰት ተጠርጥረው ክስ የቀረበባቸው አቶ ጌታቸው ጉዳይ፤ ፖለቲካዊ ወይም ሕጋዊ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል የሚል የተከፋፈለ ስሜት በሚንሸራሸርበት ሰአት ከሕግ ጥያቄ ወጥቶ የፖለቲካ ጥያቄ የሚያደርገው ነገር መጀመሪያ ምላሽ ሊሰጠው እንደሚገባ የቀድሞው የኢዴፓ ፕሬዚዳንት አቶ ሙሼ ሰሙ ይናገራሉ። ለዚህም የፌደራል ወይም የትግራይ ክልል መንግሥት ኃላፊነታቸውን ሊወስዱ ይገባል ባይ ናቸው።

ምንም እንኳን የፌደራል መንግሥቱ ባለው ስልጣን መሰረት የማንንም ፍቃድ ሳይጠይቅ ወደ የትኛውም ክልል ሄዶ በወንጀል የጠረጠረውን ግለሰብ በቁጥጥር ስር የማዋል ስልጣኑ ቢኖረውም፤ ባላቸው የሻከረ ግንኙነት ምክንያት የፖለቲካ መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል የሚሉ አካላት አሉ። ለአቶ ሙሼ ይህ የማያስማማቸው ጉዳይ ነው።

"ለኔ ማንኛውም ነገር ከህግ በታች ነው። ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የህግ የበላይነት ላይ መተማመን ነው" ይላሉ።

የፌደራል መንግሥቱ የወንጀል ተጠርጣሪ አድርጎ ክስ እስከመሰረተባቸው ድረስ ማንኛውም ዜጋ በሚታይበት የህግ ስርአት መሰረት ነፃ፣ ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት ጉዳያቸው ሊታይ እንደሚገባ የሚናገሩት አቶ ሙሼ፤ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ተጠቅመዋል አልተጠቀሙም የሚለውን በፍርድ ቤት ሂደት ተጣርቶ የሚደረስበት እንደሚሆን ይናገራሉ።

ለዚህ ሁሉ ግን የህግ የበላይነት ፅንሰ ሃሳብ ላይ ከስምምነት ላይ ሊደረስ እንደሚገባ አፅንኦት ይሰጣሉ።

የፖለቲካ ጥያቄ ለመሆን የሚያስችለው ጉዳይ ምንድን ነው? በማለት በዋነኝነት ጥያቄ የሚያነሱት አቶ ሙሼ፤ ”አቶ ጌታቸው እንደ ግለሰብ ባላቸው የፖለቲካ አቅም ነው? በዙሪያቸው የተሰባሰበው ኃይል አለ? ወይስ ክልሉ ነው የፖለቲካ ጉዳይ ያደረገው?” የሚለው መልስ ሊሰጥበት ይገባልም ይላሉ።

"ከነበራቸው የኃላፊነት ሁኔታ ጉዳዩ ታይቶ የሚያመጣውን ደስ የማያሰኝ ሁኔታ ለማረምና ለማስተካከል ተፈልጎ ከሆነ ጉዳዩን በውስጥ ውይይት መጨረስ ተገቢ ነው።" ይላሉ አቶ ሙሼ።

በጉዳዩ ቢቢሲ ያነጋገራቸው ሌላናው ፖለቲካኛ ደግሞ ዶ/ር መረራ ጉዲና ናቸው።

የፌደራል መንግሥት ጥያቄ ባቀረበው መሰረት፤ የትግራይ ክልል አቶ ጌታቸው አሰፋን አሳልፎ የሚሰጥ ይመስልዎታል ወይ? በሚል ከቢቢሲ ለቀረበላቸው ጥያቄ ዶ/ር መረራ ጉዲና ሲመልሱ በወንጀል የተጠረጠረን ግለሰብ አሳልፎ መስጠት እንደሚገባ ገልጸዋል።

ይህ ካልተከናወነ ግን በቀጣይ ፈታኝ ሁነቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ስጋታቸውን ይገልጻሉ።

•"የፌደራል መንግሥት በወንጀል የጠረጠረውን ግለሰብ ክልል አላስረክብም ማለት ሌላ መንግሥት መፍጠር ነው የሚሆነው፤ ይህ ደግሞ ለትግራይም ሆነ ለኢትዮጵያ ህዝብ ቀጣይነት ፈታኝ ነው። መተባበሩ የሚመረጥ ይመስለኛል። " በማለት ይናገራሉ።

በወንጀል የተጠርጠረ ሰው ሊያገኘው የሚገባው መብት ሳይነካ በፍትሃዊ መንገድ ጉዳያቸው እንዲስተናገድ ዋስትና ይሰጠኝ ብለው መጠየቅ ይገባቸዋልም ይላሉ ዶ/ር መረራ።


መራራ ጉዲና


አብርሃ ደስታ


ዶ/ር መንግሥቱ አረፋይኔ


ሙሼ ሰሙ

ወንጀለኛ ተብሎ የተጠረጠረን ሰው አሳልፎ ስለመስጠት ሕጉ የሚለው ግልፅ ቢሆንም፤ አሁን ባለው የሃገሪቱ ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ ከፍተኛ ስጋትና፣ የኃይል ፍትጊያ በናረበት፣ ሃገሪቷን በሚመራው ኢህአዴግ ውስጥ ከፍተኛ መከፋፈል እያለ በተለይም ኢህአዴግን እንደ ግንባር ተሰብስበው ከመሰረቱት ጥምር ፓርቲዎች መካከል አንደኛው ተነጥሎ ኢላማ በመደረግ ህብረተሰቡን ከፋፍሎታል የሚሉት በመቀለ ዩኒቨርስቲ የሕግ መምህር የሆኑት ዶ/ር መንግሥቱ አረፋይኔ ናቸው።

ስልጣን የያዘው ቡድን የብቀላ ፖለቲካ የሚመስል አካሄድ አለው በማለትም የፌደራል መንግሥቱን ይወነጅሉታል።

"አንድ ክልል እየተገለለ ለሁሉም ወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ሰላምና መረጋጋትን ሊያመጣ አይችልም።" ይላሉ ዶ/ር መንግሥቱ አረፋይኔ።

ምንም እንኳን በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ ወንጀል የሰሩ ግለሰቦች የየትኛውም ብሔር አካል ይሁን ማንኛውንም ቋንቋ ይናገሩ ተጠያቂ ሊሆኑ ቢገባም ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው በሀገሪቱ ያሉ ግጭቶችንና ጦርነቶችን ማስቆም፣ መፈናቀልን መቀነስና ሃገሪቱ ከገባችበት ውጥንቅጥ የማረጋጋት ስራ መሰራት እንደሆነ ያስረዳሉ።

በዚህም ምክንያት ክልሉ አሳልፎ የመስጠት ያለመስጠት ቀላል ጥያቄ ነው ይላሉ።

"ለሃገሪቱ የሚያስብ መንግሥት ከሆነ የአንድ ወይም ጥቂት የግለሰቦች መታሰር ትልቅ ልዩነት አያመጣም።" ይላሉ

"ሃገሪቱ ውስጥ ብዙ ወንጀል የሰሩ ሰዎች ተፈትተዋል፤ መንግሥት ላይ ጦር ያነሱ ሰዎች በሰላም ግቡ ተብለዋል። በአንድ በኩል የእርቅ መንፈስና ሂደት መንግሥት እያከናወነ በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎችን ሰዎች ማሰር ምን አመጣው?" በማለት ጥያቄ ያነሳሉ።

አቶ ሙሼ በበኩላቸው የትግራይ ክልል አሳልፎ ሊሰጥ ይገባል ወይም አይገባም ከሚለው በፊት፤ የአቶ ጌታቸው ጉዳይ የትግራይ ክልል ጉዳይ ለመሆን መነሻው ምንድን ነው? የሚለው መሰረታዊ ጥያቄ መመለስ ያለበት ጉዳይ ነው ይላሉ።

ከዚህ በተቃራኒው ግን ይላሉ አቶ ሙሼ "በአግባቡ ያሉትን ሕጎች፣ ሕገ-መንግሥቱን ማዕከል ከማድረግ ይልቅ ጉዳዩ የህዝብ ግንኙነትና የመድረክ ፍጆታ ነው የሆነው። ይሄስ ጉዳይ ለህዝብ ፍጆታ የሚውለው ለምንድን ነው?" ሲሉም ይጠይቃሉ።

ምንም እንኳን በተለያዩ ማህበራዊ ሚዲያዎች ዘንድ የአቶ ጌታቸው አሰፋን ተላልፎ መሰጠት የትግራይ ህዝብ እንደሚቃወም ተደርጎ ቢቀርብም የአረና ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ አብርሃ ደስታ አቶ ጌታቸው ለትግራይ ህዝብ አጀንዳ አይደሉም ይላሉ።

ለዚህም እንደ መነሻነት የሚያነሳው አቶ ጌታቸው ከነበራቸው ስልጣን ተነስተው ወደ ትግራይ ክልል በመጡበት ወቅት ጥያቄ አለመነሳቱን ነው።

ምንጭ:ቢቢስ



ወንድሙ ነጋሽ
(ኢ/ር) ከለንደን

# “በፈተና ያልተፈተሸ ሕይወት ረብ የለሽ ነው”

## ሶቅራጠስ

### አጭር ማብራሪያ

ይህንን ጽሑፍ ለማሰናሰል የረዳኝን ዋና ጭብጥ ሲቢቲን(CBT) በማብራራት ልጀምር::ሲቢቲ በምእራቡ ዓለም በስፋት  የሚተገበር የአስተሳሰብ ሕክምና ሲሆን ምጽሐረ ቃሉም የሚከተለውን ይመስላል፤C= “Cognitive ”ን ይወክላል::በሕይወት ውስጥ እኛ ለክስተቶች ወይም ጉዳዮች ወይም ኩነቶች ላይ ያለን አመለካከትን እንጂ ማከም ያለብን ድርጊቶቹን አይደለም የሚል መሰረታዊ ትርጉም አለው:: B= “Behavioural ” ን ይወክላል::ለነገሮች የምንሰጣቸው ምላሾች በስሜታችንና በሀሳባችን ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖና የባሕሪ ለውጥን ይመለከታል::T= “Therapy” ን ይወክላል:: ስለ አንድ ነገር የሚኖረንን አስተሳሰብና ግምት በማስተዋል፣ ባህሪያችንን ቀስ በቀስ ለመግራት የምንሞክርበት ሂደት ነው:: አስተሳሰቦችንን እና ባህሪያችንን በተለመከተ የነደፍነውን የማሻሻያ እቅድ በተግባር ለመፈተሽ ሙከራዎችን እናዘጋጃለን:: ቀስ በቀስ ከውጤቶቹ እየተማርን እንደገና ለለውጥ እንተጋለን::

### ከሁሉ በፊት ራስህን እወቅ

ላይላ ሠላሳ ዓመቷ ነው::የአብራኳ ፍሬ የሆኑ ሦስት ልጆች አሏት:: ሕይወት ለላይላ ጣእም አልባ ሆናባታለች:: ጀምበር ወጥታ እስክትገባ ድረስ መተንፈሻ የላትም፤ባለቤቷ በጋራ በከፈቱት ጋራዥ ውስጥ ዘወትር ተፍ ተፍ ሲል እርሷ ደግሞ የቤት ጣጣውን ትሸፍናለች:: ምሽት ምሽት ደግሞ የገራዡን ሂሳብ ኦዲት ታደርጋለች::ባላት የተጣበበ ጊዜ ውስጥ በእድሜ የገፉ ወላጆቿን ለመንከባከብ ወደ መኖሪያ ቤታቸው በዕየለቱ መለስ ቀለስ ትላለች:: ባተሌነቷ በዚህ አያበቃም:: በአንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ የዲሲፒሊን ኮሚቴ በመሆን ነጻ አገልግሎት ትሰጣለች::ላይላ ይህንን ሁሉ ሃላፊነት በምትወጣ ጊዜ ከሰዎች የምትጠብቀው ፍጹም ይሁንታን ነው:: ሰዎች ስህተት አልባ ሥራ እንደምትሠራ እንዲያውቁላት በእጅጉ ትሻላች:: ይህ በሰዎች ዘንድ ስለእርሷ ያላቸው እምነት ከተጓደለ ግን የላይላ ስሜት በቀላሉ ይጎዳል::

አንድ ቀን እንደተለመደው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ትምህርት ቤቱ ጎራ አለች:: ያ ቀን መጥፎ ዱብዳ ጣለባት:: ድንገት ከአንዲት ወላጅ ጋር እዚህ ግባ በማይባል ጉዳይ እሰጣ ገባ ውስጥ ገባች:: ሴትየዋ የላይላን ስህተት መሥራት እየደጋገመች ትናገራታለች:: ይህ ደግሞ ለላይላ ከባድ ዱላ ነበር:: እርሷ በሌላ ሰው መተቸት በፍጹም ጤና አይሰጣታም:: ይረብሻታል፤ ስሜትዋ ቶሎ ይጎዳል:: እንደመተቸት የምትፈራው አውሬ የለም:: በዚህም ምክንያት ሌሊቱን በሙሉ ስታነባ አደረች:: ይህ የስሜት መጎሳቀል ነው ወደ እኔ የጤናና የስነልቦና ማዕከል ብቅ እንድትል ያስገደዳት :

“የበጎ ፍቃድ እሠራበታለሁ ባልኩበት ት/ቤት ውስጥ መልካም ባደረኩ እንዴት እወገዛለሁ? የጽድቅ ሥራ እስራለሁ ብዬ በዚህ መልኩ መተቸቴ በጣም እጅግ በጣም ተሰምቶኛል፤ ድሮም ይሄ ሕዝብ ወርቅ ይነጠፍልህ ሲባል ፋንድያ....” እያለች ቢሮዬ ውስጥ እንባዋን ዘራችው::

እንደተረዳዃት ከኾነ ላይላ ፍጹምነትን በራሷ ላይ ትጠብቃች:: ካላት የሳሳ በራስ መተማመን እና ስር የሰደደ የጸጸት ስሜት የተነሳ ሰዎችን ማባበል፣ በምላሹም ፍጹም እንደኾነች እንዲነገራት ትሻለች::ይህን የምታደርገው ኋላ ላይ ሊመጣባት ከሚችለው ደስ የማይል የትችት ስሜት ለመሸሸግ

ነው:: ጥሎባት ሁሉም ሰዎች የፍቅር ሰው እንደሆነች አድርገው እንዲስሏት ትፈልጋለች:: የኂላ ኂላ እንደተረዳኹት ሰዎች ስለርሷ ስለሚያስቡት ነገር አብዝታ መጨነቋ ሳይጎዳት አልቀረም::

እዚህ ጋር የምንረዳው አንድ ትልቅ ነጥብ አለ:: የላይላ ሰዎችን የማባበልና ስለርሷ በጎ አመለካከት

እንድይዙ አጥብቆ የመሻት ባህሪ በ “ሲቢቲ” አጠራር አስኳል እምነት በሚል ይታወቃል:: የላይላ አስኳል እምነት ሰዎችን ማባባልና ሁልጊዜም ከኔ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ ካልቻልኩ ዋጋ አይኖረኝም የሚል ነው:: ነገር ግን ይህንን አስኳል እምነት መገላለጥ እንድትችል ላይላን ብንረዳት ቀሪው ሥራ እጅግ በጣም ቀላል ይሆናል:: በእርግጥም ለይላ ለራሷ የሰጠችውን ያልተገባ ግምት ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መስበር ከቻለች እንደማንኛውም ሰው መሆን ትጀምራለች:: በዚህም ለይላ ከራሷ ጋር ትታረቃለች:: ይህም ሕይወቷ በሁሉም መስመር እንዲቃና ያደርግላታል::

አንዳንድ ሰዎች ሆደ ቡቡ ናቸው:: ለሠው ይራራሉ፤ ሠዎችን ማገዝ ያስደስታቸዋል:: ያንን የሚያደርጉት ግን እንደ አለመታደል ኾኖ ሰዎች ስለነርሱ መልካም ነገር እንዲያስቡ ለማድረግ ብቻ ይኾናል:: ይህ ቀስበቀስ ስለራሳቸው ፍጹምነትና እንከን የለሽነት አብዝተው እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል:: ስለራሳቸው የገነቡት ምስለ-ራስ ድንገት ሲነካ አእምሯቸውም አብሮ ይነካል:: በሁለት እግር መቆም ሁሉ ያቅታቸዋል:: ሕይወታቸው እንደ የእምቧይ ካብ ፍጹም ይናጋል:: ይህን አስኳል እምነታቸውን በማከም ወደ ጤናቸው መመለስ ግን ከባድ አይደለም::

### የሲቢቲ ምልከታ

ሲቢቲ አስተሳሰብህ እና ባህሪህ ከአንድ ወንዝ ነው የሚቀዱት ይልኻል::የምታሳየው ባህሪ የሚጸነሰው በአስተሳሰብህ ውስጥ ነው:: አስተሳሰብህ ደግሞ በባህሪህ ይገለጣል:: ይህ ነጥብ እጅግ

ቁልፍ ነጥብ ስለኾነ ልብ ብለህ ተከታተል:: ለመድገም ያህል ባሕሪህ የሚጸነሰው ከአስተሳሰብህ ነው:: ባህሪህ የአስተሳሰብ ሞተርህን ይቀሰቅሰዋል:: ወይም ደግሞ ሁሉቱ እርስ በእርስ አንዱ አንዱን እየቆሰቆሰ ያለማቋረጥ የሚሽከረከሩ መዘውሮች አድርገህ አስባቸው::

ለምሳሌ ሕዝብ ፊት ቆሞ ማውራት ትፈራለህ:: ያልብሀል:: ለምን ላባበኝ ብለህ ራስህን ጠይቅ እስኪ:: ያላበህ አዳራሹ ስለታመቀ ይመስልኻል? አይደለም:: ምክንያቱም የአዳራሹ መስኮቶች በሙሉ ቢከፈቱና አንድ ሺ የንፋስ ማራገቢያ አዳራሹ ውስጥ ቢሽከረከር ያንተን ፍርሃትና ላብ አያጠፉትም:: ያላበህ ሰዎች አንተ ላይ በሕብረት ስላፈጠጡ ይመስልኻል? አይደለም:: የሰዎች ዐይን ምንም ቢያፈጥ አንተ ላይ ትኩሳት የመልቀቅ ጉልበት አይኖረውም::

እውነት ለመናገር  አንተን ያላበህ አስተሳሰብህ ስላላበው ነው:: በሌላ አነጋገር አስተሳሰብህ (ሕዝብ ፊት ቆሞ የመናገር ግንዛቤህ) የፍርሃት ሞተርህን ተረክ አድርጎ ስላስነሳው ሰውነትህ ሁሉ መንዘፍዘፍ

ጀመረ:: እንደምታውቀው ሁሉም የሰውነት ክፍልህ ትዕዛዝ የሚቀበለው ከአእምሮህ ነው:: ይህም ማለት የፍርሃት አስተሳሰብ በአእምሮ ውስጥ ተጋግሮ ነበር ማለት ነው:: ይህ በአእምሮህ የተጋገረ የፍርሃት አስተሳሰብ ንግግሩን ለማድረግ ገና ከመድረክ ላይ መውጣት ስትጀምር እጅህ እንዲንቀጠቀጥ እና ፊትህ በላብ እንዲጠመቅ ምክንያት ሆኗል:: ስለዚህ እመነኝ ክምር ሶፍት ወረቀትና ተጣጣፊ ፎጣ ግንባርህ ላይ ሽፍ ያለ ላብህን ይቀንሱት ይኾናል እንጂ ዘላቂ መፍትሄ አይሰጡኽም:: ዘላቂ መፍትሄ ያለው ከአእምሮ ላይ ነው:: “ሲቢቲ” ለዚህ መፍትሄ ይጠቁምኻል::

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!





+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.facebooook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu
ኢ-ሜይል:
enqu2013@gmail.com